አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3532 | ቅዳሜ ሐምሌ 26 ቀን 2017 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# አረንጓዴ ዐሻራውን ያሳካነው

## “ሀብታም ስለሆንን ሳይሆን ሀብታም ልብ ያላቸው ዜጎች ስላሉን ነው”

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)



ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ቀዳማይ እመቤት ዝናሽ ታያቸው የዘንድሮውን የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር በጅማ ባስጀመሩበት ወቅት

**በሳህሉ ብርሃኑ**

በእንግሊዝ ሀገር የሚገኘው ናቹራል ሂስትሪ ሙዚየም (Natural History Museum) የአካባቢ ጉዳዮች ተመራማሪ ፕሮፌሰር አንዲ ፑርቪዝም የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር ያለውን ግንኙነት የተመለከተ ጥናት አካሂደዋል፡፡ ተመራማሪው በጥናታቸው እንደገለጹት፣ የዓለም ህዝብ ቁጥር በእጥፍ ከጨመረበት ከ1970ዎቹ ወዲህ ሰዎች በነፍስ ወከፍ የሚጠቀሙት የምግብ ፍጆታ በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመሩ የሰው ልጅ በተፈጥሮ ላይ እያሳረፈው ያለው ጫና ከፍተኛ ሆኗል፡፡ የሰው ልጆች እስከ አሁን ምድር ላይ በቆዩባቸው ጊዜያትም ቢያንስ 70 በመቶ የሚሆነውን የምድር ክፍል ለራሳቸው ምቾት ሲሉ ቀይረውታል፡፡

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

### የአንድ ጀንበሩን እጆች የሚፈልገው ምዕራፍ


6

ፎቶ- ከገፀ ድር

በግንፍሌ ወንዝ ዳር በተካሄደው የዘንድሮው የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር የተሳተፉ የህብረተሰብ ክፍሎች

### የልማት ምሰሶዎች


4

ፎቶ-ከፋይል

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ከፊል ገፅታ

### የተጫዋቾች ዝውውር ከሌላ ማዕዘን



20

ፎቶ- ከገፀ ድር

የ2025 የክረምት የዝውውር መስኮት ከፍተኛ የገንዘብ እንቅስቃሴዎችን አስተናግዷል

# የ4 ኪሎ ፈርጦች

## “አዲስ አበባን ከቀድሞ ታሪኮቿ ጋር እያጣጣምን ዘመናዊ ከተማ እያደረግናት እንገኛለን”

የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ

**በጊዜው አማረ**

አዲስ አበባ ትናንትን የምታስታውስ ታሪካዊ መዲና፣ ዘመናዊነትን ያቀፈች የዛሬ ከተማ እና የወደፊቱን ከግምት ያስገባች ማዕከል ሆና ብቅ እያለች ነው። ባለፉት ጥቂት ዓመታት በከተማዋ እየተሰሩ ያሉ መጠነ ሰፊ የልማት ስራዎች ታሪካዊነቷን ጠብቀው፤ ገጽታዋን እየቀየሩት ነው። ይህ ደግሞ አዲስ አበባ ለነዋሪዎቿ ምቹ እና ጽዱ እንድትሆን ከማድረጉም ባሻገር በዓለም አቀፍ ደረጃ ይበልጥ ማራኪና ተወዳዳሪ እንድትሆን እያደረጋት ይገኛል።

በከተማዋ እየተከናወኑ ያሉ የዘመናዊ ከተማ ግንባታዎች ብዙ ናቸው። ከፍታ ያላቸው ሕንፃዎች፣ ሰፋፊ መንገዶች፣ ዘመናዊ የመብራትና የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶች ደረጃዋን ከፍ እያደረጉት ይገኛል። የከተማዋን ውበት የሚጨምሩት የአረንጓዴ ልማት ፕሮጀክቶችም የዘመናዊቷ አካል ሆነዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዋና ዋና መንገዶችና በአደባባዮች ዙሪያ የተተከሉት ዛፎች

ወደ ገጽ 7 ዞሯል



ፎቶ- ከገፀ ድር

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የ4 ኪሎ ፕሮጀክቶች ምረቃ ላይ ንግግር ሲያደርጉ




# “የስራ እድል ፀጋዎችን ከወጣቱ ፍላጎት አንፃር መቃኘት የበጀት ዓመቱ ዋና ተግባር ነው”

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስራና ክህሎት ቢሮ

- **ለ350 ሺህ በላይ ዜጎች ቋሚ የስራ እድል ለመፍጠር እቅድ ተይዟል**

**በሰገነት አስማማው**

“የከፍተኛ ትምህርቴን ካጠናቀቅሁ በኋላ በተማርኩት ዘርፍ ስራ ለማግኘት ከነበረኝ ጉጉት የተነሳ በየቀኑ የስራ ማስታወቂያ እከታተል ነበር፡፡ ሆኖም ላገኝ ባለመቻሌ የቀን ስራም ቢሆን ማማተር ጀመርኩ፡፡ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በህዝብ መናፈሻ

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

# ርዕሰ አንቀፅ



## አረንጓዴ ዐሻራን ማኖርና መንከባከብ ይቀጥል!

የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ልክ እንደ የዓድዋ ድል እና ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሁሉ የኢትዮጵያውያን የጋራ ጉዳይ ከሆነ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ መርሃ ግብሩ ባለፉት ስድስት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል በነቂስ ወጥቶ እየተሳተፈበት ያለማቋረጥ በቋሚነት ተካሂዷል፡፡ ዘንድሮም የክረምቱ ወቅት ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በመላው የኢትዮጵያ ክፍሎች እየተከናወነ ይገኛል፡፡ በተለይ የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር በተሳካ አኳኋን ተከናውኗል፡፡

በዘንድሮው የአንድ ጀንበር መርሃ ግብር 700 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ የነበረ ሲሆን፣ በህዝቦች የጋራ ርብርብ 714 ነጥብ 7 ሚሊዮን ችግኞችን በመትከል ከእቅድ በላይ ማሳካት ተችሏል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መርሃ ግብሩን በጅማ ተገኝተው ባስጀመሩበት ወቅት ባስተላለፉት መልዕክት፣ በአረንጓዴ ዐሻራው ትልቅ ውጤት እየተገኘ መሆኑን አመላክተው፣ "አረንጓዴ ዐሻራውን ያሳካነው ሀብታም ስለሆንን ሳይሆን ሀብታም ልብ ያላቸው ዜጎች ስላሉን ነው" ሲሉ የህዝቦችን የመተባበር አቅም፣ አንድነትና አይበገሬነት ገልፀዋል፡፡

በአንድ ጀንበር ይህን ሁሉ ችግኝ መትከል በጣም ትልቅ እምርታ ነው፡፡ ይህ ውጤት የተገኘው በቂ ዝግጅት የተደረገበትና ዜጎች በእናታቸው ጀርባ ከታዘሉ እስከ አረጋውያን ድረስ የእለቱ የአየር ሁኔታ ሳይበግራቸው የተሳተፉበት በመሆኑ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ተባብረው ያሳኩት የ714 ነጥብ 7 ሚሊዮን የአንድ ጀንበር ችግኝ ተከላ በዓለም ትልቁ የአንድ ቀን የተከላ ውጤት ነው፡፡ በዚህ ዓመት በጠቅላላው ወደ 8 ቢሊዮን ገደማ ችግኞች ይተከላሉ። ይህን ማሳካት ከተቻለ እስከ አሁን ባሉት ጊዜያት በድምሩ 48 ቢሊዮን ችግኝ ተተከለ እንደ ማለት ነው፡፡

ጠቅላይ ሚስትር ዐቢይ (ዶ/ር) በመልዕክታቸው፣ "ለዕቅድ ዘመኑ መጠናቀቅ አንድ ዓመት እየቀረ 48 ቢሊዮን ችግኝ ከተተከለ በቀጣይ ዓመት ከሚከናወነው ተከላ ጋር ከ55 ቢሊዮን በላይ መትከል ተቻለ ማለት ነው፡፡ ይህም ኢትዮጵያ ትልልቅ ነገር ተልማ፣ አቅዳና ህዝቦቿን አስተባብራ ማሳካት እንደምትችል ለእኛም ለሌሎችም ማሳያ ነው" ሲሉ አንስተዋል፡፡ የዘንድሮው ክረምት ገና እየተጋመሰ በመሆኑ የዘንድሮውን እቅድ ጨምሮ አቅም የፈቀደውን ያህል ለመትከል በቀጣይ ጊዜያትም መረባረብ ያስፈልጋል፡፡

በ2011 ዓ.ም የአንድ ጀንበር የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ሐምሌ 22 ቀን 2011 ዓ.ም የተከናወነ ሲሆን 354 ሚሊዮን ችግኞች ተተክለዋል፤ በ2015 ዓ.ም ከ566 ነጥብ 8 ሚሊዮን በላይ፣ በ2016 ዓ.ም 615 ነጥብ 7 ሚሊዮን፣ ዘንድሮ ማለትም ከትናንት በስቲያ ሐምሌ 24 ቀን 2017 ዓ.ም ደግሞ በአንድ ጀንበር 700 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ 714 ነጥብ 7 ሚሊዮች ችግኞች ተተክለዋል፡፡

የአንድ ጀንበር መርሃ ግብሩ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ተነሳሽነት፣ አንድነትና ህብረት ወጥተው ችግኝ የሚተክሉበት ልዩ ዕለት እየሆነ መጥቷል፡፡ በርካታ ኢትዮጵያውያን አንድነታቸውን በሚያሳይ መልኩ ወጥተው ችግኝ መትከላቸው የአረንጓዴ ዐሻራ ፋይዳው ጉልህ መሆኑን ያመላከተ ነው፡፡

ህዝብ በአንድ ጀንበር ወጥቶ ችግኝ በሚተክልበት ወቅት ችግኞቹን ለመንከባከብ ሁሉም ዜጋ በራሱ ተነሳሽነት ማህበራዊ ኃላፊነቱን እንዲወጣ የሚያደርግ በመሆኑ፣ አንዱ ከሌላው ጥሩ ልምድ የሚወስድበት ዕድል ስለሚኖር ከመትከል ባሻገር የአረንጓዴ ዐሻራ ስራው በስኬት እንዲቀጥል ጥሩ መደላድል ይፈጥራል፡፡ ዞሮ ዞሮ የተከልናቸው አድገው ዛፍ እስኪሆኑ የመንከባከብ ኃላፊነት እንዳለብን በመገንዘብ ይኸንኑ መተግበር ያስፈልጋል፡፡

# የእኔ እይታ

**ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።**

## ያልተቀረፉት የትራንስፖርት አገልግሎት ችግሮች

በሀብታሙ ደበሌ

እየተሻሻለ በመጣው የትራንስፖርት አገልግሎት ውስጥ አሁንም አንዳንድ ችግሮች መስተዋላቸው አልቀረም። በዚህ ፅሁፍ ልገልፅ የምሞክረው በትራንስፖርት አገልግሎት፤ በተለይም በታክሲዎች ላይ የሚታየውን የአገልግሎት አሰጣጥ ውስንነት ነው። ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል ቢኖርም፤ ባለታክሲዎች ሕግና ስርዓትን አክብረው ለማገልገል የትራፊክ ፖሊሶችን ወይም የመንገድ ትራንስፖርት ባለሙያዎችን መኖርና አለመኖር የሚጠብቁበት ሁኔታ በስፋት ይታያል፡፡ ሕግና ሥርዓትን ማክበር ህሊናዊና ሞራላዊ ጉዳይ ከማድረግ ይልቅ፤ "በሌባ እና ፖሊስ" ዓይነት ድብብቆሽ የሚፈፀም መሆኑን አብዛኞቻችን የተመለከትንበት አጋጣሚ እንደሚኖር እገምታለሁ፡፡ የታክሲ አሽከርካሪዎች እና ረዳቶቻቸው እርስ በርሳቸው የሚግባቡባቸውን የምልክት ቋንቋዎች (ጡሩምባ፣ መብራት፣ እጅ ማውለብለብና የመሳሰሉት) ለዚህ ሕገ ወጥነት እንደ አንድ መሳሪያ አድርገው ይጠቀሙበታል፡፡

ትርፍ መጫን፣ አቆራርጦ መጓዝ፣ ከታሪፍ በላይ ማስከፈል በከተማዋ የታክሲ አገልግሎት ላይ ከሚስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች መካከል ይጠቀሳሉ። ትርፍ መጫን ሕጋዊና የተፈቀደ ይመስል የሚተገበርባቸው አካባቢዎች አሁንም አሉ፡፡ በተለይ የትራፊክ ፖሊሶች እና የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥርዓት አስከባሪዎች በማይደርሱባቸው ወጣ ወጣ ያሉ አካባቢዎችና የውስጥ ለውስጥ አጫጭር መስመሮች ላይ ትርፍ መጫን "እንደ መብት" የሚቆጠር ይመስላል። ከአስኮ አዲሱ ሠፈር እንዲሁም ከፈረንሳይ ጉራራ አራት ኪሎ ወይም ፒያሳ ጊዮርጊስ ያሉት የጉዞ መስመሮች እንቅስቃሴ ለዚህ ችግር ሁነኛ ማሳያዎች ናቸው፡፡ በእነዚህ መስመሮች ትርፍ መጫን፣ ከታሪፍ በላይ ማስከፈል እና አቆራርጦ መጓዝ በስፋት ይስተዋላል፡፡

ከፈረንሳይ ጉራራ- አራት ኪሎ ወይም ፒያሳ ጊዮርጊስ ባለው የጉዞ መስመር ትርፍ መጫን "መብት ነው" ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ በዚህ መስመር ላይ አቆራርጦ መጫንም የተለመደ ሕገ ወጥ ተግባር ነው፡፡ በተመሳሳይ ከአስኮ አዲሱ ሰፈር አካባቢም መሰል ችግር ይስተዋላል። በዚህ መስመር ላይ ለሚደረገው አጭር ርቀት የታክሲ አሽከርካሪዎች ለአንድ ሰው በ10 ብር አገልግሎት እንዲሰጡ የተፈቀደላቸው ቢሆንም፤ ተሳፋሪውን እጥፍ ለማስከፈል ምክንያቶችን ነው የሚፈልጉት፡፡ በተለይ ከምሽቱ 1:30 ሰዓት በኋላ ባለ 10 ብሩ የጉዞ ታሪፍ ወደ 20 ብር ከፍ ይላል፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ ትርፍ የመጫንን መብት ለራሳቸው በሰጡ አሽከርካሪዎች ነው፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች የተመደቡ ተራ አስከባሪዎችም የዚህ ሕገ ወጥ ተግባር ተባባሪ የሚሆኑበት አጋጣሚም ይስተዋላል፡፡

ሕገ ወጥነት ለማንም አይጠቅምም። የሚጠቀምም ካለ ቁጥሩ ጥቂት የሆነ ሕገወጥ ነው፡፡ በጥቂት ሕገ ወጦች ደግሞ የብዙሃኑ ማህበረሰብ መብት ሊጣስ አይገባውም፡፡ ስለዚህም ችግሩን በመረዳት መፍትሄ መስጠት ይገባል። ለመፍትሄው አጋዥ ይሆናሉ ብዬ ከማስባቸው ተግባራት ውስጥ ደግሞ ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባር አንዱ ነው፡፡ በተለይ የታክሲ አሽከርካሪዎች ሕግንና ተገልጋይን ማክበር ቀዳሚው ጉዳያቸው እንደሆነ ማወቅና መተግበር ይኖርባቸዋል፡፡ የትራፊክ ፖሊሶች እና የመንገድ ትራንስፖርት ሕግ አስከባሪዎች ሕገ ወጥነቱ በሚበዛባቸው አካባቢዎች ትኩረት ሰጥቶ በመሰማራት ሕግና ስርዓትን ማስከበር፣ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ መሥራት፣ ጥሰት በሚፈፅሙት ላይ አስተማሪ ቅጣት መውሰድ ይገባቸዋል እላለሁ፡፡

ADDIS MEDIA NETWORK
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜልባ ፕሪንቲንግ ፐብሊሺንግ ኤንድ ፓኬጂንግ ሼር ካምፓኒ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
አብርሃም ገብሬ
ሰገነት አስማማው
ለይላ መሀመድ
ሽዋርካብ ቦጋለ

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለሰ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# አረንጓዴ ... ከገጽ 1 የዞረ

ሰዎች እንደዚህ አሟጥጠው እየተጠቀሟት ያለችውን ምድር ግን ለመጠበቅ እያደረጉት ያለው ጥረት የሚያስተዛዝብ ነው የሚሉት ፕሮፌሰሩ፣ “በደን ልማት ስራ በአርዓያነት የሚጠቀሱት ቻይናውያን ‘ምድርን የምትጠብቅበት ከሁሉ የተሻለው ጊዜ ከሃያ ዓመት በፊት ነበር። ሁለተኛው ምርጥ ጊዜ ደግሞ አሁን ነው’ የሚል አባባል እንዳላቸው ጠቁመዋል፡፡ መላው የዓለም ሀገራትም ይህንኑ መርህ እንዲከተሉ ያሳስባሉ፡፡

የችግኝ ተከላን አስቸኳይነት እና ወዲያውኑ እርምጃ የመውሰድን አስፈላጊነትን ለመግለጽ ቻይናውያኑ የተጠቀሙበትን ይህን ድንቅ አባባል የተገነዘቡት እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገራት ታዲያ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ሀገርን አረንጓዴ ለማልበስ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የዘንድሮውን የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ባስጀመሩበት ወቅት ባስተላለፉት መልዕክት በአረንጓዴ አሻራው ትልቅ ውጤት እየተገኘ መሆኑን አመላክተው፣ “አረንጓዴ ዐሻራውን ያሳካነው ሀብታም ስለሆንን ሳይሆን ሀብታም ልብ ያላቸው ዜጎች ስላሉን ነው” ብለዋል፡፡

አክለውም፣ “ዜጎቻችን ልባቸው ሀብታም፤ አርቆ ማየትን፣ የጋራ ራዕይ መሰነቅን፣ አብሮ መቆምን፣ በጋራ መስራትን፣ በልፋትና በድካም ውስጥ ውጤታማ መሆንን ያውቃሉ፡፡ ዜጎቻችን ይህን ያሳኩት ትርፋማነት ለራስ ብቻ ሳይሆን ለልጆቻችንም ጭምር መሆኑን ማመን ስለቻሉ ነው፤ ለዚህም ነው በአረንጓዴ ዐሻራ ስራ የተሻለ ውጤት ያገኘነው” የሚል ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአንድ ጀንበር 700 ሚሊዮን ችግኝ የመትከል መርሃ ግብርን በጅማ ባስጀመሩበት ወቅት በሰጡት ማብራሪያ፣ በአንድ ጀንበር ይህን ሁሉ ችግኝ መትከል በጣም ትልቅ እምርታ መሆኑን ገልፀው፣ ይህ ውጤት በዓለም ትልቁ የአንድ ቀን ተከላ ውጤት ነው ብለዋል፡፡ አክለውም፣ “በዚህ ዓመት ወደ 8 ቢሊዮን ገደማ ችግኞች ይተከላሉ። ይህንን ካሳካን በድምሩ 48 ቢሊዮን ችግኝ እንተክላለን ማለት ነው” ሲሉም ተደምጠዋል፡፡

“ዕቅዳችን 50 ቢሊዮን መትከል ነው። ለዕቅድ ዘመኑ መጠናቀቅ አንድ ዓመት እየቀረ 48 ቢሊዮን ችግኝ ከተተከለ በቀጣይ ዓመት ከሚከናወነው ተከላ ጋር ከ55 ቢሊዮን በላይ መትከል ተቻለ ማለት ነው፡፡ ይህም ኢትዮጵያ ትልልቅ ነገር ተልማ፣ አቅዳና ህዝቦቿን አስተባብራ ማሳካት እንደምትችል ለእኛም ለሌሎችም ማሳያ ነው” ብለዋል፡፡

የምግብ እጥረት፣ የድህነትና የችግር ምሳሌ ተደርጋ ትወሰድ የነበረችው ኢትዮጵያ አሁን መልኳና ስሟ እየተቀየረ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፣ “ይህ እየሆነ ያለው ሰርተን ነው። ጭቃ አብኩተን፣ አፈር ነክተን ነው፡፡ ማንም ይህንን ሊያደርግልን አይችልም፤ እኛው ሰርተን፣ ምግባችንን በጓሯችን አምርተን ኢትዮጵያን ከችግር ማውጣት አለብን፤ ይህን ማድረግ የዜጎቿ ኃላፊነት ስለሆነ በመጀመሪያ ችግሩን (የድሃ ሀገር ዜጎች መሆናችንን) አምነን መቀበል፣ መስማማት፣ አንድ የጋራ ራዕይ መሰነቅ፣ ራዕዩን ለማሳካት ደግሞ በጋራ መረባረብ ነበር የሚጠበቅብን፤ አካሄዳችን ተስፋ ሰጪ ነው፤ ዘንድሮ በታቀደው መሰረት እየተከናወነ ነው ያለው” የሚል ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

በዘንድሮው የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ከ714 ነጥብ 7 ሚሊዮን በላይ ችግኞች መትከል መቻሉን ልብ ይሏል፡፡

የዓለም ጤና ድርጅት ምድርን አረንጓዴ ማልበስ የሚኖረውን ዘርፈ ብዙ ፋይዳ አስመልክቶ እ.ኤ.አ በ2023 ይፋ ባደረገው መረጃ፣ የአረንጓዴ ልማት የተለያዩ የዕፅዋት ዝርያዎች በአንድ ስፍራ እንዲለሙ በማድረግ ልዩ ልዩ የእንስሳት ዝርያዎች በምቾት የሚኖሩበትን ዕድል ይፈጥራል፤ ይህም ብዝሃ ሕይወት እንዲኖር ያደርጋል። ፓርኮች፣ መናፈሻዎች እና አረንጓዴ ኮሪደሮች የዱር እራዊትን የሚደግፉ እና ዝርያዎችን ለመጠበቅ የሚያበረታቱ የስነ-ምህዳር መረቦችን ይፈጥራሉ ይላል።

በአረንጓዴ ልማት ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎችን ያስገኛል የሚለው መረጃው፣ አረንጓዴ ቦታዎች የንብረት እሴቶችን ይጨምራሉ፣ ቱሪስቶችን ይስባሉ፣ ጤናማ የአኗኗር ዘይቤዎችን በማስተዋወቅም ለህክምና የሚውለውን በርካታ ገንዘብ፣ ጉልበትና ጊዜ በመቀነስ ሀገራት አቅማቸውን በሌሎች ልማቶች ላይ እንዲያውሉ ዕድል ይሰጣል፡፡

የደን ልማትና የደን ምርቶች ለሀገራዊ ኢኮኖሚ ያላቸውን አስተዋጽኦ በተመለከተ በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል። እነዚህ ጥናቶች የደን ልማት ስራ እንደ እንጨት፣ ፍራፍሬ፣ ማር፣ መድኃኒትነት ያላቸው ዕፅዋት፣ ለእንስሳት መኖነት የሚያገለግሉ ምርቶችን ለማግኘት እንደሚያግዝ ያብራራሉ፡፡ እንደዚሁም የገቢ ምንጭነት፣ ለውጭ ምንዛሪ ማስገኛነት እና ለጥቅል ሀገር ውስጥ ምርት (GDP) ዕድገት ፋይዳ እንዳላቸውም ይጠቁማሉ፡፡

በአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ዙሪያ ከዚህ ቀደም ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ሙያዊ ማብራሪያ የሰጡት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሰቲ የእፅዋት ኢኮሎጂ እና ብዝሃ ህይወት ተባባሪ ፕሮፌሰር ገመዶ ዳሌ (ዶ/ር)ዓለም በተለይ ባለፉት 50 ዓመታት ሰዎች የሚፈልጉትን የማቅረብ አቅሟ እየተሟጠጠ መምጣቱን ጠቅሰው፣ ሰዎች ለአካባቢያቸው በቂ ጥበቃ እያደረጉ ባለመሆናቸው የደን መጨፍጨፍ፣ የመሬት መራቆትን፣ የብዝሃ ህይወት መጥፋትና ብክለትን እንድንጋፈጥ ሆነናል ይላሉ፡፡

ዛፎች የአፈር ለምነትን በማሻሻል፣ ውሃ በመያዝ እና የአየር ንብረትን በማስተካከል የግብርና ምርቶችን ለማሳደግ ይረዳሉና የችግኝ ተከላ ስራ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ የሚገባው ጉዳይ ስለመሆኑም አስረድተዋል። ዛፎች ንፁህ አየር የሚሰጡን፣ በነጻ የሚንከባከቡን ጸጋዎቻችን በመሆናቸው እያንዳንዱ ሰው ባለው አካባቢ አንድ ዛፍ መትከልና መንከባከብ ይኖርበታል፡፡ ይህን ሲያደርግ ቤተሰቡንና አካባቢውን ተንከባከበ ማለት ነው ሲሉም ይመክራሉ፡፡

ገመዶ ዳሌ (ዶ/ር) ቻይናን በአብነት በማንሳት በአረንጓዴ ልማት ስራዋ ከፍተኛ ገንዘብ ወጪ በማድረግ እና ሰፋፊ ፕሮጀክቶችን በመተግበር በርካታ ጥቅሞችን እንዳገኘች ይገልጻሉ። ሀገሪቱ ደንን በማልማቷ ተጠቅማለች ያሏቸውን ጉዳዮች ሲዘረዝሩም የደን ሽፋን መጨመር፣ የካርቦን ልቀትን መቀነስ፣ የአየርና ውሃ ጥራት መሻሻል፣ የኢንዱስትሪ ልማት፣ የስራ ዕድል ፈጠራና የህዝብ ጤና መሻሻልን ከብዙ በጥቂቱ መጥቀስ ይቻላል፡፡

ቻይና በታዳሽ ኃይል ላይ ባደረገችው ከፍተኛ የገንዘብ ወጪ የካርቦን ልቀትን በመቀነስ ረገድ ትልቅ እመርታ አሳይታለች። እ.ኤ.አ በ2024 ከዓለም አቀፍ ታዳሽ ኃይል አቅም ውስጥ ከ40 በመቶ በላይ የሚሆነውን ድርሻ የያዘች ሲሆን፣ እ.ኤ.አ በ2022 ደግሞ በታዳሽ ኃይል ምርት ወደ 2 ነጥብ 26 ቢሊዮን ቶን ካርቦን ዳይኦክሳይድ ልቀትን ቀንሳለች።

ልክ እንደ ቻይና ሁሉ ኢትዮጵያም ባለፉት ጥቂት ዓመታት ባከናወነችው የደን ልማት ስራ በርካታ ስኬቶችን አስመዝግባለች፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት ይፋ ባደረገው መረጃ መሰረት የኢትዮጵያ የደን ሽፋን የአረንጓዴ ዐሻራ ንቅናቄ በተጀመረበት ወቅት (በ2011 ዓ.ም) ከነበረበት 17 ነጥብ 2 በመቶ አሁን ወደ 23 ነጥብ 6 በመቶ ከፍ ማለት ችሏል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) በማብራሪያቸው፣ በአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ከ20 እስከ 30 ሚሊዮን የሚደርስ ህዝብ እንደሚሳተፍ (በዘንድሮው የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ብቻ 29 ነጥብ 7 ሚሊዮን ሰዎች መሳተፋቸውን ልብ ይሏል) ጠቁመው፣ በዚህ አስደናቂ ስራም ኢትዮጵያ ያሰበችውን ማሳካት እንደመትችልና የአረንጓዴ ዐሻራው ልክ እንደ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የኢትዮጵያውያን ትልቅ የዐሻራ አካል ነው ብለዋል፡፡ አክለውም፣ በዚህም አትርፈናል፤ በቡና፣ በሻይ፣ በፍራፍሬና አትክልት ቀላል ያልሆነ ትርፍ አግኝተናል በማለት አብራርተዋል፡፡

“ይህ ታላቅ ዓላማ እንዲሳካ በረደን፣ ሰለቸን ሳይሉ በብርድ እና በዝናብ ሳይበገሩ አስተዋፅኦ ላበረከቱ ዜጎች ምስጋና ይገባቸዋል” ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ “ጀምረናል እንጨርሳለን፤ ተልመናል እናሳካለን፤ ድሃ ነበርን እንበለፅጋለን፤ የኢትዮጵያ ስም፣ መልክና ታሪክ ይቀየራል፤ የዚህ ታሪክ አካል መሆን መታደል ስለሆነ ሁላችንም ዕድሉ እንዳያመልጠን እንበርታ” የሚል መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡



ፎቶ ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ቀዳማይ እመቤት ዝናሽ ታያቸው የዘንድሮውን የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር በጅማ ባስጀመሩበት ወቅት

# የልማት ምሰሶዎች



ፎቶ ከፋይል
ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ከፊል ገፅታ



ፎቶ ከፋይል
የቻይናው ስሪ ጎርጅ ግድብ ከፊል ገፅታ

**በሳህሉ ብርሃኑ**

በዓለም ላይ በርካታ ሀገራት ሰፋፊ ግድቦችን በመገንባት ከፍተኛ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጠቀሜታዎችን አግኝተዋል። እነዚህ ግዙፍ የውሃ ማጠራቀሚያዎች ለኃይል ማመንጫ፣ ለመስኖ ልማት፣ ለጎርፍ መከላከልና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። በዚህ ጽሑፍም ትልልቅ ግድቦችን ገንብተው የተጠቀሙ አንዳንድ ሀገሮችን እንመለከታለን።

በጥቂት አስርት ዓመታት ውስጥ ጠንካራ ኢኮኖሚ ወደገነባችውና በርካታ ግድቦች ወዳሏት ቻይና ስናቀና ‘ሦስቱ ገደሎች’ ግድብን እናገኛለን። በዓለም ትልቁ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ የሆነው ‘ስሪ ጎርጅ’ ግድብ (Three Gorges Dam) በያንግትዜ ወንዝ ላይ የተገነባ ሲሆን፣ ለቻይና ከፍተኛ መጠን ያለው ንጹህ ኃይል ያቀርባል። በተጨማሪም ለጎርፍ መቆጣጠሪያነት፣ ለመርከብ ትራንስፖርት እና ለመስኖ ልማት ትልቅ አስተዋፅዖ አድርጓል።

ግንባታው እ.ኤ.አ በ2008 የተጠናቀቀው ይህ ግድብ 30 ቢሊዮን ዶላር ወጪ ተደርጎበታል፡፡ በቻይና በያንግዜን ወንዝ ጠባብ ሸለቆዎች ላይ ከተገነቡ ሶስት ግድቦች መካከል 22 ነጥብ 5 ጊጋ ዋት በማመንጨት ‘ሦስቱ ገደሎች’ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ከዓለማችን ትልልቅ የውሃ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ጎራ መሰለፍ ችሏል፡፡ በቻይና ‘ስሪ ጎጅስ ኮርፖሬሽን’ የተገነባው ይህ የውሃ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ቁመቱ 185 ሜትር ሲሆን፣ 2 ሺህ 309 ሜትር ደግሞ ይሰፋል፡፡ ግድቡ በአጠቃላይ ካሉት 32 የኃይል ማመንጫ ተርባይኖች መካከል በግራ በኩል 14 እንዲሁም በቀኝ በኩል ደግሞ 12 ዋና የኃይል ማመንጫ ተርባይኖች አሉት፡፡

እነዚህ ኃይል አመንጪ ተርባይኖች እ.ኤ.አ በ2008 ወደ ስራ ሲገቡ 18 ሺህ 300 ሜጋ ዋት ኃይል ማመንጨት ችለዋል፡፡ በኋላ ደግሞ 6 የምድር ኃይል ማመንጫዎች ምድር ውስጥ በሚገኘው የግንባታው ክፍል ውስጥ የተተከሉ ሲሆን፣ ሶስት ዓመታትን ቆይቶ እ.ኤ.አ በ2011 ከእነዚህ 6 ተርባይኖች መካከል ሶስቱ ስራ እንዲጀምሩ ተደረገ። በመቀጠልም በዚያኑ ዓመት ቀሪዎቹ በመሬት ውስጥ የተተከሉት 31ኛ እና 32ኛ ተርባይኖች ኃይል ማመንጨት ጀመሩ። በመጨረሻም 32ቱ የኃይል ማመንጫ ተርባይኖች በሙሉ አቅማቸው ኃይል ማምረት ሲጀምሩ አጠቃላይ ያመነጩት ኃይል 22 ሺህ 500 ሜጋ ዋት ሆኖ ተመዝግቧል ይላል የፓወር ቴክኖሎጂ ዶት ኮም ገፀ ድር መረጃ፡፡

ይህን ግድብ ቻይና በምትገነባበት ወቅት፣ “እኛ እያለን ብቻሽን ይህን ግዙፍ ፕሮጀክት አትገነቢም፤ ባይሆን በምንችለው ቤት ባፈራው አቅም ሁሉ አለንልሽ” ሲሉ እንደ ጀርመን፣ ስዊዘርላንድ፣ ስዊድን፣ ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ እና ጃፓን እጃቸውን ለድጋፍ እንደዘረጉላት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

አህጉረ አፍሪካም ለረዥም ጊዜ የኃይል አቅርቦት እና የውሃ እጥረት ፈተናዎች ሲገጥሟት ቆይቷል። ይሁን እንጂ አንዳንድ የአፍሪካ ሀገራት ትልልቅ ግድቦችን በመገንባት እነዚህን ተግዳሮቶች ለመቅረፍና የኢኮኖሚ እድገትን ለማምጣት ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ነው። እነዚህ ግዙፍ የውሃ ማጠራቀሚያዎች ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ ለመስኖ ልማት፣ ለጎርፍ መከላከል እና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ወሳኝ ናቸው። ከእነዚህም መካከል ለሀገሪቱ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ እያደረገ የሚገኘውና በደቡብ አፍሪካ ያለው ትልቁ የውሃ ማጠራቀሚያ የሆነው ጋሪየፕ ግድብ (Gariep Dam) አንዱ ነው፡፡

ይህ ግድብ በኦሬንጅ ወንዝ ላይ የተገነባ ሲሆን፣ ለደቡብ አፍሪካ በርካታ ጥቅሞችን ያስገኛል። ከግድቡ ዋነኞቹ ጥቅሞች አንዱ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ መሆኑ ነው። በግድቡ ግድግዳ ውስጥ የሚገኙት አራት የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ጄኔሬተሮች ለደቡብ አፍሪካ የኃይል አቅርቦት ከፍተኛ ድርሻ ያበረክታሉ። እነዚህ ጄኔሬተሮች በተለይም የኃይል ፍላጎት በሚጨምርባቸው ሰዓታት (peak hours) እና ድንገተኛ ሁኔታዎች ላይ ለሀገሪቱ የኤሌክትሪክ ኃይል በማቅረብ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ።

ካሪባ ግድብ ላይ ጥናት ያደረጉት አንትሮፖሎጂስቱ ታየር ስካደር እንደሚሉት ግድቡ ከሚያስገኛቸው ትልልቅ ጥቅሞች አንዱ ለመስኖ ልማት የሚያቀርበው ውሃ ነው። ከግድቡ በስተጀርባ ያለው ሰፊ የውሃ ማጠራቀሚያ በሺዎች ለሚቆጠሩ ሄክታር የእርሻ መሬቶች የመስኖ ውሃ ያቀርባል። በተለይም በ‘ኦሬንጅና ፊሽ’ ወንዞች ሸለቆዎች የሚገኙ የእርሻ መሬቶች በጋሪየፕ ግድብ ከሚገኘው ውሃ ተጠቃሚ ይሆናሉ። ይህ የመስኖ ልማት የሀገሪቱን የምግብ ምርት በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ይረዳል። ውሃው ወደ ታላቁ ፊሽ ወንዝ በ82 ኪሎ ሜትር ርዝመት ባለው ‘ኦሬንጅና ፊሽ’ ዋሻ አማካኝነት ይተላለፋል፤ ይህም ለምስራቅ ኬፕ ግዛት ሰፊ የግብርና አካባቢዎች ውሃ ያደርሳል።

የጋሪየፕ ግድብ ለደቡብ አፍሪካ ከተሞች እና ለኢንዱስትሪዎችም የመጠጥ ውሃ ያቀርባል። እንደ ብሎምፎንቴይን (Bloemfontein) እና ግቄበርሃ (የቀድሞዋ ፖርት ኤልዛቤት) ላሉ ከተሞች የውሃ አቅርቦት ወሳኝ ነው። ይህም የህዝብ ጤናን ከመደገፍ ባሻገር የከተሞችን መስፋፋትና የኢንዱስትሪዎችን ሥራ ያረጋግጣል።

የ‘ሃይድሮ ፓወር ኦርግ’ን ገፀ ድር መረጃን ዋቢ አድርገን ስንመለከት ‘ኦሬንጅና ፊሽ’ ወንዝ ዋሻ በተፈጥሮው በጎርፍና በድርቅ ሁኔታዎች መካከል የሚለዋወጥ ነው። ጋሪየፕ ግድብ የዚህን ወንዝ ፍሰት በመቆጣጠር ለታችኛው የ‘ኦሬንጅና ፊሽ’ ወንዝ አካባቢዎች የጎርፍ አደጋን ለመቀነስ ይረዳል። በዚህም የጎርፍ መቆጣጠሪያ ዘዴ ንብረትን ከመጠበቅ ባሻገር የህዝብን ደህንነት ያረጋግጣል።

> **ግድቦች ግዙፍ የውሃ ማጠራቀሚያዎች ሲሆኑ ለኃይል ማመንጫ፣ ለመስኖ ልማት፣ ለጎርፍ መከላከልና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ**

ከላይ ከተጠቀሱት ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች በተጨማሪ፣ የጋሪየፕ ግድብ በአካባቢው ለመዝናኛና ለቱሪዝም ትልቅ አስተዋጽዖ አለው። ግድቡ ያለው ሰፊ የውሃ አካል ለጀልባ ጉዞ፣ ለዓሳ ማጥመድና ለውሃ ስፖርቶች ምቹ ነው። በአካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችም ለቱሪስቶች መስህብ ናቸው። ይህ ደግሞ በአካባቢው የቱሪዝም ኢንዱስትሪን በማሳደግ የስራ ዕድሎችን ይፈጥራል። በአጠቃላይ እንደ ሃይድሮ ፓወር አርግ ገፀ ድር፣ የደቡብ አፍሪካው ጋሪየፕ ግድብ ለሀገሪቱ የኃይል አቅርቦት፣ የምግብ ዋስትና፣ የውሃ አቅርቦትና የጎርፍ መከላከል ወሳኝ ምሰሶ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል።

ጥናቶች እንደሚያሳዩት ጋሪየፕ ግድብ ለዓሣ አጥማጆች በጣም ተወዳጅ ከሆኑት ስፍራዎች አንዱ ነው። ብዙ ሰዎች ወደዚህ ግድብ የሚመጡት እንደ ካርፕ፣ ባርበል፣ ቢጫ ዓሣ እና ሙድፊሽ ያሉ ዓሳዎችን ለማጥመድ ነው። ግድቡ ለአካባቢው ማህበረሰብም በተለይም ለዓሳ አጥማጆች አስፈላጊ የምግብ እና የገቢ ምንጭ ነው። በአካባቢው ይህ ዓሳ አጥማጅነት በተለይ ሌሎች የገቢ ምንጮች በሚገደቡበት ጊዜ እንደ የደህንነት መረብ ሆኖ ያገለግላል። ጋሪየፕ ግድብ የተረጋጋና ትልቅ የውሃ አካል በመሆኑ ለአንዳንድ የዓሣ ዝርያዎች የተረጋጋ መኖሪያ ይሰጣል።

በዛምቤዚ ወንዝ ላይ የሚገኘው ‘ካቦራ ባሳ’ ግድብም የአፍሪካ ትልልቅ ግድቦች ከሚባሉት ውስጥ አንዱ ነው። ግድቡ በዛምቢያና በዚምባብዌ መካከል የጋራ ፕሮጀክት ሲሆን፣ በአፍሪካ ከሚገኙት ግዙፍ የውሃ ኃይል ማመንጫዎች አንዱ ነው። ይህ ግድብ ለሁለቱም ሀገራት ከፍተኛ መጠን ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል ያቀርባል። የ‘ካቦራ ባሳ’ ግድብ የተገነባው እ.ኤ.አ በ1950ዎቹ መጨረሻ ላይ ሲሆን፣ ከግንባታው ወዲህ ለሁለቱ ሀገራት ኢኮኖሚ እድገትና ለብዙ ማህበረሰቦች ብርሃን በመሆን ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል። ይህ ግድብ በዋናነት ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ የሚያገለግል ሲሆን፣ ለሞዛምቢክና ለጎረቤት ሀገራት የኃይል አቅርቦት ወሳኝ ነው። 2 ሺህ 70 ሜጋዋት ኃይል የሚያመነጨው የ‘ካቦራ ባሳ’ ግድብ የሞዛምቢክን ኢኮኖሚ በመደገፍና የኢንዱስትሪ ዘርፉን በማጎልበት ትልቅ ሚና ተጫውቷል።

ወደ አውሮፓ አምርተን በሩሲያ በሳያኖጎርስክ ካካሲያ በዬኒሴይ ወንዝ ላይ የሚገኘውን ‘ሳያኖ-ሹሺንስካያ’ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድብን በአጭሩ ቃኝተን ጽሑፋችንን እንቋጭ፡፡ የኃይል ማመንጫው ግንባታ እ.ኤ.አ በ1963 ተጀምሮ እ.ኤ.አ በ1978 የተጠናቀቀ ሲሆን፣ 10 ኃይል ማመንጫ ክፍሎችን ይዟል፡፡ እነዚህ ማመንጫዎች እያንዳንዳቸው 640 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም አላቸው። ‘ሳያኖ-ሹሺንስካያ’ ከሚያመነጨው ኃይል 70 በመቶው በሳይቤሪያ የሚገኙ 5 የአልሙኒየም ማቅለጫ ፋብሪካዎች ይጠቀሙታል፡፡

በመስከረም ሊሞሸር ቀጠሮ የተያዘለትና ኢትዮጵያ የገነባችው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ጨምሮ በርካታ ሀገራት የኃይል ፍላጎቷን ለማሟላትና ልማቷን ለማፋጠን ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ (GERD) ሲጠናቀቅ በአፍሪካ ትልቁ የኃይል ማመንጫ ይሆናል፡፡ ይህ ግድብ ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገት፣ ለኃይል አቅርቦትና ለቀጠናዊ ትብብር ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

# “የምንተክለው ምግባችንንም ጭምር ነው”

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ**

- **የከተማዋ የደን ሽፋን ከ6 ዓመት በፊት ከነበረበት 2 ነጥብ 8 በመቶ አሁን ወደ 22 በመቶ ደርሷል**

**በሳህሉ ብርሃኑ**






ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የዘንድሮውን የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር በግንፍሌ ወንዝ አካባቢ ተገኝተው ባስጀመሩበት ወቅት

የአየር ንብረት ለውጥ የዓለም አሁናዊ ፈተና ነው፡፡ ችግሩ እያስከተለ ያለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመከላከል፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገትን እውን ለማድረግ የደን ልማት ወሳኝ ድርሻ አለው፡፡ ይህንኑ ባገናዘበ መልኩ ኢትዮጵያ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ የአረንጓዴ ልማት መርሐ ግብርን ስታከናውን ቆይታለች፡፡

በኢትዮጵያ እንደ ሀገር የተጀመረውን የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር አዲስ አበባም በመከተል እና ልዩ ትኩረት በመስጠት ላለፉት 6 ተከታታይ ዓመታት በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ችግኞችን መትከል ችላለች፡፡ ዘንድሮም ለ7ኛ ጊዜ እያከናወነች ባለችው የችግኝ ተከላ መርሐ ግብር ተጨማሪ ውጤት የሚያስገኝ የተጠናከረ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የመዲናዋን የ2017 ዓ.ም የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሐ-ግብርን ባስጀመሩበት ወቅት እንደገለጹት፣ ላለፉት 6 ተከታታይ ዓመታት የተካሄደው የችግኝ ተከላ መርሐ-ግብር የከተማዋን የደን ሽፋን አሳድጎታል፡፡

ከንቲባ አዳነች አክለውም፣ “የአረንጓዴ አሻራው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር መሆን እንዲችል የሚያደርግ ፅኑ መሰረት የተጣለበት ነው፡፡ የምንተክለው ምግባችንንም ጭምር ነው” ብለዋል፡፡

ችግኝ መትከል የምግብ ሉዓላዊነትን የምናረጋግጥበት ነው ያሉት ከንቲባ አዳነች፣ “የምንተክለው ጥላ ብቻ አይደለም፣ ውበት ብቻ አይደለም፣ ለጫካ የሚሆኑ ዛፎች ብቻም አይደለም፤ የምንተክለው ምግባችንንም በመሆኑ የምግብ ዋስትናችንንም የምናረጋግጥበት ነው” ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በእርግጥም ከንቲባ አዳነች እንደገለፁት ችግኞችን መትከል የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እና የማይበገር የአየር ንብረት ለውጥን ለመገንባት ወሳኝ ነው፡፡ የዓለም አግሮፎረስተሪን ማዕከል (ICRAF) መረጃም ይህንኑ ነው የሚያመላክተው፤ በአፍሪካ ውስጥ በርካታ ፕሮጀክቶችን እና ጥናቶችን የሚያካሂደው የአግሮፎረስትሪ ምርምር ማዕከል የዛፍ ተከላ በምግብ ዋስትና ላይ ያለውን ተፅዕኖ በተመለከተ ሰፊ ስራዎችን ያከናውናል። ዛፎች ካርቦን ዳይኦክሳይድን በመምጠጥ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ ይረዳሉ። የአየር ንብረት ለውጥ ደግሞ በግብርና ምርት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ስለሚያሳድር፣ የዛፍ ተከላ ቀጥተኛ ያልሆነ የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ፋይዳ አለው።

የዓለም አግሮፎረስተሪን ማዕከል (ICRAF) ተመራማሪ የሆኑት ፈርጉስ ሲንክሌርም (ዶ/ር) ችግኝ መትከል ለምግብ ዋስትና ወሳኝ እንደሆነ ይስማማሉ። ምክንያታቸውን ሲያስቀምጡም፣ የሰብል ምርታማነትን ከማሳደግ ባሻገር፣ የአመጋገብ ጥራትን ያሻሽላል፣ የገቢ ምንጭ ይፈጥራል፣ የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋም አቅምን ይጨምራል። ይህ ደግሞ ዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት ቁልፍ ሚና ይጫወታል።

የቀድሞው የዓለም አግሮፎረስተሪ ዋና ዳይሬክተር ቶኒ ሲሞንስ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ ዛፎች የአፈር መሸርሸርን ይከላከላሉ፤ የአፈርን ለምነት ይጨምራሉ፤ የውሃ አያያዝን ያሻሽላሉ። ይህም የሰብል ምርትን ከፍ ያደርጋል፤ በተለይ ደግሞ የውሃ እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች ዛፎች የከርሰ ምድር ውሃን በመሙላት እና የአፈርን እርጥበት በመጠበቅ የሰብል እድገትን ይደግፋሉ።

የፍራፍሬ ዛፎችን፣ ለውዝ የሚያፈሩ ዛፎችን እና ሌሎች የሚበሉ የዛፍ ምርቶችን መትከል የምግብ ምንጮችን በማብዛት የአመጋገብ ዋስትናን ያረጋግጣል። ይህ በተለይ በአንድ የሰብል አይነት ላይ ጥገኛ የሆኑ ማህበረሰቦች የምግብ እጥረትን እንዲቋቋሙ ይረዳል ይላሉ ቶኒ ሲሞንስ (ዶ/ር)።

አክለውም ብዙ ዛፎች እንደ ፍራፍሬ፣ ቅጠላማ አትክልቶች፣ ለውዝ እና የመሳሰሉ ጠቃሚ ንጥረ ነገሮችን የያዙ ምርቶችን ያቀርባሉ። እነዚህም የአመጋገብ ጥራትን በማሻሻል የምግብ እጥረትን ለመቀነስ ይረዳሉ። በተለይም በገጠር አካባቢዎች ለህጻናት እና ለሴቶች የአመጋገብ ደህንነት ወሳኝ ስለመሆናቸውም ያብራራሉ።

ከንቲባ ወይዘሮ አዳች አቤቤም የአንድነትና የጋራ መንፈስ እየታየበት ያለውና ማህበረሰቡ በጋራ ተስማምቶ ከሰራቸው ትላልቅ ሀገራዊ አጀንዳዎች ውስጥ አንዱ የሆነው አረንጓዴ አሻራ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን እያስገኘ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች፣ የአንድ ጀንበር የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብርን በግንፍሌ ቀበና ወንዝ ዳርቻ ባስጀመሩበት ወቅት እንደተናገሩት፣ መላው ኢትዮጵያውያን ባለፉት 6 ዓመታት በተተከሉ ችግኞች ታላቅ ገድል ሰርቷል፡፡

> **ችግኝ መትከል የሰብል ምርታማነትን ከማሳደግ ባሻገር፣ የአመጋገብ ጥራትን ያሻሽላል፤ የገቢ ምንጭ ይፈጥራል፤ የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋም አቅምን ይጨምራል**

ከንቲባዋ አክለውም፣ “ችግኝ በመትከላችን በብዙ ተጠቅመናል፡፡ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብርን ጥብቅ በሆነ መንገድ ያለ ፆታ፣ ዕድሜ፣ ብሔር፣ ኃይማኖት እና ፖለቲካ አመለካከት ልዩነት የተተከለው ትልቅ አሻራ ከትውልድ ትውልድ የሚሸጋገር ነው፡፡ ” ብለዋል፡፡

በከንቲባ ወይዘሮ አዳነች ማብራሪያ መሠረት፣ በአዲስ አበባ በአንድ ጀንበር መርሐ ግብሩ ከ271 ሳይቶች በ1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት ላይ ችግኞች ተተክለዋል፡፡ በክረምት መርሐ ግብር 4 ነጥብ 2 ሚሊዮን ችግኞች ይተከላሉ፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃ ዓመቱን ሙሉ ችግኞች እንደሚተከሉና በተጠናቀቀው በጀት ዓመትም 5 ሚሊዮን ችግኞች ስለመተከላቸው ተመላክቷል፡፡ ከ6 ዓመት በፊት የመዲናዋ የአረንጓዴ ሽፋን ከ2 ነጥብ 8 በመቶ ያነሰ ነበር፡፡ አሁን ላይ 22 በመቶ ደርሷል፡፡ በዓለም አቀፍ መመዘኛ መስፈርት መሰረት ደግሞ ከተሞች 30 በመቶ መድረስ ይገባቸዋል። ይህንን ግብ በ2018 ዓ.ም ለማሳካት እየተሰራ ነው፡፡

አዲስ አበባን በአረንጓዴ ልማት ለማበልፀግ፣ ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ውብ፣ ከአፍሪካ እህት ከተሞች መካከል ቀዳሚና ተመራጭ ለማድረግ ጥረቶች እየተደረጉ ነው፡፡ ይህን ግብ ለማሳካት እንዲቻል የአረንጓዴ ልማት ስራ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ በመርሐ ግብሩ በ2011 ዓ.ም በመዲናዋ 6 ሚሊዮን 84 ሺህ 372 ችግኞችን መትከል፣ በ2012 ዓ.ም 8 ሚሊዮን 513 ሺህ 531 ችግኞች፣ በ2013 ዓ.ም 11 ሚሊዮን 441 ሺህ 961 ችግኞች፣ በ2014 ዓ.ም 14 ሚሊዮን 795 ሺህ 595 ችግኞች፣ በ2015 ዓ.ም ደግሞ 17 ሚሊዮን 445 ሺህ 385 ችግኞች፣ በ2016 ዓ.ም ደግሞ ከ27 ነጥብ 7 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን መትከል እንደተቻለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ መረጃ ያመላክታል።

በእነዚህ የአረንጓዴ አሻራ የችግኝ ተከላ መርሐ ግብሮች በሚሊዮን የሚቆጠሩ የመዲናዋ ነዋሪዎች ከሊቅ እስከ ደቂቅ በሚባል ደረጃ የተሳተፉ ሲሆን፣ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የኃይማኖት ተቋማት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሌሎችም በጋራ ስለ መዲናዋ ገጽታ ግንባታ እና ለጋራ ጥቅም በጋራ መቆምን ለዓለም ያሳዩበት አኩሪ ተግባር ሆኗል፡፡

የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብር አዲስ አበባ ለጀመረችው የዘመናዊ ከተማ ግንባታ ሂደት አንዱ ገጽታ ሆኖ እየተተገበረም ይገኛል፡፡ ይህ ተግባር ከተማዋን አረንጓዴ፣ ውብና ለኑሮ ምቹ እንድትሆን እየተሰራ ከሚገኘው የኮሪደር ልማት ስራ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው።

በመሆኑም በየኮሪደሩ በተዘጋጁ የአረንጓዴ እና የመዝናኛ ስፍራዎች ላይ ለመዲናዋ ውበት እና ድምቀት የሚሰጡ የተለያዩ የዕፅዋት አይነቶች በመተከል ላይ ናቸው፡፡ በመዲናዋ የሚገኙ በርካታ የተራቆቱ አካባቢዎችን ማልማት የተቻለ ሲሆን፣ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም፣ በስራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተሰፋ ሰጪ ውጤቶች ተገኝተውበታል፡፡

በተለይ በመዲናዋ እየተከናወነ በሚገኘው የኮሪደር ልማት እየተተከሉ የሚገኙ ችግኞች የመዲናዋን ውበትና ገጽታ ከማላበስ ባለፈ ጤናማ፣ በአካል ብቃት የዳበረ እና በመንፈስ የተረጋጋ ትውልድ ለመፍጠር በሚደረገው ጥረት የላቀ ሚና እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡

# የአንድ ጀንበሩን እጆች የሚፈልገው ምዕራፍ

**በተከላው መርሃ ግብር እንደተሳተፍነው ሁሉ በእንክካቤውም ተግተን እንቀጥላለን ሲሉ በዘንድሮው የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር በግንፍሌ ወንዝ አካባቢ የተሳተፉ የከተማዋ ነዋሪዎች ተናገሩ**

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**

ላለፉት 6 ዓመታት ኢትዮጵያውያን ተባብረው ችግኝ ሲተክሉ ከርመዋል። ዘንድሮም የክረምቱ ወቅት ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ለ7ኛ ዙር በመርሃ ግብሩ እየተሳተፉ ይገኛሉ። በመደበኛነት ከሚካሄደው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ባሻገር በየዓመቱ በሚከናወነው የአንድ ጀንበር መርሃ ግብርም በነቂስ ወጥተው ይሳተፋሉ። ዘንድሮም በመላው ኢትዮጵያ 29 ነጥብ 7 ሚሊዮን ሰዎች በመርሃ ግብሩ ተሳትፈዋል።

የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብሩ በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃም በከፍተኛ የህዝብ ተሳትፎ ተከናውኗል። በግንፍሌ ወንዝ ዳርቻ ተገኝተን የችግኝ ተከላውን ሂደት ቃኝተናል። ለመሆኑ ለተከላው በነቂስ እንደተወጣው ሁሉ በእንክብካቤውም ላለመጉደል ምን ማድረግ ይገባል? ስንል በስፍራው ለተገኙ የመርሃ ግብሩ ተሳታፊዎች ላቀረብነው ጥያቄ ተከታዩን ምላሽ ሰጥተውናል።

በግንፍሌ ወንዝ አካባቢ በተካሄደው የዘንድሮው የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር በነቂስ ወጥተው የተሳተፉ የከተማዋ ነዋሪዎች በተከላ መርሃ ግብሩ በትብብር እንደተሳተፍነው ሁሉ በእንክካቤውም ተግተን እንቀጥላለን ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የቀበናና አካባቢው ፖሊስ ጣቢያ የወንጀል መከላከል ማስተባበሪያ ኃላፊ ምክትል ኢንስፔክተር ፈይሳ ዘውዴ በቀበና ወንዝ አካባቢ በተዘጋጀው የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ላይ ከሌሎች የፖሊስ አባላትና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ችግኝ ሲተክሉ አግኝተን አነጋግረናቸዋል፡፡ በቆይታችን፣ “ፖሊስ የአካባቢውን ሰላምና ፀጥታ ከማስጠበቅ ጎን ለጎን እንደዚህ አይነት ለትውልድ ትልቅ አሻራ በሚጣልባቸው ሀገራዊ ጉዳዮች ላይም ግንባር ቀደም ተሳታፊ ነው” ብለውናል፡፡

ምክትል ኢንስፔክተር ፈይሳ እና ሌሎች ባልደረቦቻቸው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ከተጀመረ ወዲህ በተከናወኑ የችግኝ ተከላ መርሃ ግብሮች ተሳታፊ እንደነበሩ አስታውሰው፣ ችግኝ መትከል ብቻ ሳይሆን የተተከሉትን በመጠበቅና በመንከባከብ ረገድም የጎላ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡

እንደምክትል ኢንስፔክተሩ ገለፃ፣ ችግኞችን መንከባከብና መጠበቅ በጊዜ የሚወሰን አይደለም፡፡ ችግኝ መትከል ልክ ልጅ ወልዶ እንደማሳደግ ነው፡፡ አንድ ልጅ ተወልዶ ለማደግ የወላጆቹን እንክብካቤና ድጋፍ እንደሚፈልግ ሁሉ ችግኞችም ከተተከሉበት ጊዜ ጀምሮ ጥበቃና እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

ችግኞች የተተከሉበት አካባቢን በመከለል የቤት እንስሳት ጉዳት



ፎቶ- ከገፀ ድር

በግንፍሌ ወንዝ ዳር በተካሄደው የዘንድሮው የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር የተሳተፉ የህብረተሰብ ክፍሎች

እንዳያደርሱ መጠበቅ ብሎም በበጋ ወራት እንዳይደርቁ ውሃ ማጠጣት እንደሚገባ አስታውሰው፣ የፖሊስ አባላቱም የተከሏቸውን ችግኞች ልክ እንደመደበኛ ስራቸው በመመልከት አስፈላጊውን ክትትልና እንክብካቤ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል፡፡

ወይዘሮ አሰገደች አካሉ በግንፍሌ ወንዝ ዳር በተካሄደው የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ከተሳተፉ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ሲሆኑ፣ በወቅቱ በሰጡን አስተያየት ችግኝ መትከል የተተኪውን ትውልድ ህይወት ማስቀጠል እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ዛሬ በተከሉት ችግኝ ነገ ልጆቻቸው ከፀሐይ የሚጠለሉበት፣ ንፁህ አየር የሚተነፍሱበት ከመሆን አልፎ ፅዱ፣ አረንጓዴና ያማረ አካባቢን ለትውልድ የማስረከብ ኃላፊነትን የሚወጡበት ጥሩ መሰረት እያኖሩ እንደሆነ ገልፀው፣ ችግኝን ተንከባክቦ ማሳደግ ለሰፈራቸው ብሎም ለከተማዋ ውበትና ልማት ትልቅ አስተዋፅኦ እዳለው ተናግረዋል፡፡

ወይዘሮ አያንቱ ገለታ በዘንድሮው የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር በግንፍሌ ወንዝ ዳርቻ ችግኝ ሲተክሉ አግኝተን ባነጋገርናቸው ወቅት፣ አንድ ሆነን ችግኞችን የምንተክለው በመሬት መራቆት ምክንያት ከሚደርስብን የጎርፍ አደጋ ለመዳን ብቻ ሳይሆን ምግብም ለማግኘት ነው ብለዋል፡፡

“ችግኝ የደን ሽፋናችንን ያሳድጋል፤ የአፈር ለምነትን በመጠበቅ ምርታማነታችንን ለመጨመርም ስለሚያግዝ በተከላው ላይ በትኩረት እየተሳተፍኩ ነው፡፡ እንክብካቤው ላይም እበረታለሁ" ሲሉም ተናግረዋል፡፡

የአራዳ ክፍለ ከተማ የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ፅህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ተካ ደመቀ ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደገለፁት፣ በክፍለ ከተማው በአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር አስራ ሰባት አካባቢዎች ተከናውኗል፡፡

በችግኝ ተከላው ከ21 ሺህ 690 የሚበልጡ የክፍለ ከተማው የህብረተሰብ ክፍሎች የተሳተፉ ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል 12 ሺህ 185 ሴቶችና 9 ሺህ 512 ወንዶች መሆናቸውን ነው ያስታወቁት፡፡ በእለቱ እንደ ክፍለ ከተማ 16 ሺህ 355 ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ፣ 23 ሺህ 59 ችግኞች ተተክለዋል፡፡

ከተተከሉ ችግኞች 14 ሺህ 604 የጥላ፣ 2 ሺህ 772 የውበት አበባዎችና 5 ሺህ 683 የፍራፍሬ መሆናቸውን የጠቆሙት ኃላፊው፣ በመርሃ ግብሩ ከፍተኛ አመራሮች እና በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች የተሳተፉ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

ህብረተሰቡ ስለ ችግኝ ተከላና እንክብካቤ ያለው ተሳትፎና ግንዛቤ እለት ከእለት እየተሻሻለና እየጎለበተ መጥቷል ብለው፣ በመርሃ ግብሩ ህብረተሰቡ በጊዜ ወጥቶ መሳተፉን ገልፀዋል፡፡ ችግኝ መትከል ብቻ ሳይሆን የተተከለውን ተንከባክቦ በማፅደቅ ረገድም ጠንካራ አመለካከት እና ግንዛቤ ያለው ማህበረሰብ መፈጠሩን ጠቁመው፣ ለዚህም ባለፈው ተመሳሳይ ወቅት የተተከሉ ችግኞች የፅድቀት መጠን 89 በመቶ መሆኑን እንደማሳያ አንስተዋል፡

በየወረዳው ያሉ ነዋሪዎች ከሚያከናውኑት የእንክብካቤ ስራ በተጨማሪ የከተማ አስተዳደሩ የመደባቸው በ17 ማህበር የተደራጁ 170 የሚጠጉ የስራ እድል የተፈጠረላቸው ወገኖች በቋሚነት የእንክብካቤውን ስራ እንደሚሰሩ ጠቁመው፣ ይህ ዘንድሮ የሚተከሉ ችግኞች ከቀድሞው በበለጠ የመፅደቅ እድል እንዲኖራቸው ያስችላልም ብለዋል፡፡

በዘንድሮው የአንድ ጀንበር ችግኝ ተከላ መርሃ ግብር በአራዳ ክፍለ ከተማ ተሳትፎ ካደረጉ የከተማና የፌዴራል እንዲሁም የግል ተቋማት መካከልም ከንቲባ ፅህፈት ቤት፣ የኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር እና አቤት ሆስፒታል ተጠቃሾች ናቸው። የችግኝ ተከላውም በግንፍሌና ቀበና ወንዝ ዳርቻ፣ ጃንሜዳ፣ በክፍለ ከተማው ወረዳ 2 የሙስሊም መቃብር፣ በወረዳ 1 በሚገኘው ጆን.ኤፍ.ኬኔዲ ትምህርት ቤት እንዲሁም ወረዳ 1 የጎርደሜ ወንዝ ዳርቻን ጨምሮ በ17 የተለያዩ አካባቢዎች ነው የተከናወነው፡፡

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 አስተዳደር የውበትና አረንጓዴ ልማት ፅህፈት ቤት ባለሙያ አቶ ባየው ብርሃኔ ችግኞችን የመትከል ፋይዳ ቀላል አለመሆኑን ጠቅሰው፣ ከዛፍ ምርቶቻቸው ለመጠቀም፤ የተጎዱ መሬቶች መልሰው እንዲለሙ ለማድረግ፤ አካባቢን ለማስዋብ፣ ለአፈርና ውሃ ጥበቃ፣ የተፈጥሮን ሚዛን ለመጠበቅ፣ በካይ ነገሮችን ለመቀነስ፣ የአየር ጥራት ለማሻሻል በጥቅሉ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ከፍተኛ አስተዋፆኦ እንዳላቸው አብራርተዋል፡፡

ባለሙያው የችግኝ ተከላ መርሃ ግብሮች ውጤታማ እንዲሆኑ በሙያቸው ከማገዝ አልፈው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር እንደሀገር ተግባራዊ መደረግ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በግላቸውም ችግኝ በመትከል የግል ድርሻቸውን ሲወጡ መቆየታቸውን ገልፀው፣ ችግኞችን ከመትከል ባለፈ የፅድቀት መጠናቸው ከፍ እንዲል ጠንካራ ክትትልና ድጋፍ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል፡፡

እንደ ባለሙያው ገለፃ፣ የተተከሉ ችግኞች እንዲፀድቁ በተለይ በበጋ ወራት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችንና ባለሃብቶችን በማስተባበር ውሃ በማጠጣትና በመኮትኮት እንክብካቤ ሲደረግ ቆይቷል፡፡

በግንፍሌ እና ቀበና ወንዝ አካባቢ ከሁለት ዓመት በፊት የተተከሉ ችግኞች የፅድቀት መጠን ለዚህ ማሳያ ናቸው ያሉት ባለሙያው፣ የተተከሉት ችግኞች ሙሉ በሙሉ በመፅደቃቸው ድካም ለተጫጫነው ማረፊያ ለአካባቢውም ልዩ ውበትን አጎናፅፈውታል፡፡

ዘንድሮም ባሉት ክፍት ቦታዎች እንደ አቮካዶ፣ ማንጎ፣ ዘይቱን እና ፓፓያ ያሉ ለምግብነት የሚውሉ የፍራፍሬ ችግኞች የተተከሉ ሲሆን፣ ችግኝ ተክሎ መተው ብቻ ሳይሆን ተከታታይነት ያለው የእንክብካቤ ስራ በቀጣይ እንደሚሰራም ነው ያረጋገጡት፡፡

የተተከሉ ችግኞች እንዲፀድቁ ከጉድጓድ ቁፋሮ ጀምሮ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ያሻል ያሉት ባለሙያው፣ በተለይ በንቅናቄ በሚተከልበት ወቅት ችግሮች እንደሚያጋጥሙ ነው፡፡ በተደጋጋሚ ከሚያጋጥሙ ችግሮች መካከል ከነ ፕላስቲኩ መትከል፣ በደንብ አፈር ሳያለብሱ መተው፣ እንዲሁም ችግኞቹን በተዘጋጀላቸው ጉድጓድ ከመትከል ይልቅ ሜዳ ላይ ጥሎ መሄድ የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

## የ4 ኪሎ ... ከገጽ 1 የዞረ

እና አበባዎች ለከተማዋ አዲስ ገጽታ እና ውበትን ሰጥተዋታል። ከመሬት በታች የተሰሩ የእግረኛ መንገዶች፣ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች፣ የንግድ ማዕከላትና ሌሎች ፕሮጀክቶች ደግሞ መዲናዋን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንድትሆን ስንቅ የሚሆኗት መገለጫዎቿ ናቸው፡፡ ለአብነት በትናንትናው እለት የተመረቁት 4 ኪሎ ፕላዛ፣ 4 ኪሎ የገበያ ማዕከል እና መኪና ማቆሚያ ለመዲናዋ ትልቅ የኢኮኖሚ አቅም ለመፍጠር አጋዥ ከመሆናቸውም ባሻገር ተጨማሪ ውበትንና ምቹነትን የሚሰጡ፣ አዲስ ገጽታንም የሚያላብሱ ናቸው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የፕሮጀክቶቹን ስራ መጀመር አስመልክተው በማህበራዊ የትስስር ገጻቸው ላይ ባሰፈሩት ጹሑፍ፣ አዲስ አበባን ከቀድሞ ታሪኮቿ ጋር እያጣጣምን ዘመናዊ ከተማ እያደረግናት እንገኛለን ብለዋል።

ከንቲባዋ የሀገራችን ብሎም የከተማችን አበይት ታሪካዊ ስፍራ፣ የድል ሀውልታችን መገኛ፣ የተለያዩ ጋዜጦችና መፅሔቶችን ያነበብንበትን፣ እውቀት የቀሰምንበትን፣ ስራ ፍለጋ ማስታወቂያ ለማንበብ የተመላለስንበትን የ 4 ኪሎ አደባባይ አካባቢን መልሰን ገንብተናል። የያዘውን ግዙፍ ታሪክ የሚመጥኑ፣ ትላንታችንን ከዛሬ እና ከነገአችን ጋር የሚያገናኙ፣ ከፍተኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ፣ ዘመናዊ የከተማ ዲዛይን እና እሴት ያላቸው ውብ የ4 ኪሎ የገበያ ማዕከልን፣ መኪና ማቆሚያን እና 4 ኪሎ ፕላዛን ገንብተን ለአገልግሎት ክፍት አድርገናል ሲሉም አክለዋል።

ፕሮጀክቶቹ ከመሬት በታች የተገነቡ እጅግ ዘመናዊ 102 የስጦታ እና የአልባሳት መደብሮች፣ ካፌዎች፣ ካፍቴሪያዎች፣ ማንበቢያ ስፍራዎች፣ ሱፐር ማርኬቶች፣ ከ100 በላይ ተሽከርካሪዎችን በአንድ ጊዜ የሚያስተናግድ የመኪና ማቆሚያ እና በአንድ ጊዜ እስከ 5 ሺህ ሰዎችን መሰብሰብ የሚያስችል የፕላዛ፣ የአንፊ ቴአትርና የተለያዩ የጥበብ ስራዎችን ማቅረቢያ ስፍራዎችን የያዙ፣ የሲቪል ተሳትፎን፣ የባህል ዕድገትን፣ የእግር ጉዞን የሚያበረታቱ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዙ፣ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በተለይም አቅመ ደካሞችና አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረጉ ናቸው።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንደገለጹት፣ ፕሮጀክቶቹ ከወዲሁ ከ500 በላይ ለሚሆኑ ወጣቶችና ሴቶች የስራ ዕድል የፈጠሩ ሲሆን፣ የቱሪዝም ፍሰቱን በመጨመር ለዘርፉ ዕድገት የራሱ ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል፡፡

በእርግጥም አዲሱ 4 ኪሎ ፕላዛ፣ 4 ኪሎ የገበያ ማዕከል እና መኪና ማቆሚያ የአዲስ አበባ የትናንት ታሪክ ከዘመናዊነት ጋር የተጣጣሙና ለወደፊቱ ትውልድም ትልቅ ትርጉምና ጥቅም እንዲሰጡ ተደርገው የተሰሩ ናቸው፡፡ ይህ አይነቱ ስራ ቀጣዩ ትውልድ ከታሪኩ ጋር ትስስር እንዲኖረው፣ ታሪኩን እያወቀና እየኮራበት ከዘመናዊው ዓለም ጋር እንዲራመድ ይረዳል። የከተማዋ ለውጥ የሚያሳየው፣ ያለፈ ታሪክን ሳይዘነጉ



ፎቶ- ከገፀ ድር

የተመረቁት የ4 ኪሎ ፕሮጀክቶች ከፊል ገፅታ

> “የሀገራችን ብሎም የከተማችን አበይት ታሪካዊ ስፍራ፣ የድል ሀውልታችን መገኛ፣ የተለያዩ ጋዜጦችና መፅሔቶችን ያነበብንበትን፣ እውቀት የቀሰምንበትን፣ ስራ ፍለጋ ማስታወቂያ ለማንበብ የተመላለስንበትን የ 4 ኪሎ አደባባይ አካባቢን መልሰን ገንብተናል”

እንዴት ወደፊት መሄድ እንደሚቻል ነው። ይህም የኢትዮጵያ መዲና፣ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ እና የዓለም የዲፕሎማሲ ማዕከል የሆነችው አዲስ አበባን ከትልልቅ ከተሞች ጋር ተወዳዳሪና ምቹ የሚያደርጋት ነው፡፡

ሞላ አለማየሁ (ዶ/ር) በኢትዮጵያ የኢኮኖሚክ አሶሴሽን ከፍተኛ ተመራማሪ ናቸው፡፡ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት፣ “አንዲት ከተማ ምቹ ለመባል መሰረታዊ የሆኑ አገልግሎቶችን ማሟላት አለባት፡፡ እንዲሁም ከመሰረታዊ ፍላጎት በተጨማሪ ነዋሪዎች የተሻለ የሚዝናኑበትን መሰረተ ልማት ማሟላት ይኖርባታል፡፡ በአጠቃላይ ዜጎች የሚፈልጉትን መሰረተ ልማት በበቂ ሁኔታና በጥራት ማቅረብ የምትችል ከተማ ለኑሮ ምቹ ነች ተብሎ ይታሰባል” ይላሉ፡፡

ከዚህ አንጻር በአዲስ አበባ የተጀመሩ ስራዎች ተስፋ ሰጪ እንደሆኑ አንስተዋል። እነዚህን ልማቶች በማስፋትና አቅምን በማሳደግ መዲናዋን ህዝቡ በሚፈልገው ልክ ምቹ ከማድረግ አንጻር ከዚህም በላይ መስራት እንደሚያስፈልግ አክለዋል፡፡

በትናንትናው እለት በከንቲባ አዳነች አቤቤ ተመርቆ ለአገልግሎት ክፍት የሆነው የ4 ኪሎ ፕላዛ፣ 4 ኪሎ የገበያ ማዕከል እና መኪና ማቆሚያ በካናዳዋ ቶሮንቶ ከተማ ከተሰራው “Path Underground Shopping Mall”፣ በደቡብ ኮሪያዋ ጄጁ ከተማ ከሚገኘው “Jeju Jungang Underground Shopping CenterÈ፣ በኦስትሪያዋ ሳልዝበርግ ከሚገኘው Çthe Mönchsberg garageÈ እንዲሁም በጃፓኖቹ ቶኪዮ እና ኦሳካ ከመሬት በታች ከሚገኙት ፕሮጀክቶች ጋር የሚወዳደሩ ናቸው፡፡

የዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሃብት ምሁሩ ፋሲል ጣሰው ፕሮጀክቶቹን አስመልክተው በቅርቡ ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል በሰጡት አስተያየት፣ እንደ ቻይና እና ጃፓን ባሉ ሀገራት ረጅም ኪሎ ሜትሮችን የሚጓዙ፣ ከተሞችን እርስ በእርስ የሚያገናኙ የባቡር መስመሮች በመሬት ውስጥ መዘርጋታቸው የደረሱበትን ደረጃ ያመላክታል፡፡ ይህ ልምድ በእኛም አገር፤

ወደ ገጽ 16 ዞሯል

# የመዲናዋ የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ስራ ምን ውጤት እያስገኘ ነው?



ፎቶ- ከፋይል

በአዲስ አበባ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ከተሰሩ ስራዎች ጥቂቶቹ

በስንታየሁ ምትኩ

ለሰው ልጅ በሙሉ ሰላም፣ እድገትና ብልፅግናን ለማምጣት ነበር የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባል ሀገራት በፈረንጆቹ አቆጣጠር 2030 የሚሳኩ ዘላቂ የልማት ግቦችን ይፋ ያደረጉት። ድህነትና ረሃብን ማጥፋት፣ የጤና፣ የትምህርት ጥራትን ማሳደግ፣ የፆታ እኩልነትን፣ የአየር ንብረት ለውጥ መከላከልን ጨምሮ 17 ግቦችን ያካተቱ እንደሆኑ የተባበሩት መንግስታት በገፀ-ድሩ ያወጣው መረጃ ያመለክታል፡፡

ዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት የምግብ ዋስትናና ጤናማ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ ምግብ ለሁሉም ማዳረስ አይነተኛ መፍትሔ ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን ለዚህም በግብርና ምርታማነት እና የምግብ ስርዓት ላይ ጉልህ የሆነ ለውጥ ማምጣት እንደሚገባ የዓለም የምግብና እርሻ ድርጅት "Sustainable food systems Concept and framework" በሚል ርዕስ በ2018 ያወጣው ሰነድ ያመለክታል፡፡

በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2021 በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አዘጋጅነት ከምግብ ስርዓት ጋር የሚያያዙትን የዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት የመጀመሪያው የምግብ ስርዓት ጉባኤ ተካሄደ፡፡ ጉባኤው የዓለምን የምግብ ስርዓት የበለጠ አካታች፣ ጠንካራና ዘላቂ ለማድረግ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ እርምጃዎችን ለመውሰድ ታልሞ የተካሄደ እንደነበር በገፀ-ድሩ የወጣው መረጃ ያመለክታል፡፡

ከአራት ዓመት በኋላ ሁለተኛው የተባበሩት መንግስታት የምግብ ስርዓት ጉባኤ የተለያዩ ሀገራት መሪዎች፣ ሚኒስትሮች፣ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች በተገኙበት ከሐምሌ 20 እስከ ሐምሌ 22 ቀን 2017 ዓ.ም በአዲስ አበባ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን አዳራሽ ተካሂዷል። ጉባኤውን ኢትዮጵያ፣ ጣሊያን እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በመተባበር ያዘጋጁት ነው፡፡

በጉባኤው መክፈቻ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፤ እንደተናገሩት፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የምግብ ስርዓት ከአየር ንብረት ለውጥ፣ ከግጭት፣ ከገቢ አለመመጣጠን፣ ከኢኮኖሚ አለመረጋጋት ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ጫና ውስጥ ወድቋል፡፡ በተመሳሳይ የልማት ድጋፍ እየቀነሰና የባለብዙ ወገን ትብብርም እየተቀዛቀዘ መጥቷል፡፡ እነዚህ ፈተናዎች ምርታማነትን፣ አቅርቦትን፣ የዜጎችን ሰብዓዊ ክብርና የሀገራትን መረጋጋት ፈተና ውስጥ እየጣሉ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የምግብ ስርዓት ሽግግርን ማምጣት የሰው ልጅ ክብር ጋር የሚያያዝ ጉዳይ አድርጋ በትኩረት እየሰራች ትገኛለች፡፡ በምግብ ራስን ለመቻልም በሀገር ውስጥ ምርታማነትን በማሳደግ፣ ከውጭ የሚገቡ ምርቶች ላይ ያለውን ጥገኝነት በመቀነስ፣ ህዝብንና ነገን ታሳቢ ያደረገ የማይበገር ስርዓት ለመገንባት እየተንቀሳቀሰች እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) እንደገለፁት፣ ኢትዮጵያ በመስኖ ስንዴን በማልማት ከውጭ የሚገባ የስንዴን ምርት በማስቀረት በምግብ ራስን መቻልን እያረጋገጠች ትገኛለች፡፡ በሌማት ትሩፋት ንቅናቄም በዶሮ፣ በእንስሳትና የዓሳ እርባታ እንዲሁም ግብርናን በማሳደግ የተመጣጠነ ምግብ ለሁሉም በማዳረስ ውጤት ማምጣት ተችሏል፡፡

ሌላኛዋ ጉባኤውን ከኢትዮጵያ ጋር በመተባበር ያዘጋጀችው ሀገር ጣሊያን ስትሆን፣ የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ጆርጂያ ሜሎኒ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የምግብ ዋስትና አለመረጋገጥ 10 በመቶ ለሚሆነው የዓለም ህዝብ በተለይ በአፍሪካ ትልቅ ፈተና ሆኗል፡፡ ጣሊያን በአፍሪካ ምርታማነት እንዲያድግና ጠንካራ የምግብ ስርዓት እንዲገነባ ድጋፍ እንደምታደርግ ተናግረዋል፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ በበይነ መረብ ባስተላለፉት መልዕክትም፤ ከመጀመሪያው የምግብ ስርዓት ጉባኤ በኋላ የምግብ ስርዓት ሽግግርን ለማምጣት በተደረገ ጥረት ውጤት መገኘቱን ተናግረዋል፡፡ ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑ ሀገራት የምግብ ስርዓት ሽግግርን ከብሔራዊ የልማት እቅዳቸው ጋር አዋህደው እየሰሩ ነው፡፡ ከ100 በላይ ሀገራት የምግብ ስትራቴጂን የአየር ንብረት ለውጥን መከላከል እና የብዝሃ ህይወት ጥበቃ ስራ ጋር በማጣመር እየሰሩ እንደሆነ አንስተዋል፡፡

ኢትዮጵያ የስንዴ ምርታማነትን በማሳደግና የአየር ንብረት ለውጥ መከላከል ጋር የተጣጣመ ፖሊሲ በመተግበር ከውጭ የሚገባውን ምርት መቀነስ እንዲሁም ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር ችላለች፡፡ የዜጎችን የስርዓተ ምግብ ጥያቄ ለመመለስ መንግስት ብቻ ሳይሆን የግሉ ዘርፍ በፈጠራ፣ ሎጂስቲክስን በማሳለጥና ፋይናንስ በማቅረብ ቁልፍ ሚና መጫወት እንደሚጠበቅበትም አንስተዋል፡፡

ከምግብ ስርዓት ጉባኤው መድረክ ባሻገርም የጉባኤው ተሳታፊዎች በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን በአካል ተመልክተዋል፡፡ የጉባኤው ተሳታፊ የሆኑት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ምክትል ዋና ፀሀፊ አሚና መሀመድ፣ "ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት የምግብ ስርዓትን በማሻሻል ብቻ ሳይሆን በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስክ እድገት እያሳየች ነው፡፡ በየጊዜው ወደ አዲስ አበባ ስንመጣ ትልቅ ለውጥ ነው የምናየው።" ብለዋል፡፡ የተመጣጠነ ስርዓተ ምግብን ተደራሽ ከማድረግ አኳያም በትምህርት ቤቶች የሚከናወነው ምገባ ህፃናት ትምህርታቸው ላይ እንዲያተኩሩ ከማድረግ ባሻገር የወላጆችን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግር በማቃለል ጉልህ ፋይዳ እንዳለው መመልከታቸውን ተናግረዋል፡፡

## መዲናዋ ምን እየሰራች ነው?

ከተሞች የምግብ እጥረትን ለመፍታት እንደ ትልቅ መፍትሔ እየወሰዷቸው ከሚገኙ እርምጃዎች መካከል የከተማ ግብርና አንዱ ነው። በከተማ ግብርና ነዋሪዎችን በማሳተፍ የምግብ ፍጆታቸውን መሸፈን እንዲችሉ ከማብቃት ባለፈ ለበርካታ ዜጎች ገቢ ማስገኘትና የስራ ዕድል መፍጠር ችለዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዓለም ዙሪያ በአብነት የሚጠቀሱ ከተሞች በርካታ ናቸው፡፡ ለምሳሌ:- የካሪቢያን ሀገሯ ኩባ፣ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1990ዎቹ ካጋጠማት የኢኮኖሚ ቀውስና የምግብ እጥረት ለመውጣት የቻለችው የከተማ ግብርናን በመተግበር ነው፡፡ በዋና ከተማዋ ሀቫና ከ60 እስከ 90 በመቶ ያህሉ ትኩስ የግብርና ምርት ከከተማና ከከተማ ዙሪያ እንደሚገኝ "Cuban Urban Agriculture as a Strategy for Food Sovereignty" በሚል ርዕስ መንዝሊ ሪቪው መጽሔት በገፀ ድሩ ያወጣው መረጃ ያሳያል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማም የሚያስፈልገው የምግብ ፍጆታ የሚሸፈነው በዋናነት ከተለያዩ ሀገሪቱ አካባቢዎች ምርቶችን በማስገባት ሲሆን፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ለከተማ ግብርና ዘርፍ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል፡፡

በተለይ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ የከተማ ግብርና ዘርፍ ራሱን ችሎ እንዲደራጅ በማድረግ በጓሮ አትክልት ልማት፣ በእንስሳት ልማት ዘርፍ የእንቁላል፣ የዶሮ ስጋ፣ የበሬና የፍየል ስጋ እንዲሁም የማርና ዓሳ ምርቶች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራባቸው እንደሚገኝ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነርና የኤክስቴንሽን ዘርፍ ኃላፊ አቶ መለሰ አሸንቦ በሐምሌ ወር 2017 ዓ.ም ለዝግጅት ክፍላችን የሰጡት መረጃ ያመለክታል፡፡

ነዋሪዎች በመኖሪያ ቤት ቅጥር ግቢ፣ በዙሪያቸውና ማሳቸው፣ በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት የተለያዩ አትክልቶችንና ፍራፍሬዎችን በመትከል፣ የምግብ ፍጆታቸውን ከመሸፈን ባሻገር ለገበያ እያቀረቡ ነው፡፡ የከተማ ግብርናን ለማጠናከር በተሰራው ስራም በተለያዩ ዘርፎች ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት 4ኛ መደበኛ ጉበዔ ላይ የ2017 በጀት ዓመት አፈፃፀም ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት እንደተናገሩት፣ ማህበረሰቡ በከተማ ግብርና ልማት ስራ ላይ ያለው ግንዛቤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል፡፡ የተሳታፊዎች ቁጥር እና የከተማ ግብርና ምርትም እያደገ ሲሆን፣ በከተማ ግብርና በበጀት ዓመቱ ብቻ በእንቁላል፣ ወተት፣ ማር፣ አሳ እና የጓሮ አትክልት ልማት 280 ሺህ 406 ቶን ምርት ማግኘት ተችሏል፡፡ በዘርፉ የተሰማሩ በርካታ የከተማዋ ነዋሪዎችም ኑሯቸውን አሻሽለዋል፡፡

ምክትል ኮሚሽነርና የኤክስቴንሽን ዘርፍ ኃላፊ አቶ መለሰ እንደተናገሩት፣ በአሁኑ ወቅት በቤተሰብ ፍጆታና ተደራጅተው ለገበያ የሚያቀርቡትን ጨምሮ በቀን ከ2 ሚሊዮን በላይ እንቁላል ይመረታል፡፡ ከዚህ ውስጥ ከፍጆታ ባሻገር ከ509 ሺህ በላይ እንቁላል ለገበያ ይቀርባል፡፡ ወተት በቀን ከ100 ሺህ ሊትር በላይ ይመረታል፡፡ 1 ሚሊዮን 28 ሺህ የህብረተሰብ ክፍሎች እና 2 ሺህ 565 ተቋማት በከተማ ግብርናው ዘርፍ ተሳታፊና ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ፡፡

በመዲናዋ የጓሮ አትክልቶች፣ የእንስሳት ተዋፅኦዎች፣ በዋናነት በማስፋፊያ አካባቢዎች የሰብል ምርቶች ይመረታሉ። ከዚህ ባሻገር የሚያስፈልገው ፍጆታ ከተለያዩ ክልሎች የሚገባ ሲሆን ከአምራች እስከ ሸማች ድረስ ባለው ሂደት በደላላ ጣልቃ ገብነት የሚፈጠረውን ፍትሐዊ ያልሆነ የዋጋ ንረት ለመከላከል በከተማዋ በአምስት መግቢያና መውጫ በሮች የግብርና ምርት መሸጫና ማከማቻ ማዕከላት ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

## “የስራ ... ከገጽ 1 የዞረ

ስፍራዎች አትክልት በመንከባከብ በወር በ3ሺህ ብር ደመወዝ እየሠራሁ እገኛለሁ” ይላል፤ አራት ኪሎ የጋዜጣ ማንበቢያ ስፍራ የስራ ማስታወቂያ ሲያነብ ያገኘነው ወጣት ማስረሻ አቡሃይ።

በ2013 ዓ.ም በኢኮኖሚክስ የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪውን የያዘው ወጣቱ፣ ባንክን ጨምሮ የተለያዩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቢወዳደርም ማለፍ ሳይችል ቀርቷል፡፡ ሆኖም ግን አሁንም ጥረቱን እንደሚቀጥልና ወጣቶች ተመርቀው “ስራ የለም” ብለው ከመቀመጥ ይልቅ ነገ የተሻለ ስራ እስኪያገኙ ያገኙትን ቢሰሩ ሲል ምክሩን ለግሷል፡፡

ሌላዋ አስተያየት ሰጪ ወጣት ራሄል ገብረየሱስም በ2010 ዓ.ም በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የመጀመሪያ ዲግሪዋን ይዛለች። “ከተመረቅሁ በኋላ እስከ አንድ ዓመት የሥራ ማስታወቂያ እከታተል ነበር። አብዛኛው ማስታወቂያ የስራ ልምድ ይጠይቃል፡፡ በዚህም ምክንያት በተማርኩበት ሙያ ስራ እስከማገኝ ቁጭ ከማለት ይሻላል በሚል ኮምፒዩተር ቤት በፀኃፊነት እየሰራሁ ነው” ስትል ገልፃለች።

በ2016 ዓ.ም በአካውንቲንግ እና ፋይናንስ በዲግሪ የተመረቀው ወጣት አማረ ፈንታ “የስራ ማስታወቂያ በየጊዜው እመለከታለሁ፡፡ አብዛኞቹ የስራ መደቦች ደግሞ ከሶስት እስከ አምስት አመት የስራ ልምድ ይጠይቃሉ፡፡ ቅድሚያ የሚያገኙት የሥራ ልምድ ያላቸው ናቸው፡፡ ይህ ለኔ ፈተና ሆኖብኛል፡፡” ይላል፡፡

እነዚህን ለማሳያነት አነሳን እንጂ በመዲናዋ ከትምህርት ተቋማት የተመረቁ፣ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ በርካታ ስራ ፈላጊ ዜጎች ይገኛሉ፡፡ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2022 ያደረገው ጥናት፣ በአዲስ አበባ የስራ አጥነት ምጣኔው 22 ነጥብ 8 በመቶ እንደሆነ ያሳያል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስራና ክህሎት ቢሮ የስራ ስምሪት አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ ሰብሀዲን ሱልጣን ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት መረጃ፤ ቢሮው የስራ እድል ፀጋዎችን በመጠቀም ለዜጎች ቋሚ የስራ እድል ከመፍጠር አንፃር የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ እንደሚገኝ ይናገራሉ፡፡ በዋናነትም የስራ እድል ይፈጠርልኝ ጥያቄ ያላቸው ዜጎች እንዲመዘገቡ በከተማ ደረጃ በየሩብ ዓመቱ ሰፊ የንቅናቄና ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ይሰራል፤ በዚህ መሰረትም ጥያቄ እያቀረቡ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ አኳያ በወረዳ አንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ በኢትዮጵያ የስራ ገበያ መረጃ ስርዓት (E-LMIS) በመመዝገብ ስራ አጥ ካርድ (Labor ID) የያዙ መሆናቸውን በትክክል የማረጋገጥ ስራ ይሰራል፡፡ ስራ አጥ መሆናቸው ከታወቀ በኋላ በመረጡት የስራ ዘርፍ ላይ የቴክኒካልና የልል ክህሎት (Technical and Soft Skills) ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡

ቢሮው ለስራ ፈላጊ የማህበረሰብ ክፍሎች የሚሆኑ የስራ እድሎችን የማመቻቸት ስራ የሚሰራ ሲሆን በዋናነትም በመንግስትና የግል ተቋማት፣ በግዙፍ የመንግስት ፕሮጀክቶች፣ በነባር



ፎቶ ከፋይል

በ2017 በጀት ዓመት ከተፈጠሩ የስራ እድሎች መካከል አንዱ

ኢንተርፕራይዞች ውስጥ የስራ እድል ሊፈጥሩ የሚችሉ ፀጋዎችን የመለየት ስራ በትኩረት ያከናውናል፡፡ ቢሮው የስራ እድል ፀጋዎችን በመለየት ባለፉት ዓመታት ለበርካታ ስራ ፈላጊ ዜጎች የስራ ዕድል እንዲመቻችላቸው አድርጓል። በ2013 ዓ.ም 345 ሺህ፣ በ2014 ዓ.ም 421 ሺህ 850፣ በ2015 ዓ.ም 417 ሺህ፣ በ2016 ዓ.ም ከ291 ሺህ 500 በላይ የስራ እድል ፈጥሯል፡፡ እስከ 2015 ዓ.ም ድረስ የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው በሚል የሚያዘው በጊዜያዊነት እና ቋሚነት ስራ የሚፈጠርላቸው ነበሩ፡፡ ከ2016 ዓ.ም ጀምሮ ግን ስራ እንደተፈጠረላቸው የሚመዘገቡት በቋሚነት የስራ ዕድል ያገኙ ናቸው፡፡

በተጠናቀቀው 2017 በጀት ዓመትም የመስሪያ ቦታ ለሚፈልጉ 2 ሺህ 210 ኢንተርፕራይዞች ቦታ ተሰጥቷል። በከተማ ግብርና፣ በኮንስትራክሽን፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በንግድ፣ በአገልግሎት ዘርፎች በተለዩ የስራ እድል ፀጋዎች ላይ 350 ሺህ ለሚሆኑ ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ 366 ሺህ ለሚሆኑ ዜጎች ቋሚ የስራ እድል በመፍጠር ከእቅድ በላይ ማሳካት እንደተቻለ ዳይሬክተሩ ገልፀዋል፡፡

እንደ አቶ ሰብሀዲን ማብራሪያ፣ ወጣቱ ለስራ ያለውን አመለካከት ወደ አዎንታዊ ለመቀየር ግንዛቤ ማስጨበጥ ላይ በስፋት በመሰራቱ፣ የሚፈልገውን የስራ እድል ፀጋ መለየት በመቻሉ፣ ከግል ባለሃብቱና ባለድርሻ አካላት ጋር ስራ አጥነትን ለመቀነስ በተካሄደ ተደጋጋሚ ውይይት የግል ዘርፉ ለወጣቱ የስራ እድሎችን በመፍጠሩ፣ በኮሪደር ልማቱ ፕሮጀክት በተፈጠሩ የስራ እድሎች እንዲሁም ከማዕከል እስከ ወረዳ ድረስ በከፍተኛ አመራሩ በየሳምንቱ፣ በየአስራ አምስት ቀኑና በየወሩ ስራዎች ላይ ክትትልና ድጋፍ በመደረጉ የስራ ዕድል ፈጠራ አፈፃፀሙ ስኬታማ ሆኗል፡፡

ያነጋገርናቸው ወጣቶች በተማሩበት የሙያ ዘርፍ ስራ ለማግኘት የስራ ማስታወቂያ ቢከታተሉም የስራ ልምድ የሚጠይቅ በመሆኑ በሙያችን ለመስራት ተቸግረናል ሲሉ ላነሱት አስተያየት አቶ ሰብሀዲን ሲመልሱ፤ “በአዲስ አበባ ከተማ የስራ ይፈጠርልኝ ጥያቄ አቅርበው እየተፈጠረላቸው የሚገኙ ዜጎች በርካቶች ናቸው፡፡ መንግስት ለዜጎች በቻለው አቅም የስራ እድልን እያቀረበ ይገኛል። በስራ ዕድል ፈጠራ ዕድገት ተኮር ዘርፎች (ማኑፋክቸሪንግ፣ ከተማ ግብርና፣ ኮንስትራክሽን፣ አገልግሎትና ንግድ ዘርፍ) ያሉ የስራ እድል ፀጋዎችን አሚጥጠን አዘጋጅተናል፤ ፍላጎት ያላቸው ዜጎችም መጥተው እድሉን እየተጠቀሙ ነው፡፡

ሆኖም አንዳንድ ስራ ፈላጊዎች የቀረበላቸውን የስራ እድል ፀጋ ያለመቀበል ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ ሌላው በተማሩት ዘርፍ ብቻ የተሻለ ስራና ደመወዝ በመፈለግ ላይ የተጠመዱ ዜጎች አሉ፡፡ ሆኖም የተሻለ ስራ የማግኘት ፍላጎት እንዳለ ሆኖ ዜጎች መንግስት በሚያቀርባቸው የስራ እድል ፀጋዎች ላይ ለመስራት ቢዘጋጁ እና ስራን ሳያማርጡ በመስራት ተጠቃሚ ቢሆኑ መልካም ነው፡፡ ቢሮውም ስራን ማማረጥ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለማስተካከል ተከታታይነት ያለው የአመለካከት፣ የአቅም ግንባታና ሌሎች ስልጠናዎችን ይተገብራል” ሲሉ አቶ ሰብሀዲን መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

እንደ ዳይሬክቶሬቱ ገለፃ፤ ቢሮው በ2018 በጀት ዓመት ለ350 ሺህ በላይ ዜጎች ቋሚ የስራ እድል ለመፍጠር እቅድ ተይዟል፡፡ የስራ አጥ ምጣኔውንም በረጅም ጊዜ እቅድ (በፈረንጆቹ አቆጣጠር 2030) ወደ ነጠላ አሃዝ ለማውረድ በርብርብ ይሰራል፡፡ እየተለዩ ያሉ የስራ እድል ፀጋዎችን በተለይ ከወጣቱ ፍላጎት አንፃር መቃኘት የበጀት ዓመቱ ዋናው ተግባር ነው፡፡ ይህም ዘመኑ የቴክኖሎጂ በመሆኑ ወጣቶች በኦንላይን ቀለል ያሉ ስራዎችን የሚሰሩበት አግባብ እንዲፈጠር በዚህ ረገድ ያሉ የሥራ እድል ፀጋዎችን መለየት ላይ በትኩረት ይሰራል፡፡ እድሜያቸው ከ18 ዓመት እስከ 26 ዓመት የሆኑ 9 ሺህ 615 ወጣቶች በተለያዩ ድርጅቶች የስራ ላይ ልምምድ እያደረጉ ሲሆን ልምምዳቸውን ሲጨርሱ በ2018 በጀት ዓመት ገበያው ወደሚፈልገው የስራ ዘርፍ እንደሚሰማሩ አቶ ሰብሀዲን አስረድተዋል፡፡

ስራን ማማረጥ ላይ ያለውን የአመለካከት ክፍተት ለመቅረፍም ግንዛቤ ከማስጨበጥ ባለፈ የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም የስራ ባህልን የማዳበር ስራ ይሰራል፡፡ ይህም ከወጣቱ ፍላጎት ጋር ሊሄዱ የሚችሉ የስራ ባህልን፣ ምርታማነትን በሚያሳይ መልክ ትኩረት ያደረገ ‘የሚሰሩ እጆች ወግ’ የሚል ተከታታይ ፕሮግራም ከአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ጋር በመተባባር የሚቀርብ በመሆኑ ሌሎችንም በማካተት የስራ ባህል አመለካከትን ሊያዳብሩ የሚችሉ ስራዎች በሰፊው እንደሚከናወኑ ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል፡፡

ማንኛውም ስራ ፈላጊ የህብረተሰብ ክፍል በተለይ ወጣቶች፣ ተመራቂዎች በከተማዋ በሚገኙ የስራ እድል ፀጋዎች ተጠቃሚ ለመሆን መመዝገብ አለባቸው። ይህም የአዲስ አበባ ከተማ የነዋሪነት መታወቂያ ያለው፣ ስራ አጥ (ስራ ፈላጊ) መሆኑን የሚገልፅ መረጃ በማቅረብ በከተማዋ በሚገኙ በ119 ወረዳዎች ላይ በመመዝገብ መንግስት ባመቻቸላቸው የስራ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ አቶ ሰብሀዲን መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

## ምን ልርዳዎ?

### የስራ ይፈጠርልኝ ጥያቄ ለማቅረብ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች

በአዲስ አበባ ከተማ ስራ ፈላጊ የሆነ ዜጋ የስራ ይፈጠርልኝ ጥያቄ ለማቅረብ ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የአዲስ አበባ ከተማ የነዋሪነት መታወቂያ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡
- ስራ የሌለው/ላት (ስራ ፈላጊ) መሆኑ/ኗ በብሎክ የስራ እድል ፈጠራ ኮሚቴ የተተቸ ወይም የተመሰከረለት መሆን አለበት፣
- እድሜ ከ18 ዓመት በላይ እና ከ60 ዓመት በታች፣
- መንግስት በሚያቀርበው የስራ እድል ፀጋዎች ወይም በሚቀርቡ የስራ እድሎች ላይ ለመሰማራት ዝግጁ የሆነ/ች፣
- በወረዳዎች የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ በኢትዮጵያ የስራ ገበያ መረጃ ስርዓት (E-LMIS) በመመዝገብ ስራ አጥ ካርድ (Labor ID) መያዝ ይጠበቃል።
- መንግስት በሚያመቻቸው የልል እና ቴክኒካል ክህሎት (soft and hard skills) ስልጠና ለመውሰድ ዝግጁ መሆንና መወሰድ ያስፈልጋል፡፡

**ምንጭ፡-** የአዲስ አበባ ስራና ክህሎት ቢሮ

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ

# በምሽት የንግድ እና የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ የወጣው ደንብ ምን ይዟል?

## (ክፍል ሁለት)

ምህረት ወ/ማርያም (ዐቃቤ ህግ)

በምሽት የንግድ እና የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጥ የወጣው ደንብ ቁጥር 185/2017 እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ግዴታ ምንነትን በተመለከተ በክፍል አንድ ፅሁፍ አዘጋጅተንላችሁ ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ ቀጣዩን ክፍል ይዘንላችሁ ቀርበናል፡፡

በደንብ ቁጥር 185 መሰረት ከላይ ከተጠቀሱት ግዴታዎች በተጨማሪ የተቀመጠው ግዴታ መብራት ስለማብራት ሲሆን ይህንንም ግዴታ በደንቡ አንቀጽ 6 ተደንግጎ እናገኘዋለን። በዚህም መሰረት አግባብ ያለው የከተማው አስፈጻሚ አካል ባወጣው የመብራት ስታንዳርድ መሰረት ማንኛውም የአገልግሎት ሰጪ ተቋም፣ የንግድ ተቋም እና የመኖሪያ ቤት የሕንጻ የፊተኛው ገጽ መብራት ወይም የፋሳድ ላይት መብራት ማስገባት እንዳለባቸው አስቀምጧል፡፡ ተቋማቱ ከምሽቱ 12 ሰዓት ጀምሮ እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት ድረስ የተቋማቸውን የውጭ እና የውስጥ መብራት የማብራት ግዴታ አለባቸው ሲል የደንቡ አንቀጽ 6(2) ግዴታ ጥሏል። ከዚህ በተጨማሪም እነዚህ በአንቀጹ መሰረት ግዴታ የተጣለባቸው አካላት መብራቱ የሚሰራ መሆኑን በየዕለቱ ከመምሸቱ በፊት ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል ሲል ደንቡ ያስቀምጣል፡፡

ይህ ግዴታ ከአንቀጹ ንባብ እንደምንረዳው በተቋማት ላይ ብቻ ሳይሆን የተጣለው በመኖሪያ ቤቶች ላይ ጭምር ሲሆን፤ እነዚህ አካላት በደንቡ መሰረት የህንጻቸው የፊተኛ ክፍል ላይ የፋሳድ ላይት መብራቶችን የመግጠም ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

በደንብ ቁጥር 185/2017 መሰረት የተከለከሉ ተግባራት የትኞቹ ናቸው? የሚያስከትሏቸው ቅጣቶችስ?

በደንብ ቁጥር 185/2017 ክፍል ሦስት የምናገኘው ስለ ክልከላዎች እና አስተዳደራዊ እርምጃዎች የሚደነግጉ አንቀጾችን ሲሆን፤ አንቀጽ 8 እነዚህን ክልከላዎች በዝርዝር ይዟል፡፡ በዚህ መሰረትም በአንቀጹ በመጀመሪያ የተቀመጠ ክልከላ የንግድ ተቋማትን የስራ ጊዜን የሚመለከት ሲሆን፤ ማንኛውም የንግድ ተቋም ከምሽቱ 3፡30 በፊት የንግድ ተቋሙን መዝጋት የተከለከለ ነው፡፡ ለተገልጋይ ሊያቀርብ የሚችለው



አገልግሎት ወይም ምርት እያለው የለም በማለት ተገልጋይ እንዳይስተናገድ ማድረግም ፍጹም የተከለከለ ተግባር እንደሆነ ከደንቡ አንቀጽ 8 መገንዘብ የምንችል ይሆናል፡፡ ይህንንም ክልከላ በመተላለፍ ድርጊቱን የፈጸመ ተቋም ከደንቡ ጋር አባሪ በተደረገው አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት ሰንጠረዥ ተራ ቁጥር አንድ እና ሁለት መሰረት ለእያንዳንዱ ህገ-ወጥ ተግባር 10,000 ብር (አስር ሺህ ብር) የገንዘብ ቅጣት እንደሚያስከትል ተደንግጎ ይገኛል፡፡

መንገድ ዳር ያሉ ንግድ ተቋማት እና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ከምሽት እስከ ንጋት ድረስ የተቋሙን የውጭ እና የውስጥ መብራት አለማብራት ሌላኛው የተከለከለ ተግባር ነው፡፡ በቅጣት ሰንጠረዡ ተራ ቁጥር 3 መሰረት 7,000 ብር (ሰባት ሺህ ብር) እንደሚያስቀጣ ተቀምጧል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሕንጻ የፊተኛው ገጽ መብራት ወይም የፋሳድ ላይት መብራት ያለመስቀል እና ያለማብራት በደንብ ቁጥር 185 መሰረት ሌላኛው ክልከላ የተጣለበት ተግባር ነው፡፡ ይህንን ተግባር ያልፈጸመ አካል ማለትም እነዚህን መብራቶች ያልሰቀለ ወይም ደንቡ በሚያዘው ሰዓት መሰረት ያላበራ 5,000ብር (አምስት ሺህ ብር) እንደሚቀጣ የቅጣት ሰንጠረዡ ያስቀምጣል፡፡

የንግድ ተቋማትም የመግቢያ በራቸውን ዝግ በማድረግ አገልግሎት የሚሰጡ ከሆነ ክፍት መሆኑን የሚያመለክት በኤሌክትሪክ የሚሰራ ምልክት ያለማድረግ በደንቡ መሰረት የተከለከለ ተግባር ሲሆን፤ ይህንንም ክልከላ መተላለፍ 5,000 (አምስት ሺህ) ብር እንደሚያስቀጣ ተደንግጓል፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት ክልከላዎች በተጨማሪ በደንብ ቁጥር 185/2017 መሰረት ክልከላዎች የተጣለው በህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ ነው፡፡ እነዚህ ተቋማት ከምሽቱ 4 ሰዓት በፊት የትራንስፖርት አገልግሎት ማቋረጥ ወይም ከስምሪት መውጣት ወይም የስምሪትን መስመር ማቆራረጥ፣ የከተማ አስተዳደሩ ካወጣው የትራንስፖርት አገልግሎት ታሪፍ በላይ ተሳፋሪውን ማስከፈል የተከለከሉ ተግባራት ናቸው፡፡ በቅጣቱ ሰንጠረዥ መሰረት 5,000 (አምስት ሺህ) ብር የሚያስቀጣ ሲሆን፤ የከተማ አስተዳደሩ ካወጣው የትራንስፖርት አገልግሎት ታሪፊ በላይ ተሳፋሪውን ማስከፈል በተመሳሳይ ለብቻው የ5,000 ብር (አምስት ሺህ) የገንዘብ ቅጣት እንዳለው ከቅጣት ሰንጠረዡ ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡

### አስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ

አስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድን በሚመለከት ያለውን ሂደት ደንብ ቁጥር 185 አንቀጽ 9 ላይ በዝርዝር የተቀመጠ ሲሆን፤ በዚህ አንቀጽ መሰረትም አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ሰው የተሰጠውን አስተዳደራዊ ቅጣት ማስታወቂያ ወረቀት በመያዝ ወዲያውኑ ጥፋቱ በተፈፀመበት አካባቢ በሚገኘው የወረዳ ንግድ ጽህፈት ቤት ወይም ትራንስፖርት ቢሮ ቀርቦ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መክፈል አለበት፡፡ መክፈያ ዘዴውም በሦስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ገንዘቡን ገቢ በማድረግ ቅጣቱን መፈጸም እንዳለበት አንቀጹ የሚያስቀምጥ ሲሆን አስተዳደራዊ መቀጫውን ገቢ ያላደረገ ሰው የተጣለበትን የቅጣት ገንዘብ መጠን እጥፍ እንዲከፍል እንደሚደረግ አንቀጹ ያስቀምጣል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም የቅጣት ማስታወቂያ ለመቀበል ፍቃደኛ ካልሆነ እንደተቀበለ ተቆጥሮ እጥፍ እንዲከፍል ይደረጋል ሲል አንቀጹ በግልጽ ያስቀምጣል፡፡

ከላይ በተቀመጠው አግባብ መሰረት የገንዘብ ቅጣት ገቢ ያላደረገ ማንኛውም ሰው ላይ ክስ እንዲቀርብ የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ወይም የትራንስፖርት ቢሮ እንደ ጉዳዩ አግባብነት ማስረጃዎችን በማደራጀት ለከተማው አስተዳደር ፍትህ ቢሮ እንደሚልኩ ደንቡ አስቀምጧል፡፡

ቅሬታና አቤቱታ አቀራረብን በሚመለከት ደንብ ቁጥር 185 አንቀጽ 11 ላይ የአቀራረብ ስርዓት የዘረጋ ነው። ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅር የተሰኘበትን ጉዳይ በመያዝ ውሳኔ በተሰጠበት በሦስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ውሳኔ ለሰጠው አስፈጻሚ አካል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ እንደሚችል እና ቅሬታውን የተቀበለው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴም ቅሬታውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በሚኖሩት 5 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን መርምሮ የውሳኔ ሀሳቡን ለቢሮው ወይም ለትራንስፖርት ቢሮ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ አለበት፡፡ ደንቡ ያስቀመጠው በተመሳሳይ የበላይ ኃላፊውም በ5 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን መስጠት ያለበት ሲሆን፤ ውሳኔው ግን የመጨረሻ እንደሆነ እና በኃላፊው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል።

በአጠቃላይ ደንብ ቁጥር 185/2017 በምሽት የንግድ እና የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ የወጣ ደንብ እንደመሆኑ በእጅጉ የባለድርሻ አካላትን ቅንጅታዊ አሰራርን የሚጠይቅ ደንብ ሲሆን፤ እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል በተለይም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰላም እና ፀጥታ እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ ትራፊክ ማኔጅመንት ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የበኩላቸውን ጉልህ ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል፡፡

# በትጋትና ውጤት የታጀበ የህይወት መንገድ

## “ከሰው ሰራሽ አስተውሎት ጋር የተያያዙ ስራዎችን ኢትዮጵያ ውስጥ ለመስራት በዝግጅት ላይ ነኝ”

ጋዜጠኛ እና የአይሲቲ ባለሙያው ደረጀ ተድላ

በለይላ መሃመድ

“አልችልም” የሚለው ነገር የለም። በጥረት ትልቅ ደረጃ መድረስ እንደሚቻል ያምናል፡፡ በተለይም ንባብ የሰውን ልጅ የአስተሳሰብ አድማስ በማስፋት ህልምን እውን ለማድረግ አይነተኛው መሳሪያ እንደሆነ በጽኑ ተረድቷል፤ በተግባርም ሆኖ አይቶታል፤ የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ (አይ ሲ ቲ) ባለሙያና ጋዜጠኛ ደረጀ ተድላ፡፡

የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያው ደረጀ ኢትዮጵያ ውስጥ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (አይቲ) ተቋም ለመክፈት የሚያስችሉ የተለያዩ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ በመጣበት ወቅት አግኝተን ስለህይወት መንገዱ እንዲነግረን አደረግነው፡፡



ፎቶ- በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ (አይ ሲ ቲ) ባለሙያና ጋዜጠኛ ደረጀ ተድላ

**ኢትዮጵያ ላይ የአይቲ ፓርክ እና ሳይንስ ሙዚየም መቋቋማቸው በዘርፉ ብዙ መስራት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል**

### ከመምህርነት እስከ ጋዜጠኛነት ሙያ የተደረገ ግስጋሴ

ደረጀ፤ የተወለደው በሀዋሳ ከተማ ነው፡፡ በተወለደ በ5 ዓመቱ መምህር አባቱ በዝውውር ወደ አርሲ አመሩ። አርሲ የምትገኘው ሀቡራ ወይንም ሆጎልቾ ከተማም የልጅነት ጨዋታ እና የትምህርት ማዕከሉ ሆና ተቀበለችው። በዚህች ከተማ በሚገኝ ትምህርት ቤት ብዙ የገፉበትን የዘመናዊ ትምህርት አህዱ ብሎ ጀመረ፡፡ እስከ 12ኛ ክፍል ከአርሲ ሳይወጣ፤ ከተሞችን በመቀያየር ተከታተለ፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አርሲ ሁሩታ ከተማ አጠናቀቀ፡፡

ከ12ኛ ክፍል ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚያስገባ ውጤት በማምጣትም ከቀድሞው የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ከአሁኑ ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት ሙያ ተመርቋል፡፡ እንደተመረቀም በሰሜን ሸዋ ዞን፤ መንዝ ሞላሌ ከተማ በሚገኘው ሞላሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመምህርነት ሙያ ለሁለት ዓመታት ያህል አገልግሏል፡፡ እድል ወደ መምህርነት ሙያ ጠልፋ ትውሰደው እንጂ ከውስጡ ታምቆ ያኖረው የጋዜጠኝነት ሙያ ፍቅርን ቸል አላለውም፡፡ ከማስተማሩ ጎን ለጎን የሚወደውን የጋዜጠኛነት ሙያ መስመር እንዳይዝለት ለማድረግ በተለያዩ የሥነ ጽሁፍ ምሽቶች ላይ ተሳትፎ ያደርግ ነበር፡፡ የተለያዩ ይዘት ያላቸውን ፅሁፎች በማሰናዳት የቦታ ርቀት እና ሁኔታ ሳይወስነው በኢትዮጵያ ሬዲዮ እና በለገዳዲ ሬዲዮ ትምህርት ስርጭት አገልግሎት ይሳተፍ ነበር፡፡ እንዲሁም ፈታሽ፣ ጎዳናው፣ ማራቶን እና ሌሎች ጋዜጦች ላይም ይጽፍ ነበር፡፡

ጋዜጠኛ የመሆን ሀሳቡ የተጸነሰው በልጅነት አእምሮው እንደነበር የሚያስታውሰው መምህር፣ ጋዜጠኛና የአይሲቲ ባለሙያው ደረጀ፤ ገና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ እያለ የሚጽፋቸው የተለያዩ አጫጭር ታሪኮች ከሚያምረው የእጅ ጽሑፉ ጋር ተደማምሮ ብዙዎችን ይስብ ነበር፡፡ ከዚህ በመነሳት የአንደኛ ደረጃ መምህሮቹ፤ ‘አንተ ጋዜጠኛ ነው የምትሆነው’ እያሉ የወደፊት እጣ ፈንታውን ይተነብዩ እንደነበር ደረጀ ያስታውሳል፡፡ “ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስሸጋገር በሚኒ ሚዲያ ክበባት ጠንካራ ተሳትፎ ማድረግ ጀመርኩ፡፡ የስፖርትና የመዝናኛ ዜናዎችን እያዘጋጀሁ ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አስደምጥ ነበር፡፡ በማቀርባቸው ፕሮግራሞች በተማሪዎችና በመምህራን አድናቆት ይቸረኝ ስለነበር የበለጠ ጋዜጠኛ የመሆን ፍላጎት እንዲያድርብኝ አድርጎኛል፡፡” በማለት የልጅነት ጊዜውን ያስታውሳል፡፡

“የጋዜጠኝነት ሙያ የነፍሴ ጥሪ ነው” የሚለው መምህር፣ የአይቲ ባለሙያውና ጋዜጠኛ ደረጀ ከሰሜን ሸዋ መንዝ የመምህርነት ቆይታው በኋላ፤ በ1991 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ተቀጥሮ መሥራት ጀመረ፡፡ ወደ አዲስ አበባ የመግባቱ ምስጢርም ሙሉ ለሙሉ ጋዜጠኛ ሆኖ ለመሥራት የሚያስችለውን ዕድል ለማግኘት የሚዲያ ማስታወቂያ በቅርብ ርቀት ለመከታተል ነበር፡፡ በተቀጠረበት ትምህርት ቤት እያስተማረ ሙያውን የበለጠ ለማዳበር ጋዜጦችን፣ መጽሄቶችን ያነብብ እንዲሁም ሌሎች የመገናኛ ብዙሃን አማራጮችን ይከታተል ነበር፡፡ በመምህርነት ሙያ እያገለገለ የጋዜጠኝነት ሙያንም እያነበበ የተለያዩ ሚዲያዎች ላይ የሰዎችን የህይወት ታሪክ ፕሮፋይል፣ ዜናዎችን በመጻፍ መሳተፍ ጀመረ። ይህም ተጨማሪ ገንዘብ አስገኘለት፤ አኗኗሩንም አሻሻለለት፡፡

ከብዙ ጥረት በኋላ “ከአንጀት ካለቀሱ…” እንደሚባለው ወዳለመው የጋዜጠኝነት ሙያ መግባት ቻለ። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በ1992 ዓ.ም ባወጣው ማስታወቂያ ተወዳድሮ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የስፖርት ጋዜጠኛ ሆኖ በቋሚነት መሥራት ጀመረ። የጋዜጠኝነቱን ዓለም ከተቀላቀለ በኋላ ያጋጥመው የነበረውን የተለያዩ ፈተናዎች በነበረው ውስጣዊ የሙያ ፍቅር ያሸንፈው እንደነበር ስራውን ለማሳካት ይሔድበት የነበረው ርቀት ምስክር ነው፡፡ በተለይም አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ይጽፉ የነበሩት በርካታ ጋዜጠኞች የዳበረ ልምድና እውቀት ያካበቱ በመሆናቸው እርሱ የሚጽፋቸው ዘገባዎች፤ መጣጥፎች፤ ወይም ዜናዎች አንባቢያንን እንዲመጥኑ ለማድረግ በጋዜጠኝነትና ሥነ ጽሑፍ ላይ የሚያጠነጥኑ በርካታ መጽሐፍትን ያነብብ ነበር፡፡ በተለይም በወቅቱ በየመስሪያ ቤቱ እንደ አሁኑ የኢንተርኔት አገልግሎት አልተስፋፋም ነበር፡፡ ይህንን ችግር ለመፍታት የግል ኢንተርኔት ቤቶችን በከተማዋ በማማተር የውጭ ዜናዎች ያዘጋጅ ነበር፡፡ ከነበረው ሙያዊ ፍቅር የተነሳ ለኢንተርኔትና ለፕሪንተር ከፍተኛ ገንዘብ ያወጣ እንደነበርም ነግሮናል፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ የጻፈው ጽሁፍ በጋዜጣው ታትሞ በማየቱ ልዩ የደስታ ስሜት ፈጥሮለት እንደነበር ይገልጻል። በወቅቱም ለራሱ ከሚሰጠው ድርሻ በተጨማሪ ሦስት ጋዜጣ ገዝቶ ለቤተሰቡ አባላት እንዲያነቡ ማድረጉን የሚገልጸው አሁንም ቢሆን ለሙያው ያለውን የጋለ ፍቅርና ክብር ባሳበቀ ሁኔታ ነው፡፡ ስሙ በተደጋጋሚ እንዲወጣ ካለው ጽኑ ፍላጎትም ያለመታከት ቶሎ ቶሎ ይጽፍ እንደነበር ነው ያጫወተን፡፡

በዚሁ ስራ ላይ እያለ የሀገር ውስጥና የውጭ ዜናዎችን ተርጉሞ ከማዘጋጀትም በላይ የውጭ ሀገር ሻምፒዮናዎችን ለመዘገብ ብርቱ ጥረት ያደርግ እንደነበር ያስታውሳል፡፡ ይህም ከተለያዩ ዓለም አቀፍ የስፖርት ተቋማት ጋር እንዲፃፃፍ፤ ግንኙነቱንም እንዲያሳድግ ዕድል እንደፈጠረለት ይገልጻል፡፡ የምስራቅ አፍሪካ የአትሌቶች የብቃት ደረጃን (ፐርፎርማንስን) የሚያሳይ ጽሁፍ አዘጋጅቶ ለዓለም አቀፉ እና ለአፍሪካ አትሌቲክስ ፌዴሬሽኖች ማኅበራት እስከመላክም ደርሶ ነበር፡፡ ይህም በሩሲያ ሞስኮ ተዘጋጅቶ የነበረውን የዓለም የቤት ውስጥ አትሌቲክስ ሻምፒዮና እና የጃፓን ፉኮካ ሀገር አቋራጭ ሻምፒዮና ላይ ተገኝቶ የጋዜጠኝነቱን ተልዕኮ እንዲወጣ እድል ፈጥሮለታል፡፡

እነዚህ የውጭ ሀገር ጉዞዎች በተቀራራቢ ጊዜ በመሆናቸውና አንዱን መርጦ መሄድ ስለነበረበት፣ ወቅቱም እነ አትሌት ቀነኒሳ በቀለ፣ ስለሺ ስህን፣ መሰለች መልካሙ፣ ጥሩነሽ ዲባባ እና ሌሎች ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ገንነው የወጡበት በመሆኑ እነዚህ የወቅቱ ዝነኞች የሚወዳደሩበትን የጃፓን ፉኮካን ሀገር አቋራጭ ሻምፒዮናን መርጦ በ1998 ዓ.ም መሄዱን ይናገራል። የጃፓን ተልእኮውን ከተወጣ በኋላ ኑሮውን በዚያው አደረገ። በመቀጠልም በጃፓን ቆይታውም የትምህርት እድልም ሆነ ሙያዊ ስራ ማግኘት ባለመቻሉ እ.አ.አ በ2010 ዓ.ም ወደ አሜሪካ አቀና፡፡

### ከናሳ ጋር ያገናኘችው አሜሪካ

ወደ አሜሪካ ከሄደ በኋላ ህይወትን እንደገና ከአዲስ መጀመር ግድ ሆነበት። በጃፓን ያሳለፈው የህይወት ተሞክሮ የአሜሪካውን ኑሮ አቅልሎታል፡፡ ወደ ሙያ (ፕሮፌሽናል) ስራ ከመግባቱ በፊት ብዙ ጉልበትን የማይጠይቁ ቀለል ያሉ የተለያዩ ስራዎችን ሰርቷል። ታክሲ፣ የሸቶ ፋብሪካ ሽያጭ ባለሙያ በኋላም በማናጀርነት አገልግሏል። አልከን (ALCON) የሚባል የአይን ሌንሶችንና መድሐኒቶችን የሚያመርት እንዲሁም ጥናትና ምርምር በሚያደርግ ካምፓኒ ውስጥ መረጃ ወደ ኮምፒውተር ማስገባትና ምርቶችን ማሸግ ላይ ተቀጥሮ ሰርቷል፡፡ ይህም የጉልበት ስራና ሸክም የሌለው ቢሆንም ረጅም ሰዓት እንዲቆም ያስገድደው ስለነበር መሰልቸትና መማረር አጋጥሞት፣ ሀገሩን ለቅቆ መውጣት እንዳልነበረበትና ለመመለስም ዳድቶት እንደነበር ይገልጻል፡፡

በዚህ ሀሳብ ውስጥ እያለ በአይቲ ሙያ ሰልጥኖ ፕሮፌሽናል ስራ መስራት እንደሚቻል መረጃ ሰማ፡፡ ተቀጥሮ ከሚሰራው ስራ በተጓዳኝ መጽሐፍት ማንበብ ጀመረ፡፡ ጓደኞቹ “አትልፋ አትድከም የትም አትደርስም፤ ጊዜህን አታባክን ባለህበት ለማደግ ሞክር” እያሉ ቢሞግቱትም ማንንም ሳይሰማ በትኩረት ማንበብ ቻለ፡፡ ሁለተኛ ዓመት ላይ ተጨማሪ ስልጠናዎችን እና ዩኒቨርሲቲ በመግባትም የተወሰኑ ትምህርቶችን (ኮርሶችን) ወሰደ፡፡

በመጨረሻም ስራውን በመልቀቅ የተለያዩ የሶፍትዌር ስልጠናዎችን ለስምንት ወራት ያህል ተማረ፡፡ ይህንን ትምህርት ካጠናቀቀ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ሃሊበርተን (Halliburton) በተባለ የጆርጅ ቡሽ የነዳጅ ካምፓኒ ውስጥ በአይ ቲ ባለሙያነት ተቀጥሮ መስራት ቻለ፡፡ በዚሁ ሙያ የተለያዩ ካምፓኒዎች እየሰራ መጣ፡፡ በሂደትም ወደ ፌዴራል

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# ኪነ-ጥበባዊ ዝግጅቶች

**በአብርሃም ገብሬ**



በመዲናዋ ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል
ፎቶ- ከገፀ ድር

በመዲናዋ አዲስ አበባ ባለፉት ቀናት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች እና አዳዲስ ኪነ ጥበባዊ ስራዎች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል። ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም ከተሰናዱ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች መካከል የሙዚቃ ኮንሰርት፣ የመጽሐፍት ዓውደ ርዕይና ውይይቶች፣ የሥዕል አውደ ርዕይ፣ የቴአትር መርሃ ግብር እና ሌሎች መሰናዶዎች ይገኙበታል። ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## መጻሕፍት

“ንባብ ለሕይወት” የተሰኘ የመጻሕፍት አውደ ርዕይ በይፋ ተከፈተ፡፡ “ንባብ ለሕይወት” የመጽሐፍ አውደ ርዕይ ባሳለፍነው ሐሙስ ሐምሌ 24 የተከፈተ ሲሆን፣ የመጽሐፍ አውደ ርዕዩ እስከ ነገ ዕሁድ ሐምሌ 27 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ ይቆያል፡፡

የመጽሐፍ አውደ ርዕዩ የተዘጋጀው በመስቀል አደባባይ አካባቢ በሚገኘው በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል ውስጥ ነው፡፡ በአውደ ርዕዩ የጠፉ መጻሐፎቶችን ከመግዛት ጎን ለጎን ከታዋቂ ደራሲዎች መጽሐፍ የማስፈረምና የፎቶ መነሳት ፕሮግራም ይኖራል ተብሏል። እንዲሁም የመጻሕፍት አሳታሚዎችና አከፋፋዮች መጻሕፍትን በቅናሽ ዋጋ አንደሚያቀርቡ የተገለጸ ሲሆን፣ በአውደ ርዕዩ ላይ የመጽሐፍ ምርቃትና ሀሳብ ማንሸራሸሪያ ልዩ ልዩ መድረኮች ተዘጋጅቷል። የ”ንባብ ለሕይወት” የመጻሕፍት አውደ ርዕይ ንባብ ለህይወት የተሰኘ ፕሮጀክት ከኢትዮጵያ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጻሕፍት አገልግሎት (ወመዘክር) በመተባባር የተዘጋጀ ነው፡፡

በሌላ መረጃ የአንጋፋው ደራሲ የሠርቅ ዳንኤል መጽሐፍ ድጋሚ ሊታተም ነው፡፡ ለዓመታት ከገበያ ጠፍቶ የነበረው የደራሲው ተወዳጅ ድርሰት የሆነው “ቆንጆዎቹ” የተሰኘው መጽሐፍ በቅርብ ቀን ድጋሚ ታትሞ ለአንባቢያን እንደሚያቀርብ አሳታሚው ዋልያ መጻሕፍት መደብር በማህበራዊ የትስስር ገጹ ይፋ አድርጓል፡፡

በሌላ መጽሐፍ መረጃ፣ “ጣፋጭ ፍልስፍና” የተሰኘ መጽሐፍ ለንባብ ሊበቃ ነው፡፡ በረዳት ፕሮፌሰር ዋለልኝ ዕምሩ የተደረሰው ጣፋጭ ፍልስፍና መጽሐፍ በመጪው ሳምንት ለአንባብያን እንደሚቀርብ የመጽሐፉ አሳታሚ ዋልያ መጻሕፍት መደብር ይፋ አድርጓል። ደራሲው ከዚህ ቀደም “በፍልስፍና መደመም” እና “የህይወት ትርጉም” የተሰኙ መጽሐፎችን ለአንባብያን አድርሷል፡፡

“ሁለንታን ማን አመጣው?” በሚል ርዕስ ውይይት ይደረጋል፡፡ ውይይቱ የሚደረገው ነገ እሑድ ሐምሌ 27 ቀን 2017ዓ.ም ከቀኑ 8:00 ሰዓት ጀምሮ ይሆናል፡፡ ዝግጅቱ በዐውደ ፋኅስ የውይይት ክበብ ትብብርና አስተናጋጅነት በኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት (ወመዘክር) አዳራሽ ይደረጋል።

## ሙዚቃ

ታዋቂ ሙዚቀኞች የተጣመሩበት የሙዚቃ ዝግጅት ይደረጋል፡፡ ድምጻዊያኑ ጆኒ ራጋ፣ ሚካኤል በላይነህ እና ዳዊት መለሠ የተጣምሩበት “ሸክ” የተሰኘ ሥያሜ የተሰጠው የሙዚቃ ኮንስርት ዛሬ ቅዳሜ ሐምሌ 26 ቀን 2017 ዓ.ም አመሻሽ ላይ በሚሊኒየም አዳራሽ ይካሄዳል።

ከሙዚቃ ኮንሰርት ራቅ ብሎ የቆየው ጆኒ ራጋ በ”ሸክ” ኮንሰርት በአስዮ ባንድ ታጅቦ የሙዚቃ ስራዎቹን እንደሚያቀርብም ኢቨንት አዲስ ሚዲያ ዘግቧል፡፡ ይህ ኮንሰርት ሚካኤል በላይነህ እና ዳዊት መለሠ በዚህ ዓመት ብቻ ለሶስተኛ ጊዜ የተጣምሩበት ኮንሰርት ነው። ሚካኤል እና ዳዊት አስቀድመው በዚህ ዓመት በሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጪ ሁለት ተከታታይ ኮንሰርቶችን በጥምረት ማቅረባቸው አይዘነጋም፡፡

## ሥዕል

“የቀለማት ግለ-ዝና” የተሰኘው የሥዕል አውደ ርዕይ በመታየት ላይ ነው፡፡ የሰዓሊ ኢያሱ ተላይነህ የስዕል ሥራዎች የቀረቡበት ይሄ አውደ ርዕይ በያዝነው ወር ሐምሌ 2 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ በፈንድቃ የባህል ማዕከል በመታየት ላይ ነው፡፡ ሰዓሊ ኢያሱ “የቁጥብ ገለፃና ረቂቅ የአሳሳል ዘይቤን ተከትሎ ለዓመታት በትጋት እየሰራ ያለ ሰዓሊ መሆኑ በምረቃ ሥነ-ስርዓቱ ተገልጿል፡፡ የቀለማት ግለ-ዝና የሥዕል አውደ ርዕይ እስከ ፊታችን ሐምሌ 28 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ ለጥበብ አፍቃሪያን ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡

## ቴአትር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ ከሚታዩ ቴአትሮች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡ 12ቱ እንግዶች የተሰኘው ቴአትር ቅዳሜ 8:30 ሰዓት በብሔራዊ ቴአትር ቤት ይታያል፡፡ 11፡30 ሰዓት ደግሞ ባሎችና ሚስቶች የተሰኘው ቴአትር በዚያው በብሔራዊ ቴአትር ይታያል፡፡ እሁድ በ8፡30 ሰዓት ደግሞ ንጉሥ አርማህ ቴአትር፣ እንዲሁም እምዬ ብረቷ የተሰኘው ቴአትር ደግሞ በዚሁ በብሔራዊ ቴአትር 11፡30 ሰዓት ላይ ይታያል። እንዲሁም በቀጣይ ቀናት በብሔራዊ ቴአትር የሚታዩት ማክሰኞ በ11፡30 ሰዓት ሶስቱ አይጦች፣ ረዕቡ በ11፡30 ሰዓት የቅርብ ሩቅ ቴአትር፣ ሐሙስ ቀን 11:30 ሰዓት ሽምጋይ ቴአትር፣ አርብ በ11፡30 ሰዓት የሕይወት ታሪክ በብሔራዊ ቴአትር ለጥበብ አፍቃሪያን ለዕይታ ይቀርባሉ፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ የጥያቄውን ትክክለኛ መልስ ለማግኘት በግራ በኩል ከላይ ወደታች የተደረደሩትን ሶስቱን ቁጥሮች እንደምራለን፡፡ እንዲሁም በግራ በኩል ከላይ ወደ ታች ሶስቱን ቁጥሮች እንደምራለን፡፡ ከዚያ በኋላ በግራ በኩል ደምረን ያገኘነው ቁጥር ላይ የቀኙን ድምር እንቀንሳለን፡፡ በዚህ አሰራር መሰረት የምናገኘው ቁጥር የመሃለኛው ቁጥር መምጣት ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሰረት መልሱን በቀላሉ ለማግኘት የመጀመሪያውን ክብ መልስ እንዴት እንደተገኘ አብረን እንስራለን። 16+7+19= 42፤ እንዲሁም 8+2+10 = 20፤ ከዚያ በኋላ 42-20= የመሃለኛው ቁጥር 22 ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡ 7 + 26 + 17 = 50 / 8 + 12 + 10 = 30 / 50 – 30 = **20** ይሆናል፡፡




## የዚህ ሳምንት የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት ዕትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# ልጆች ክረምቱን እንዴት እያሳላፋችሁ ነው?

**በለይላ መሀመድ**



ፎቶ- በሌላ መሀመድ

የክረምቱን ቀናት ውሎአቸውን በጥሩ ሁኔታ የሚያሳልፉት ተማሪ ልዑል ደጀኔ እና ተማሪ ነስረዲን ሸሪፍ

ልጆች፤ በኢትዮጵያውያን የዘመን አቆጣጠር አራት ወቅቶች አሉ፡፡ እነሱም መኸር፣ በጋ፣ ጸደይ እና ክረምት በመባል ይታወቃሉ። ከዚህ ውስጥ ከሰኔ ወር አጋማሽ እስከ መስከረም አጋማሽ ድረስ ያለው ጊዜ የክረምት ወቅት በመባል ይታወቃል። ይህ ጊዜ የተማሪዎች መደበኛ የትምህርት መርሐ ግብር ተጠናቅቆ ትምህርት ቤቶች የሚዘጉበት ወቅት ነው። ታዲያ ልጆች! ይህንን የክረምት የእረፍት ጊዜያችሁን እንዴት ከፋፍላችሁ እያሳለፋችሁ ነው? እናንተ በዚህ ጉዳይ ላይ ሀሳብ እየተለዋወጣችሁ እኛ የሌሎችን ተሞክሮ እንደሚከተለው አካፍለናችኋል፡፡

ስሜ ልኡል ደጀኔ ይባላል፡፡ የምማረው መቅደላ ቅደመ አንደኛ፣ አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን ዘንድሮ ወደ አራተኛ ክፍል አልፌያለሁ። የክረምት የእረፍት ጊዜዬን የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን እያሳለፍኩ ነው። የመጀመሪያው ቤተሰቦቼን መርዳት ነው፡፡ ከጠዋቱ 3 ሰዓት እስከ 5 ሰዓት ድረስ በቤት ውስጥ ስራዎችን እሰራለሁ። ለምሳሌ፡- ቤት አጸዳለሁ። ሱቅ እላላካለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እቃ አጥባለሁ፡፡ በሳምንት ሶስት ቀን ረቡዕ፣ ሀሙስ እና ቅዳሜ ከ5 እስከ 7 ሰዓት ድረስ ውሹ ስፖርት እሰለጥናለሁ፡፡ ውሹ በማልሰራባቸው ቀናት ከ6 እስከ 7 ሰዓት ከጓደኞቼ ጋር እጫወታለሁ፡፡ ማታ ላይ ከ1 ሰዓት እስከ 2 ሰዓት ድረስ የተረት መጽሐፍት አነብባለሁ፡፡

ስሜ ነስረዲን ሸሪፍ ይባላል፡፡ ትምህርት ቤቴ ረጲ ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን፤ ዘንድሮ ወደ ሶስተኛ ክፍል አልፌያለሁ፡፡ በክረምት ወቅት በየቀኑ ጠዋት እስከ አራት ሰዓት ከማከናውናቸው ተግባራት መካከል አንዱ እናቴ የምታዝዘኝን መስራት ነው፡፡ በመቀጠልም ከአራት ሰዓት እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ ከጓደኞቼ ጋር እጫወታለሁ። ከምሳ ሰዓት በኋላ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ቤት ውስጥ ቁጭ ብዬ ስዕል መሳል እለማመዳለሁ፡፡ ማታ ላይ ደግሞ ቴሌቭዥን አያለሁ፡፡

የተማሪ ልኡል ወላጅ እናት ወይዘሮ ዘሪቱ አለሙ ልጃቸው ጊዜውን በፕሮግራም መምራት የሚችልበትን ባህል እንዲያዳብር እገዛ እንደሚያደርጉለት ይገልጻሉ፡፡ በተለይም በክረምት ጊዜውን ተጠቅሞ ልምምድ እንዲያደርግ እያለማመዱት መሆኑን ነው የነገሩን። የቤት ውስጥ ስራ መስራት እንዲችል ለምሳሌ አልጋ ማንጠፍ፣ ጫማና ካልሲ ማጠብ፣ እህት ወንድም መንከባከብ፣ ቤት ማጽዳት ልምድ አድርጎ እንዲያድግ እያደረጉ ነው፡፡ የልጃቸውንም ፍላጎት ለማሟላት ቀናትን እንዲሁም የየእለቱን ጊዜ በመከፋፈል ጊዜውን የውሹ ስፖርት እንዲሰለጥንም ማስገባታቸውን ይገልጻሉ። ስልክ ላይ ብዙ ጊዜ ሲያሳልፍ የሚፈጥረው አሉታዊ ነገር እንዳለ በመረዳታቸው በቻሉት መጠን ለመቆጣጠር እንደሚሞክሩም ነው የነገሩን።

የተማሪ ነስረዲን ወላጅ እናት ወይዘሮ ዘይንያ ሀሰን በበኩላቸው ያለውን ጊዜ በመከፋፈል በየቀኑ ምን ማከናወን እንዳለበት በፕሮግራም እንዲመራ የማድረግ ልምድ እንዳላቸው ይገልጻሉ፡፡ በብዛት ከሰዓት በፊት የቤት ውስጥ ስራ ይሰራል፡፡ ለምሳሌ፡- ቤት ያስተካክላል፣ ታናናሾቹን ይንከባከባል። በግሉ መስራት የሚፈልገውን ነገር እንዲሰራም ያበረታታሉ፡፡ ስዕል መሳል ስለሚወድ በሚስልበት ወቅት ምንም አይነት ትእዛዝ አያዝዙትም፡፡ በዚህም የክረምት የእረፍት ጊዜውን ደስተኛ ሆኖ እያሳለፈ ይገኛል፡፡ ከሰፈር ጓደኞቹ ጋር የሚጫወትበት ጊዜም አለ ብለዋል፡፡

የስነ ልቦና ባለሙያ ሂላል ይመር እንደገለጹት፣ ልጆች ረጅሙን ጊዜያቸውን አዕምሯቸው በትምህርት ተወጣጥሮ ስለቆየ ክረምቱን በጨዋታና መዝናናት ማሳለፍ አለባችሁ፡፡ ጨዋታ ሲባል ለምሳሌ ከቤተሰብ ጋር አልያም አቅም ካለ ስፖርት ቤት ገብታችሁ ከ30 እስከ አንድ ሰዓት የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ብታደርጉ፤ ውጪ ወጥታችሁ የምትፈልጉትን ጨዋታ ብትጫወቱ፣ ለ30 ደቂቃ በቴሌቪዥን ትምህርት የምትቀስሙባቸውን ነገሮች ብታዩ ጥሩ ነው፡፡ እንደየፍላጎታችሁ የፈጠራ ክህሎታችሁን የሚያሳድጉ ስራዎች ላይ ትኩረት ብታደርጉ ጥሩ ነው፡፡ ሌላው ከቤተሰብ ጋር መወያየትን ማዳበር ያስፈልጋል፡፡ ይህ ወላጆች የእናንተን የልጆቻቼውን የወደፊት ህልምና ፍላጎት ለማወቅ ይረዳቸዋል፡፡

ልጆችዬ፤ ቀሪው የክረምት የእረፍት ጊዜያችሁ መልካም እንዲሆንላቸው እንመኛለን፡፡

## 5 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**እልም ካለ ዱር ገብቼ የምቆርጠው አጥቼ**

**መልሱ :-** ለ. ቡና

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**አፉ ዝም ብሎ በእጁ የሚናገር**

ሀ. ፀሐፊ

ለ. እንስሳ

ሐ. ተዋናይ

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ::**

# በጎነት ያቀናቸው ጎጆዎች

## “እንደ ሰማይ ርቆኝ የነበረው በንፁህ ቤት የመኖር ህልሜ በልበ ቀናዎች እውን ሆኗል”

ቤታቸው የታደሰላቸው ወይዘሮ የሽብርጌጥ በቀለ



ፎቶ- ከጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ኮሙኒኬሽን ጽህፈት ቤት
ወይዘሮ የሽብርጌጥ በቀለ በታደሰላቸው ቤት ውስጥ



ፎቶ- ከጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ኮሙኒኬሽን ጽህፈት ቤት
ወይዘሮ ሀድራ ከድር በታደሰላቸው ቤት ውስጥ

**በለይላ መሀመድ**

ወይዘሮ ሀድራ ከድር ይባላሉ፡፡ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ልዩ ስሙ “አባዲና” ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ነዋሪ ናቸው። በመኖሪያ ቤቱ ምክንያት ተቸግረው ዓመታትን አሳልፈዋል። ከቤቱ እርጅና ምክንያት በክረምት ወቅት ጣሪያው ስለሚያፈስስ፣ ግድግዳው ስለሚርስ ቤቱ እንዲሸት ያደርገዋል፡፡ የቤቱ ውስጥ ቅዝቃዜና ሽታ ደግሞ ወላጅ እናታቸው የአስም በሽተኛ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። እሳቸውም ቢሆን በከባድ የራስ ምታት ህመም ስቃይ ውስጥ ነበር ይኖሩ የነበሩት፡፡ አብዛኛው ልብሳቸው ሻግቶና በስብሶ ከጥቅም ውጪ የሚሆንበት ጊዜም ነበረ፡፡ በመሆኑም “መቼ ይሆን ከዚህ አይነት የስጋት ኑሮ የምወጣው?” የሚለው የዘወትር ጥያቄያቸው እንደነበር ያስታውሳሉ።

ቤታቸው ከታደሰላቸው በኋላ አዕምሯቸው መረጋጋት እንደቻለ እንዲሁም ሁልጊዜ አልለያቸው ብሎ የነበረው የራስ ምታት ህመም እንደተወገደላቸው ወይዘሮ ሀድራ ገልጸዋል፡፡ ቤታቸው ከመታደሱ በተጨማሪ የወለል ምንጣፍ፣ ፍራሽ እና የአልጋ ልብስ በስጦታ እንደተበረከተላቸውና አጠቃላይ በተደረገላቸው ድጋፍ ደስተኛ መሆን መቻላቸውንም ይገልጻሉ፡፡

የወይዘሮ ሀድራ ጎረቤት ወይዘሮ ምንትዋብ ሙሉጌታ ስለጎረቤታቸው አኗኗር ሲገልጹ፤ በአንዲት በተጨናነቀች ክፍል ውስጥ ነበር የሚኖሩት፣ የሚያበስሉትና የሚተኙትም እዛው ነው፡፡ ጠባብ ከመሆኑም በላይ የፈራረሰ ስለነበር ኑሯቸውን ፈታኝ አድርጎት ቆይቷል፡፡ ምርጫ ማጣት ካልሆነ በስተቀር የሰው መኖሪያ አልነበረም። የጣሪያው ማፍሰስ ለግድግዳው መፍረስ ምክንያት ሆኗል፡፡ የግድግዳው መፍረስ ደግሞ ተኝቶ ለማደር ይከብድ ነበር። ዙሪያውን በላስቲክ ሸፍነው ነበር የሚኖሩት፡፡ እንደ ጎረቤት እንጨነቅና እናዝን ነበር፡፡ መቆየት ደግ ነው፤ አሁን ላይ በዚህ ሁኔታ እንደገና ፈርሶ በመሰራቱ ለወይዘሮ ሀድራ ዳግም ውልደት ነው ሲሉ የነበረውንና የአሁኑን ልዩነት በንጽጽር ይገልጻሉ፡፡

ወይዘሮ የሽብርጌጥ በቀለ ለበርካታ ዓመታት የኖሩበትና በላያቸው ላይ መፍረስ በጀመረው ቤታቸው በየዓመቱ ክረምት ግም ሲል ጀምሮ እየበረታ የሚመጣውን የክረምት ዝናብ እንዲሁም አጥንት ዘልቆ የሚሰማውን ቅዝቃዜ ተቋቁመው መኖር ከጀመሩ ዓመታትን አስቆጥረዋል፡፡ ወይዘሮዋ ነዋሪነታቸው በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ልዩ ስሙ “ጎላን ጠጅ ቤት” በሚባል አካባቢ ነው። የሰው ቤት እንጀራ እየጋገሩ የልጅ ልጆቻቸውን የሚያስተዳድሩት ወይዘሮ የሽብርጌጥ፤ ጣሪያው እንደወንፊት የተበሳሳ ቤታቸውን ለማደስ አቅም ቢያጡ የክረምቱን ዝናብ ለመከላከል ላስቲክ ለብሰው ለማደር ተገድደዋል። በዝናብ ወቅት ቤታቸው በፍሳሽ ስለሚሞላ ሕይወትን ፈታኝ አድርጎባቸው እንደቆየ ወይዘሮዋ ተናግረዋል፡፡

“እንደሰማይ ርቆኝ የነበረው በንጹህ ቤት የመኖር ህልሜ በልበ ቀና በጎ ፍቃደኞች ቤታቸው ፈርሶ በብሎኬት በመሰራቱ ደስታዬን እና ምስጋናዬን በቃላት መግለጽ አልችልም” ብለዋል፡፡፡፡

የ14 ዓመቷ የልጅ ልጃቸው ተማሪ ቤዛዊት አልየ ዝናብ ሲዘንብ ላስቲክ ለብሰው ይተኙ ስለነበር ሌሊቱን ሁሉ መላ ቤተሰቡን እንቅልፍ ሳይወስዳቸው ቁጭ ብለው ያድሩ እንደነበር ትገልጻለች። እሷና ወንድሟ እንቅልፍ ሲያናውዛቸው ቤታቸው ለመተኛነት አመቺ ባለመሆኑ ሲነጋ ጓደኞቻቸው ቤት ሄደው ይተኙ እንደነበር ትናገራለች፡፡

የወይዘሮ የሽብርጌጥ ጎረቤት ወይዘሮ አረጋሽ እምሩ በበኩላቸው ቤታቸው ላያቸው ላይ ፈርሶባቸው ወና ቤት ውስጥ ነበር የሚኖሩት፡፡ አሁን በደረቅ ቤት ውስጥ ለመኖር በቁ፡፡ ከችግራቸው ያወጧቸው አካላት ምስጋና ይገባቸዋል ብለዋል፡፡

ሌላኛዋ አስተያየት ሰጪያችን ወይዘሮ ወርቅነሽ መኩሪያ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 ልዩ ስሙ “ሞጋ ኩባንያ” በሚባለው አካባቢ ነዋሪ ናቸው፡፡ ቤታቸውን ከ50 ዓመታት በላይ ኖረውበታል፡፡ የበኩር ልጃቸውን በአንቀልባ አዝለው እንደገቡም ይናገራሉ፡፡ የቤታቸው ስሪት ከአፈር በመሆኑ ለአደጋ የሚያጋልጥና የክረምቱን ዝናብ መመከት የማይችል ቢሆንም ኑሯቸው ከእጅ ወደ አፍ በመሆኑ ማደስ አልቻሉም። ይህም ኑሯቸውን አስቸጋሪ አድርጎባቸው ቆይቷል፡፡

በተለይም ክረምት ሲመጣ ለተደራራቢ ችግር ይጋለጣሉ፡፡ ጣሪያና ግድግዳው የተከፋፈተ በመሆኑ ቤታቸው የአይጥ መናኸሪያ ይሆናል፡፡ በዚህም የእንጀራ መሶባቸውን ዙሪያውን በጨርቅ በማሰር እራስጌያቸው አድርገው እያዳመጡ እስከማደር ደርሰዋል፡፡ አይጦቹ፣ “እንጀራውን እንበላለን”፤ ወይዘሮ ወርቅነሽ፣ “አትበሉም” በሚል ከአይጥ መንጋ ጋር ግብግብ ፈጥረው ያድሩ እንደነበር ነው የሚገልጹት፡፡ ከዚህ ባለፈ በክረምት ለቅዝቃዜ እንዲጋለጡ አድርጓቸዋል፡፡ ላስቲክ ለብሰው ነበር የሚያድሩት፡፡ ከላይ የሚወርደው ዝናብና ከጎን የሚነፍሰው ነፋስ ተዳምሮ ወይዘሮ ወርቅነሽን ለበሽታ አጋልጧቸዋል፡፡ “ብርዱ አጥንቴ ውስጥ ገብቶ የቁርጥማት በሽተኛ ሆኛለሁ” ይላሉ፡፡

ባለፈው ዓመት የክረምት የበጎ ፍቃድ መርሃ ግብር ቤታቸው ታድሶላቸው ለገና በዓል መግባታቸውን ሲገልጹ የደስታ እምባ እያነቡ ነበር፡፡ ደስታቸው እጥፍ ድርብ በመሆኑ የውስጣቸውን ስሜት አውጥተው ለመግለጽ እንደተቸገሩም ይናገራሉ። ምስጋና ለማቅረብ ቢያስቀድሙም እንባቸው እየቀደመ ተቸገሩ። በመጨረሻም “ከብርድ አውጥታችሁ የሞቀ ቤት ውስጥ ያስገባችሁኝ ሁሉ ፈጣሪ የልቦናችሁን ይሙላው” በማለት መርቀዋል።

በጉለሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 8 ህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ዘይነባ ዴታሞ እንደገለጹት፣ በጎ ፍቃደኞችን በማስተባበር በወረዳው በ2016/17 በጀት ዓመት የአቅመ ደካማ ሰዎችን ቤቶች የማደስ ስራ ተከናውኗል፡፡ በ2017 በጀት ዓመት ብቻ 40 ቤቶችን ለማደስ ታቅዶ የ30 ቤቶች እድሳት የተደረገ ሲሆን፤ ከነዚህም ውስጥ 27ቱ ሙሉ በሙሉ ፈርሰው መሰራታቸውና ሶስቱ የጣራ እድሳት ተደርጎላቸዋል፡፡ በዘንድሮው የክረምት የበጎ ፍቃድ መርሃ ግብር ደግሞ 23 ቤቶችን ለማደስ የታቀደ ሲሆን አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የ10 ቤቶች እድሳት ተጀምሯል፡፡

በአራዳ ክፍለ ከተማ የወረዳ 7 ህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ ታደለች ታንቱ በ2017 በጀት ዓመት በክረምትና በበጋ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ባለሀብቶችን በማስተባበር 52 የአቅመ ደካማ ቤት ለማደስ ታቅዶ በ54 ሚሊየን ብር ወጪ 54 ቤቶችን ማደስ ተችሏል። እድሳት የሚደረግላቸው ቤቶች “የማን ችግር ከማን ይበልጣል?” በሚል በአደረጃጀቶች ልየታ ከተደረገ በኋላ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በ2018 የክረምት በጎ ፍቃድ መርሃ ግብርም 27 ቤቶችን ለማደስ እቅድ የተያዘ ሲሆን፤ እስካሁን የ8 ቤቶች እድሳት እንደተጀመረ አክለዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሕብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን የበጎ ፈቃድ ግንዛቤ ማስረፅ ቡድን መሪ አቶ ቢኒያም ጊቻ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ በተጠናቀቀው 2017 በጀት ዓመት 8 ሺህ 786 የአቅመ ደካማ ቤት ግንባታ እድሳት ተከናውኗል፡፡ በዚህም የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን ህይወት ማቃለል ተችሏል፡፡ የዘንድሮው የክረምት በጎ ፍቃድ መርሃ ግብር ከግንቦት 30 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም 30 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ የሚቆይና 15 ዋና ዋና ተግባራትን ያካተተ የክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መርሃ ግብር እቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ተገብቷል። ከእነዚህም መካከል የቤት እድሳትና ግንባታ መርሃ ግብር አንዱ ሲሆን 2 ሺህ 500 ቤቶችን በማደስና በመገንባት 12 ሺህ 500 አረጋዊያንን፣ አቅመ ደካሞችን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ የሀገር ባለውለታዎችን እና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የህብረተብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዷል። እስካሁንም የ1 ሺህ 671 ቤቶች እድሳት በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

ኢኮኖሚ

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# ተግዳሮት ያልበገረው ውጤት

- ባለስልጣን  መስሪያ ቤቱ በ2017 በጀት ዓመት አፈጻጸሙ በአስተዳደሩ ሽልማት ማግኘት ችሏል




ፎቶ- ከመንገዶች  ባለስልጣን

መንገዶች  ባለስልጣን በ2017 በጀት ዓመት አፈፃፀሙ በከንቲባ አዳነች አቤቤ ሽልማት ሲበረከትለት



ፎቶ- ከመንገዶች  ባለስልጣን

የአንበሳ ጋራጅ - ጎሮ መንገድ ከፊል ገፅታ

**በሳምሶን ዮሐንስ (ከመንገዶች ባለስልጣን)**

የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን በመንገድ እና ተያያዥ መሰረተ ልማት ግንባታ፣ ጥገናና አስተዳደር የከተማዋን ህዝብ ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ከማስጠበቅና ሀገራዊ ተልዕኮውን ከማሳካት አንፃር ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ ይገኛል፡፡

በ2017 በጀት ዓመት የሁለተኛውን ምዕራፍ የኮሪደር ልማትና መደበኛ ተግባራትን በላቀ አግባብ ለመፈፀም በቂ ቅድመ ዝግጅት አድርጎ ወደ ተግባር የገባው ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ 1 ሺህ 391 ኪሎ ሜትር የመንገድ ግንባታና ጥገና ስራዎች አከናውኗል፡፡

በሌላ በኩል ከ11 ቢሊዮን ብር በሚበልጥ ወጪ ሲገነቡ የቆዩ 21 የመንገድ ፕሮጀክቶችን አጠናቅቆ ለትራፊክ ክፍት አድርጓል፡፡

ከተከናወኑት የግንባታ ስራዎች መካከል 69 ነጥብ 4 ኪሎ ሜትር የአስፋልት፣ 16 ነጥብ 1 ኪሎ ሜትር የጠጠር፣ 95 ነጥብ 2 ኪሎ ሜትር የኮብል ስቶን፣ 107 ኪሎ ሜትር የእግረኛ መንገዶች፣ 3 ነጥብ 7 ኪሎ ሜትር የድሬኔጅ መስመሮች እና የድጋፍ ግንብ፣ 79 ነጥብ 2 ኪሎ ሜትር የሳይክል መንገድ ግንባታ የሚያካትት ሲሆን በድምሩም 370 ነጥብ 5 ኪሎ ሜትር ይሸፍናሉ፡፡

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከግንባታ ስራዎች ጎን ለጎን በተለያዩ ምክንያቶች ለብልሽት የተዳረጉ 1 ሺህ 021 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያላቸው ልዩ ልዩ የመንገድ መሠረተ ልማቶች ጥገና አከናውኗል። በ2017 በጀት ዓመት የተከናወነው የመንገድ ግንባታና ጥገና ስራ ከአምና ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ25 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡

በኮንትራት የሚከናወኑ የመንገድ ፕሮጀክቶችን ግንባታ በማጠናቀቅ ለትራፊክ ክፍት ለማድረግ ከፍተኛ ክትትልና ድጋፍ መደረጉ፣ ከኮሪደር ልማት ጋር በተያያዘ ሰፊ የመንገድ መሰረተ ልማት ስራዎች መከናወኑ፤ ነባር የእግረኛ መንገዶች ላይ የመልሶ ማልማት ስራ በስፋት መከናወኑ፤ በድሬኔጅ እና ድጋፍ ግንብ ስራዎች ከራስ ሃይል በተጨማሪ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሥራዎች መሰራታቸው፤ በመንገድ ጥገና ስራዎች ላይ የተሻለ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች አቅርቦት መኖሩ ለተመዘገበው የተሻለ አፈፃፀም በምክንያትነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ከመንገድ መሠረተ ልማት ግንባታና ጥገና ባሻገር ጥራትና ደረጃቸውን የጠበቁ ልዩ ልዩ የግንባታ ግብዓቶችን የሚያመርተው ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ለመንገድ ግንባታና ጥገና አገልግሎት የሚውሉ ከ3 ቢሊዮን ብር በላይ ግምት ያላቸው የካባ ምርቶች፣ የሲሚንቶ ውጤቶች እና የአስፋልት ኮንክሪት ውጤቶችን በራስ አቅም በማምረት ለተለያዩ የግንባታና ጥገና ስራዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ አድርጓል፡፡

የሥራ ዕድል ከመፍጠር አንፃር በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ በቅጥር፣ በተቋራጭና በአማካሪ ድርጅቶች እንዲሁም ከተቋሙ ጋር በትስስር በሚሰሩ የተለያዩ ማህበራት አማካኝነት ለ14 ሺህ 468 ዜጎች ቋሚ እና ጊዜያዊ የስራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡

የስራ ተቋራጮች እና የአማካሪዎች ደካማ የስራ አፈፃፀም መኖር፣ በመንገድ ወሰን ውስጥ የሚገኙትን የልማት ተነሺዎች በተቀመጠው ምልክት መሠረት አለማስፈረስና ከፈረሰ በኋላም ከአማካሪ መሀንዲሱ ጋር ርክክብ አለማድረግ፣ የመሰረተ ልማት ማዛወሪያ ክፍያዎች ቶሎ አለመከፈል... ተቋሙ በበጀት ዓመቱ ካጋጠሙት ተግዳሮቶች መካከል የሚጠቀሱ ቢሆንም የተለያዩ መፍትሔዎችን በማስቀመጥ ችግሮቹን ለመቅረፍ ጥረት ተደርጓል፡፡

በተለይም ለፕሮጀክቶቹ በወቅቱ አለመጠናቀቅ ዋነኛ ተግዳሮት የሆነው የወሰን ማስከበር ችግር በበጀት ዓመቱ ካጋጠሙ ተግዳሮቶች መካከል በዋነኛነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ይሁንና ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከክፍለ ከተሞችና ከመሰረተ ልማት አልሚ ተቋማት ጋር ባደረገው ክትትል ባለፈው አንድ ዓመት ውስጥ 564 መኖሪያ ቤቶች፣ 835 የኤሌክትሪክና 410 የኢትዮ ቴሌኮም መሠረተ ልማቶች የማንሳት ሥራ ተከናውኗል፡፡ ለዚህም ከ3 ቢሊዮን ብር በላይ ክፍያ እንዲፈፀም ተደርጓል።

በበጀት ዓመቱ የመንገድ ጥገና ስራዎችን በማከናወን የትራፊክ ፍሰት እንዲሻሻል መደረጉ፣ በበጀት ዓመቱ በግንባታ ላይ የነበሩ 6 የኮንትራት እና 8 የራስ ሃይል ፕሮጀክቶችን እንዲሁም የካሳንቺስ እና የአንበሳ ጋራጅ-ጎሮ የኮሪደር ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅ ለአገልግሎት ክፍት እንዲሆኑ መደረጉ ባለስልጣን መስሪያ ቤት በ2017 በጀት ዓመት ያስመዘገባቸው ቁልፍ ስኬቶች ናቸው፡፡

የምዕራፍ 2 የኮሪደር ልማት ቀሪ ስራዎችንና መደበኛ ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ፣ ለወሰን ማስከበር ችግሮች መፍትሔ መስጠት፣ በምንዛሬ ምጣኔ ለውጥ ምክንያት በፕሮጀክቶች ላይ የሚመጣውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቋቋም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትኩረት መስራት፣ ደካማ አፈፃፀም ያላቸው ስራ ተቋራጮች እና አማካሪዎች ላይ በውሉ መሰረት ጥብቅ ክትትል ማድረግ በቀጣይ በጀት ዓመት ከሚከናወኑ ሥራዎች መካከል ይገኙበታል፡፡

በተጨማሪም በመንገዶች ላይ የሚፈፀሙ ህገ ወጥ ድርጊቶችን ለመከላከል እንዲቻል የመንገድ ሀብት አጠቃቀም መመሪያ በፍጥነት ፀድቆ ወደ ተግባር እንዲገባ ማድረግ፤ የምርምር፣ ቴክኖሎጂ እና ስርፀት ስራዎች ላይ ትኩረት መስጠት፤ ጀማሪ ሀገር በቀል ስራ ተቋራጮችን እና አማካሪ መሀንዲሶችን የሚያሳትፍ ፕሮጀክት ማዘጋጀት ከቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች መካከል ይገኙበታል፡፡

> **በ2017 በጀት ዓመት የሁለተኛውን ምዕራፍ የኮሪደር ልማትና መደበኛ ተግባራትን በላቀ አግባብ ለመፈፀም በቂ ቅድመ ዝግጅት አድርጎ ወደ ተግባር የገባው ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ 1 ሺህ 391 ኪሎ ሜትር የመንገድ ግንባታና ጥገና ስራዎች አከናውኗል**

1 ሺህ 184 ነጥብ 15 ኪሎ ሜትር የመንገድ ግንባታና ጥገና ስራዎች ለማከናወን አቅዶ 1 ሺህ 392 ኪሎ ሜትር በማከናወን ከጠቅላላ ዕቅዱ ከ100 ፐርሰንት በላይ አፈፃፀም አስመዝግቧል። ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ይህን ውጤት ማስመዝገብ የቻለው ያጋጠሙትን በርካታ ተግዳሮቶች አልፎ ነው፡፡ በዚህ ስኬታማ አፈፃፀሙም በአስተዳድሩ ከሚገኙና የካቢኔ አባል ካልሆኑ ተቋማት መካከል የሶስተኛ ደረጃ በማግኘት የተሸከርካሪ ተሸላሚ ሆኗል፡፡

ይህ ውጤት እንዲመዘገብ የተቋሙ አመራሮችና ሰራተኞች በቁርጠኝነትና በቅንጅት መስራታቸው፤ በአፈፃፀም ወቅት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን ለመፍታት በአመራሩ ጥብቅ ክትትልና ተከታታይነት ያለው የፕሮጀክቶች የክትትልና ግምገማ መከናወኑ ጉልህ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

**ቁጥር 001/2018ዓ/ም**

**በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስ የሰዉ ሃብት ልማት ጽ/ቤት ግዥ ቡድን ለ2018 በጀት ዓመት አንደኛ ዙር ጨረታ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ዕቃዎችና አገልግሎቶች በመደበኛ በጀት በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል። ስለሆነም**

| ሎት | አይነት | የጨረታማስከበሪያ C.P.O | ሎት | አይነት | የጨረታማስከበሪያ C.P.O |
|---|---|---|---|---|---|
| ሎት 1 | መስተንግዶ | 7000.00 | ሎት 10 | የቋሚ እቃ | 10,000.00 |
| ሎት 2 | ህትመት | 4000.00 | ሎት 11 | የመኪና ጎማና ባትሪ | 8,000.00 |
| ሎት 3 | የፎቶ ኮፒ እና የኮምፒዩተር ጥገና | 5000.00 | ሎት 12 | ኤቨንት | 5,000.00 |
| ሎት 4 | የከባድ መኪና ጥገና (ጋራዥ) | 10,000.00 | ሎት 13 | የተለያዩ የጉልበት ስራዎች | 2,000.00 |
| ሎት 5 | የከባድ መኪና የጎማ ጥገና | 5,000.00 | ሎት 14 | የመኪና ፓርኪንግ ጥላ ስራ | 5000.00 |
| ሎት 6 | የትራንስፖርትና የጭነት መኪና ኪራይ | 3000.00 | ሎት 15 | ላይቫይጆ ማቴሪያል ስራ | 2,000.00 |
| ሎት 7 | የደንብ ልብስ | 3,000.00 | ሎት 16 | የቢሮ ዕቃዎች ጥገና | 2,000.00 |
| ሎት 8 | የፅዳት እቃ | 3,000.00 | ሎት 17 | የኤሌክትሪክና ዉሃ መለዋወጫ ዕቃዎች | 2,000.00 |
| ሎት 9 | የፅህፈት መሳሪያ | 5,000.00 | ሎት 18 | የህንፃ የውስጥ እጥበት | 2,000.00 |

**ብቃት ያላቸውንና በመስኩ የተሰማሩ ተጫራቾችን አወዳድሮ ግዥ መፈጸም ይፈልጋል በዚህም መሰረት:-**

1. በጨረታው ለመወዳደር ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው፤ የዘመኑ ግብር የከፈሉ፤ የቲን ቁጥር እና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑ፤ በአቅራቢነት የተመዘገቡና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ እንዲሁም ሎት 4 የባለቤትነት ማረጋገጫ ሊብሬ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
2. ተጫራቾች የጨረታውን ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ ከላይ በሰንጠረዥ በተቀመጠው ሎት መጠን ማስያዝ ያለባቸው ሲሆን የጨረታ ማስከበሪያ ከጨረታ ሰነዳቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
3. ተጫራቾች የጨረታውን ዝርዝር የያዘ ሰነድ የማይመለስ ብር 250.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ብር ብቻ) በመክፈል ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የስራ ቀናት ኃይሌ ጋርመንት አደባባይ ን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ፐብሊክ ፑል የሰዉ ሃብት ልማት ጽ/ቤት ግዥ ቡድን 6ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 3 መግዛት ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች የገዙትን የጨረታ ሰነድ በመሙላት እና ከላይ የተገለጹትን ማስረጃዎች በ2 ፖስታ ዋናውን እና ኮፒውን በማሸግ ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 10ኛቀን 11:30 ሰዓት ድረስ ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
5. ጨረታው በ11ኛው ቀን ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪል በተገኙበት ልክ በ4:00 ሰዓት ይከፈታል፡፡
6. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡
7. በግልፅ የማይታዩ መረጃዎች እና ስርዝ ድልዝ በመስሪያ ቤ/ቱ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ ቢያስፈልግዎት ስልክ 0912885086 ይደውሉ**

**የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ፐብሊክ ስርቪስ የሰዉ ሃብት ልማት ጽ/ቤት የመንግስት ግዢ ቡድን**

---

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀድሞ 20 ቀበሌ 46 በአዲሱ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 897 በካርታ ቁጥር 09/04/4606/60182/01 በአቶ/ወ/ሮ/እነ ዮሐንስ አደራጀው ስም ተመዝግቦ ተሰጥቶ የነበረ ካርታ የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም ምክንያት ይገኖዋለሁ የሚል አካል ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ በመቅረብ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይገኖዋለሁ የሚል ከሌለ ተለዋጭ ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 277 በመክቱብ ሪል ስቴት ትሬዲንግ አክሲዮን ማህበር ስም የተመዘገበው የይዞታ ካርታ ቁጥር 04/212/1/159961 በቀን 25/10/2013 ሴሪ ቁጥር 077255 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 24/11/2017 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ካርታ ይገኖዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

## የ4 ኪሎ... ከገጽ 7 የዞረ

በተለይ አዲስ አበባ ከተማ የ4 ኪሎ ፕላዛን ጨምሮ በሌሎች ፕሮጀክቶች እየተጠናከረ መምጣቱ ይበል የሚያሰኝ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

እንደሳቸው ገለፃ፤ በመሬት ውስጥ ያለን ቦታ ለተለያየ አገልግሎት በሚውል አግባብ ማልማት ውስን የሆነውን ሃብት በተሻለ ደረጃ (እሴት ጨምሮ) ለመጠቀም ያስችላል፡፡ በውስን የመሬት ይዞታ ላይ በርካታ ዜጎችን የሚጠቅም መሰረተ ልማት ለአገልግሎት ለማብቃት ዕድል ይፈጥራል። በከተማዋ የሚታየውን የትራፊክ መጨናነቅ፣ የማምረቻ እና የመሥሪያ ቦታ እጥረት ያቃልላል። ለዜጎች የሥራ ዕድልን ይፈጥራል። ራስን፣ ቤተሰብንና ሀገርን ሊለውጡ የሚችሉ ሃሳቦችን መጋራት የሚያስችሉ ሁነኛ አካባቢዎች ሆነውም ያገለግላሉ፡፡ ስለዚህ የ4 ኪሎ ፕላዛን ዓይነት የመሬት ውስጥ መሰረተ ልማቶችን ያካተቱ ፕሮጀክቶች መስፋፋት ይኖርባቸዋል ብለዋል፡፡ ከተማ አስተዳደሩ እነዚህን ዓይነት የልማት ሥራዎች አጠናክሮ ማስቀጠል እንዳለበት በመጠቆም፤ በቀጣይ የሚሠሩት ሥራዎች ከዚህም በላይ ስፋት ያላቸው፣ በርካታ ዜጎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ፣ ዘላቂነታቸውም በጥናት የተረጋገጠ መሆን እንደሚገባው አሳስበዋል፡፡

የአንድ መስኮት አገልግሎት የሚባሉ አሰራሮች በመላው አለም እየተለመዱ መጥተዋል የሚሉት ሞላ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ የአራት ኪሎ ፕሮጀክቶች ንግድ ያቀላጥፋሉ፡፡ ጊዜን ይቆጥባሉ፡፡ የስራ እድል ይፈጥራሉ፡፡ ሻጭና ገዥን በአንድ ያገናኛሉ፡፡ የኑሮ ደረጃን ያሻሽላሉ፡፡ ምክንያቱም ብዙ አገልግሎቶችን በአንድ የያዘ ማእከል ነው፡፡ ስለዚህ ከተማዋን ምቹ ከማድረግ በተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታውም ከፍተኛ ነውና ወደ ሌሎች ቦታዎች መስፋፋት እንዳለባቸው አብራርተዋል።

## የመዲናዋ... ከገጽ 8 የዞረ

መዲናዋ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የምታደርገው ጥረት በከተማ ግብርና ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ ምንም ዓይነት ስራ የሌላቸው፣ የዕለት ጉርሳቸውን ለመሸፈን የሚቸገሩና በከፋ ድህነት ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች በአካባቢ ልማት ተሰማርተው እየሰሩና መስራት የማይችሉ ደግሞ በቀጥታ ድጋፍ እየተደረገላቸው ከድህነት እንዲወጡ ለማስቻል በከተማ ደረጃ የምግብ ዋስትና ወይም የሴፍቲኔት መርሃ ግብር እየተተገበረ ይገኛል፡፡

በአዲስ አበባ ስራና ክህሎት ቢሮ የምግብ ዋስትናና ስራ ስምሪት ዘርፍ የምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት የህብረተሰብ ተሳትፎ ቡድን መሪ አቶ አብርሃም መልኬ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ መርሃ ግብሩ በ2009 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን በርካታ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ዜጎች ተጠቃሚ ሆነውበታል። በመጀመሪያውና በሁለተኛው ምዕራፍ የምግብ ዋስትና መርሃ ግብር በአጠቃላይ 674 ሺህ 397 የሚሆኑ ዜጎች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ተጠቃሚዎች በአካባቢ ልማት፣ ፅዳትና ውበት፣ በከተማ ግብርናና ተፋሰስ ልማት ላይ በመሳተፍ ለሶስት ዓመታት ከሰሩ በኋላ የሚመረቁበትና ከተረጂነት ወጥተው ራሳቸውን ችለው ለሌሎች ወገኖች የስራ ዕድል የሚፈጥሩበትን ሁኔታ የሚያመቻች ነው፡፡

### ምሁራን ምን ይላሉ?

የከተማ ግብርና በከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እምቅ አቅም ያለው ዘርፍ ነው፡፡ በዓለም ላይም በርካታ ከተሞች በምግብ ራሳቸውን ለመቻል በክፍት ቦታ ብቻ ሳይሆን በህንፃ ግድግዳዎችና ጣሪያዎች የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ይሰራሉ። በአዲስ አበባም የከተማዋን ነዋሪዎች በከተማ ግብርናና በሴፍቲኔት መርሃ ግብር በማሳተፍ የምግብ ዋስትናን ለማቃለል የሚደረገው ጥረት ተስፋ ሰጪ እንደሆነ የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት ትምህርት ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር አዳነ ቱፋ (ዶ/ር) እንዲሁ በአዲስ አበባ የከተማ ግብርናን በመተግበር እየተገኘ ያለው ውጤት ቀላል አይደለም ይላሉ፡፡ በከተማዋ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ ዜጎች የምግብ ፍጆታን በመሸፈን ብሎም የገቢ ምንጭና የስራ አማራጭ በመሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው ዘርፍ ነው፡፡

በከተማ ግብርና የሚገኘውን ውጤት ከዚህም በላይ ማሳደግ ይቻላል የሚሉት የምጣኔ ሀብት ምሁሩ አዳነ (ዶ/ር)፣ አትክልት፣ እንቁላል፣ ወተት፣ የስጋ ምርቶችን ማሳደግ ላይ በትኩረት መስራት ያስፈልጋል፡፡ ስራውን ለማከናወን የሚያስፈልገውን የውሃ አቅርቦት፣ መስሪያ ቦታ እና የተለያዩ ድጋፎችን ማመቻቸት ላይ የተጠናከረ ስራ መስራት እንደሚጠበቅ ተናግረዋል።

> “ከተማዋ በከተማ ግብርና ዘርፍ ያላትን አቅም አሟጥጦ ለመጠቀም ከመንግስት ባለፈ የግሉ ዘርፍ በተለይ የፋይናንስ ተቋማት ብድር በማቅረብ ድጋፍ የሚያደርጉበት ፖሊሲ መኖር አለበት”

ይህን ሀሳብ ሌላኛው የምጣኔ ሀብት ምሁር ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር) የሚጋሩት ሲሆን፣ በከተማ ግብርና የሚገኘውን ውጤት ለማሳደግ ክፍት ቦታዎችን መጠቀምና የህዝብ ተሳትፎን ማሳደግ እንደሚገባ ያነሳሉ፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ ወረዳ ወይም ሰፈር ውስጥ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚገኙ ሲሆን እነዚህ አካላት ሰብሰብ ብለው ወጣቶች ወደ ዘርፉ የሚገቡበት ሁኔታ ላይ ድጋፍ ቢያደርጉ በከተማ ግብርናው ዘርፍ ብዙ ለውጥ ማምጣት ይቻላል ብለዋል፡፡

ከዚህ ባሻገር የወንዝ ዳርቻዎችን ፅዱና ውብ ለማድረግ የሚሰራው ስራ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን ለመቋቋም ዕድል እንደሚፈጥር የምጣኔ ሀብት ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ወደ ወንዞች የሚለቀቁ ፍሳሾች ሲቆሙና ወንዞች ንፁህ እየሆኑ ሲመጡ ለከተማዋ የምግብ ዋስትና መሰረት ይሆናሉ፡፡ የወንዝ ዳርቻዎችን ከማስዋብ ባለፈ የከተማ ግብርና እንዲሰራባቸው በማድረግ፣ በደኖች ለምሳሌ እንጦጦ ጫካ ውስጥም ለምግብ የሚሆኑ የፍራፍሬና የተለያዩ ለምግብነት ሊውሉ የሚችሉ ዕፅዋትን በመትከል የከተማዋን የምግብ ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት ውጤታማ ማድረግ እንደሚቻል ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር) ያነሳሉ፡፡

ከተማዋ በከተማ ግብርና ዘርፍ ያላትን አቅም አሟጥጦ ለመጠቀም ከመንግስት ባለፈ የግሉ ዘርፍ በተለይ የፋይናንስ ተቋማት ብድር በማቅረብ ድጋፍ የሚያደርጉበት ፖሊሲ መኖር ወሳኝ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር የግብአትና ቁሳቁስ ድጋፍም ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ በእጅ እየተገፉ እንደ ትራክተር ማረስ የሚችሉ አነስተኛ ማሽኖችን (Tillers) የሚያገኙበት ሁኔታ መፍጠር እንደሚያስፈልግ የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ያክላሉ፡፡

በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ ዜጎችን በከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት በማቀፍ የሚደረገው ድጋፍ የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ የሚያስችል እንደሆነ ያነሱት የምጣኔ ሀብት ምሁሩ አዳነ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ የመርሃ ግብሩ ተጠቃሚዎች በብዛት ምርታማነትንና አቅርቦትን የሚያሳድጉ ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ በማድረግ የምግብ ዋስትና ችግርን ማቃለል እንደሚቻል አመላክተዋል፡፡

አዳነ (ዶ/ር) እንደሚገልፁት፣ የግብርና ምርት ማከማቻና መሸጫ ማዕከላት ተገንብተው ስራ መጀመራቸው አምራችና ሸማቹን በማገናኘት የከተማው ነዋሪ የግብርና ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት እንዲችል ያግዛሉ፡፡ በእሁድና ቅዳሜ ገበያዎችም አምራቾች እንደ ጎመን፣ ቲማቲም፣ አቦካዶ፣ ማንጎ፣ ሽንኩርት፣ ድንች ያሉ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን የሚያቀርቡ ሲሆን ይህም ሸማቹ በተመጣጣኝ ዋጋ ምርቶቹን እንዲያገኝ በማስቻል የምግብ ዋጋን በማረጋጋት ከፍተኛ ጥቅም እንደሚኖረው ጠቁመዋል፡፡

## በትጋትና ... ከገጽ 11 የዞረ

መስሪያ ቤቶች የመስራት እድል አገኘ። እንደ አሜሪካ የምግብና የመድኃኒት ባለስልጣን፣ የፌዴራል አቪዬሽን ባለስልጣን፣ የአሜሪካ የባህር ኃይል፣ ናሳ፣ ፔንታጎን (የአሜሪካ መከላከያ መስሪያ ቤት) ጨምሮ በተለያዩ የፌዴራል መስሪያ ቤቶች በሙያው መስራቱን ቀጠለ፡፡

ከተለያዩ የግል ካምፓኒዎች እስከ ትላልቅ የመንግስት ተቋማት ድረስ በመስራቱ ያካበተውን ልምድና ተሞክሮ በመያዝ የአሜሪካ የምርምር ተቋም ወደሆነው ናሳ የመግባቱን እድል አገኘ። ያልተገደበ ጥረት ለትልቅ ስኬት እንደሚያበቃ ማሳያ የሆነው የአይ ቲ ባለሙያና ጋዜጠኛ ደረጀ፣ በአሁኑ ወቅት በናሳ ሲኒየር የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አርክቴክት ሆኖ እያገለገለ ይገኛል። በናሳ ውስጥ የስራ ድርሻው የተለያዩ መተግበሪያዎችን (አፕሊኬሽኖች) መገንባት፣ ፕሮጀክቶችን መቆጣጠርና መምራት ነው፡፡

ከዚህ በተጓዳኝ ከዛሬ አምስት ዓመታት ወዲህ ሀሴት አይቲ ሶሉሽን (Haset IT Solutions) የሚል ስያሜ የሰጠውን የግሉን የአይቲ ማሰልጠኛ፣ ማማከሪያ እና ሶፍትዌር ማበልፀጊያ ተቋም አቋቁሟል፡፡ በተቋሙ ሰልጣኞች የተለያዩ መተግበሪያዎች እንዴት መስራት እንዳለባቸው እና ራሳቸውን እንዴት መግለጽ እንደሚችሉ የማሰልጠንና የማማከር ስራ ሰርቷል፤ በመሰራት ላይም ይገኛል፡፡ እስከ አሁንም ከ3 ሺህ በላይ ተማሪዎችን አሰልጥኗል፡፡ በሀሴት አይቲ ሶሉሽን ያሰለጠናቸው ተማሪዎችም በተለያዩ የአሜሪካ የፌዴራል መስሪያ ቤቶች ለምሳሌ ኮንግረስ፤ ኋይት ሀውስና ናሳን ጨምሮ እንዲቀጠሩ እድል ፈጥሮላቸዋል፡፡ የሰው ልጅ ‘አይሆንም፤ አይቻልም’ የሚል አሉታዊ አስተሳሰብን መታገልና መቋቋም ይኖርበታል፡፡ ‘አትችልም፤ አትሞክረው’ ሲሉት የነበሩ ግለሰቦች የሀሴት አይቲ ሶሉሽን 7ኛ ዙር ሰልጣኝ ሆነው መምጣታቸውንም አልሸሸገም፡፡

### ቀጣይ እቅድ

የወደፊት እቅዱ አሜሪካ ላይ የጀመረውን ስራ ወደ ሀገሩ ማምጣት ነው። በአሁኑ ወቅት ለኢትዮጵያ ሁለንተናዊ እድገት ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የላቀ ድርሻ እንዳለው ያምናል። በተለይም ሀገሪቱ የምጣኔ ሀብቷን ለማሳደግና የተለያዩ የልማት ግቦችን ለማስፈጸም ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ግንባር ቀደም ሚና እንደሚወጣ የተረዳው የአይቲ ባለሙያው ደረጀ፣ “በተለይም የኢንተርኔት ግብይት (E-Commerce)፣ ዌብ አፕልኬሽኖች፤ የኢንተርኔት መረጃ ደኅንነት (Cyber Security) እና ሌሎች ከሰው ሰራሽ አስተውሎት (Artificial Intelligence) ጋር የተያያዙ ስራዎችን ኢትዮጵያ ውስጥ ለመስራት በዝግጅት ላይ ነኝ” ብሏል፡፡

በተለይም የሰው ሰራሽ አስተውሎት በተለያዩ ዘርፎች ምርታማነትን ለማሳደግ፣ ጊዜን እና ወጪን ለመቆጠብ፣ አስቸጋሪ እና ውስብስብ የሆኑ ስራዎችን ለመከወን እንዲሁም የስራ ጫናን ለመቀነስ እጅግ ጠቃሚ መሆኑን ገልጿል፡፡

ኢትዮጵያ ላይ የአይቲ ፓርክ እና ሳይንስ ሙዚየም መቋቋማቸው በዘርፉ ብዙ መስራት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መኖሩን ይናገራል፡፡ በቅርቡም የራሱን የአይቲ ማሰልጠኛ ተቋም ለማስተዋወቅና በዘርፉ ፍላጎት ያላቸው ኢትዮጵያውያንን ካሉበት ሆነው መማር እንዲችሉ በኦንላይን በተግባር የተደገፈ ስልጠና ለመስጠት ዝግጅቱን አጠናቅቋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሰዎች በአካል መገኘት ሳይኖርባቸው በቴክኖሎጂ ታግዘው በኦንላይን እንዲማሩ የሚያደርግ ኤል ኤም ኤስ (Learning Management System - LMS) ሶፍትዌር ለመገንባት በዝግጅት ላይ መሆኑን ገልጾልናል፡፡

### ባለሙያው በቀድሞ የስራ ባልደረቦቹ አንደበት

የአዲስ አውቶሞቲቭ የሬዲዮ ዋና አዘጋጅ እና የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዜና አንባቢ ጋዜጠኛ ሰለሞን ጥዑመልሳን በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ከሪፖርተርነት እስከ ጥናትና ምርምር የስራ ክፍል ኃላፊ በመሆን አገልግሏል፡፡ ጋዜጠኛና የአይቲ ባለሙያ ደረጀ ተድላን አዲስ ዘመን ጋዜጣ የስፖርት አምድ አዘጋጅ ሆኖ ሲያገለግል እንደሚያውቀው ይናገራል፡፡ በወቅቱ ጎበዝና ፈጣን ከመሆኑም ባለፈ ስለሚሰራው ስራ ብቻ ሳይሆን ስለብዙ ነገር የማወቅ ጉጉት ያለው ሰው ነው በማለትም ስለስራ ወዳድነቱ እና አዲስ ነገር የማወቅ ጉጉቱ አብራርቶልናል፡፡

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ጋዜጠኛ መለሰ ነጋሽም በተመሳሳይ ጋዜጠኛና የአይቲ ባለሙያው ደረጀን የሚያውቀው በ1998 ዓ.ም በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ባልደረባ ሆኖ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ “በተቋሙ በነበረው ቆይታ ትጉህ ሰራተኛ ነበር። ከዚያ በኋላም ወደ ጃፓን ሄደ። በጃፓን ብዙም ሳይቆይ ወደ አሜሪካ በመሄድ ናሳን በሚያክል ተቋም ላይ ለመስራት በቅቷል፤ ፔንታጎን ሰርቷል፤ በሌሎች ተቋማት ላይም ሰርቷል። ደረጀ አሁን የአይቲ ባለሙያ ነው። እጅግ ስኬታማ ከሚባሉት አሜሪካ-ኢትዮጵያውያን መካከል አንዱ ነው። ለዚህ የበቃው ደግሞ በትጋቱና በንባብ ነው። ለሁላችንም አርአያ መሆን የሚችል ሰው ነው” ሲል ገልጾታል፡፡

### እንደ ማጠቃለያ

ጊዜው የቴክኖሎጂ ነው፡፡ ወደፊት የዕለት ተዕለት ተግባራት ያለ ቴክኖሎጂ የማይከናወንበት ጊዜ ሊመጣ ይችላል። ለምሳሌ አሜሪካ ሀገር ውስጥ ያለ ሰው በቴክኖሎጂ ብቻ የሚንቀሳቀስ መኪና አለ፡፡ ሰዎች የሌሉበት የእቃ መሸጫ ሱቆች አሉ፡፡ እቃ ገዝተን ብር ካልከፈልን በር አይከፈትም፡፡ ያለ አስተናጋጅ ሬስቶራንት ውስጥ ገብቶ የሚፈልገውን አዝዞ ተጠቅሞ የሚወጣበት አለ፡፡ ከአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ፤ ከሮቦቲክስ፤ ከአውቶሜሽን እና ከሳይበር ሴኩሪቲ ጋር በተገናኘ ብዙ የአይቲ ስራዎች ይመጣሉ፡፡ እነዚህ ቴክኖሎጂዎች ማንዋል የሆነውን አሰራር ያስቀራሉ፡፡ ስለዚህ ሰዎች ራሳቸውን ከቴክኖሎጂ ጋር ማዛመድ ይኖርባቸዋል ሲል ደረጀ ሀሳቡን ቋጭቷል፡፡

## የጨረታ ቁጥር 001/2018

## የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

**በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 አስተዳደር እና ፋይናንስ ጽ/ቤት የ2018 በጀት ዓመት የ1ኛ ዙር ግዥ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል በመሆኑም ከታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የምታሟሉ ተጫራቾች እንድትወዳደሩ እያሳወቅን።**

| ተ.ቁ | የእቃው አይነት | የሎት አይነት | የጨረታ ማስከበሪያ ብር መጠን |
|---|---|---|---|
| 1 | ስቴሽነሪ እና ቶነሮች | ሎት 1 | 35,000 ብር |
| 2 | የፅዳት እቃዎች | ሎት2 | 40,000 ብር |
| 3 | የቢሮ መገልገያ መሳሪያዎች | ሎት3 | 5,000 ብር |
| 4 | የደንብ ልብስ | ሎት4 | 35,000 ብር |
| 5 | የመስተንግዶ አቅርቦት | ሎት 5 | 8,000 ብር |
| 6 | የትራንስፖርት አገልግሎት | ሎት 6 | 5,000 ብር |
| 7 | የህትመት አገልግሎት | ሎት 7 | 15,000 ብር |
| 8 | የኤሌክትሮኒክስ ጥገና አገልግሎት | ሎት 8 | 4,000 ብር |
| 9 | የመድረክ እቃዎች ኪራይ አገልግሎት | ሎት 9 | 8,000 ብር |

1. በጨረታ ለመወዳደር የሚፈልጉ ተጫራቾች በዘመኑ ህጋዊ የሆነ የታደሰ የንግድ ፍቃድ፣ ቲን ነምበር ያለው እና የቫት ተመዝጋቢ የሆነ እና መረጃ ማቅረብ አለበት፡፡
2. በጨረታው የሚወዳደሩ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ በየሎቱ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
3. ተጫራቾች በጨረታው ለመሳተፍ የሚያስችል በአቅራቢዎች ዝርዝር የተመዘገቡ ለመሆኑ ማስረጃ ከሰነዱ ጋር ማቅረብ የሚችል፡፡
4. ተጫራቾች ለሚወዳደሩበት እቃ ጫረታው ከመከፈቱ በፊት ናሙና ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. ተጫራቾች ዋጋ ሲሞሉ ስርዝ ድልዝ ቢፈጠር ከፊት ለፊቱ ፊርማ ሊኖረው ይገባል አለበለዚያ የተሞላው ዋጋ ተቀባይነት የለውም፡፡
6. የጨረታ ሰነዱ አንዱ የጨረታ መመሪያ መሆኑን ተጫራቾች ሊረዱት የሚገባ ሲሆን በጨረታ ሰነዱ ላይ ያልተካተቱ ችግሮች ቢያጋጥሙን በግዥ መመሪያው መሰረት የሚዳኝ ይሆናል፡፡
7. ጨረታውን ለማወዳደር የእቃ ጥራት የዋጋ ዝቅተኝነት ወ.ዘ.ተ ግምት ውስጥ የምናስገባ ይሆናል፡፡
8. ጨረታውን ለማዛባት ወይም እንቅፋት ለመፍጠር የሚሞክሩ ተጫራቾች ከጨረታ ውጪ የሚሆኑ ሲሆን ወደፊትም በመንግስት ግዥ መመሪያ መሰረት በህግ እንዲከሰሱ ይደረጋል፡፡
9. ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ተጫራቾች ባቀረቡት የመወዳደሪያ ዋጋ ለውጥ ማሻሻያ ማድረግና ራሳቸውን ማግለል አይችሉም፡፡ እንዲሁም ከስፔስፊኬሽን ወይም ካቀረቡት ናሙና ውጭ ማቅረብ አይችሉም፡፡
10. ጨረታው በሁለት ኢንቨሎፕ የሚቀርብ ሆኖ ኦርጂናል እና ኮፒ የጨረታ ሰነድ የሚል ጽሁፍ እንዲሁም ሙሉ የጨረታ ሰነዱ ኮፒ ተደርጎ በአቅራቢው ድርጅት ማህተም ተረጋግጦ ተመላሽ መሆን ይገባል፡፡
11. ጨረታው ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የስራ ቀናት ክፍት ሆኖ የሚቆይ ይሆናል፡፡
12. ተጫራቾች መጫረቻ ሰነዶችን ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ እስከ 10ኛው ቀን ድረስ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ ጨረታው በ10ኛው ቀን 11፡00 ሰዓት የሚታሸግ ሲሆን ቀጣዩ ቀን የስራ ቀን ከሆነ ጠዋት 3፡30 ሰዓት ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ቢገኙም ባይገኙም የሚከፈትና የሚለይ ይሆናል፡፡
13. የመወዳደሪያ ሰነዱን ቦ/ክ/ከ/ወ/13/ አስተዳደር እና ፋይናንስ 4ኛ ፎቅ በመቅረብ የአንድ ሎት ዋጋ የማይመለስ 300 (ሶስት መቶ) ብር በመክፈል መግዛት ይችላሉ፡፡
14. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉበትን ጠቅላላ ዋጋ 10% የውል ማስከበሪያ በማስያዝ ውል መያዝ አለባቸው። በተጨማሪም ውሉን ከተዋዋሉ በኃላ እቃውን በ10 ቀናት ውስጥ በአስተዳደሩ ግቢ ውስጥ ባለው ንብረት ክፍል አጠናቀው ማስገባት ይኖርባቸዋል።
15. ጽ/ቤቱ 20% መጨመር ወይም 20% መቀነስ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ማሳሰቢያ** የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ፡-** ገርጂ ታክሲ ተራ ወረዳ 13 አስተዳደርና ፋይናንስ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 41 በአካል በመቅረብ ወይም በስልክ ቁጥር፡- 0118931655 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤት**

አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት/መላከ ገነት ዮሐንስ አምባው የተባሉት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየካ ክ/ከተማ በቀድሞ ወረዳ 12 በቀድሞ ቀበሌ 11 በአዲሱ ወረዳ 02 የሚገኘው ቤትና ይዞታ በካርታ ቁጥር የካ154/179072/05 በሴሪ ቁጥር 035038 የሆነ በአቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት መላከ ገነት ዮሐንስ አምባው ስም በቀን 15/09/05 ዓ.ም ተመዝግቦ የተሰጣቸወ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የጠፋባቸው ስለሆነ በማናቸውም ምክንያት አግኝቸዋለሁ (ይዤዋለሁ) የሚል አካል (ሰው) ካለ እስከ 30 ቀን ድረስ በየካ ክ/ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት የይዞታ አገልግሎት ቡድን ድረስ እንዲቀርቡ ካልቀረቡ ግን በምትኩ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት (ካርታ) የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በከበደሽ ፃድቅ ደመቀ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 11 የሚገኘው በይዞታ ካርታ ቁጥር AA00008I106554 በሴሪ ቁጥሩ 047325 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው በደስታ ልየው አስረስ ስም በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር DE-B18/029 ሴሪ ቁጥር C 008456 መለያ ቁጥር AA000030900030/A፣ እና የቤት ቁጥር DE-B18/032 ሴሪ ቁጥር C 008457 መለያ ቁጥር AA000030900030/A የተመዘገበ ሁለት ካርታዎች ጠፋብኝ ብለው በቀን 21/11/2017 ዓ.ም በማመልከቻ የጠየቁ ስለሆነ፣ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳዩ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ ኦርጅናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

አለምሰገድ ገ/ዮሐንስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 በሴሪ ቁጥር C 012488 በካርታ ቁጥር አ/06/01/2774 የሆነው እና በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ (ይዤዋለሁ) የሚል ሰው ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 90 ቀን ድረስ በጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአራዳ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 ገላን 3 ውስጥ በካርታ ቁጥር 43685 በሴሪ ቁጥር 094756 በአቶ ታሪኩ ሀይሉ የተመዘገበ ይዞታ ከማህደር ክፍላችን ከማህደር ውስጥ ቀሪ ካርታ የጠፋባቸው ስለሆነ ማህደሩን የያዘ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ መጥተው ካላሳወቁ ማህደር በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

አመልካች ከበበው ደምሴ የህና ሀብታሙ ህጋዊ ወኪል በቀን 16/11/2017 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት የካርታ ቁጥር ቦሌ10-1/53/7/1/31906/00 ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የጠፋብኝ ስለሆነ በምትኩ እንዲሰጠኝ በማለት በህና ሀብታሙ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ ጣቢያ እና ለአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እንዲፃፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ወረዳ 04 የሆነው ይዞታ መኖሪያ ቤት በህና ሀብታሙ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የካርታ ቁጥር ቦሌ10-1/53/7/1/31906/00 ሴሪ ቁጥር 013935 የተሰጠበት ቀን 24/10/2017 ዓ.ም የቤቱ ስፋት በሰነድ 150 ካ.ሜ የቦታው አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነው ቤት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የጠፋ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ አስዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት ጥሪ የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ማህደሩን የምናደራጅ እና ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦሌDU/7096/50161/01 ሴሪ ቁጥር 1413456 በየሺወርቅ ገ/ፃድቅ ኃይሌ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የኮንዶሚንየም ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

አቶ ወንደወሰን ፋንታ ደምሴ ስም የተመዘገበ ይዞታ የካርታ ቁጥር ሊዝ16/7004/00/7213 ሴሪ ቁጥር 7199 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በእኛ ተቋም የተሰጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ይሁንና አቶ ወንደወሰን ፋንታ ደምሴ ስም የተመዘገበ ይዞታ የካርታ ቁጥር ሊዝ16/7004/00/7213 ሴሪ ቁጥር 7199 የተሰጠበት ቀን 18/2/98 ዓ.ም የቤቱ ወለል ስፋት 518 ሜ.ካ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ ካርታ የጠፋ ስለሆነ ይዞታ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሰውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# የግልጽ የግዥ ጨረታ ማስታወቂያ

## የግዥ ጨረታ መለያ ቁጥር 001/2018ዓ.ም

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 4 ፋይናንስ ጽ/ቤት የ2018 በጀት ዓመት የ1ኛ ዙር ጥቅል ግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል። ስለሆነም ከዚህ በታች የተዘረዘሩ መስፈርቶችን የምታሟሉ ተጫራቾች እንድትወዳደሩ እያሳወቅን ።**

**የእቃው አይነት** | **የጨረታ ማስረከብያ በኢ.ት.ዮ ብር**

ሎት1. የእስቴሽነሪ እቃዎች -------------------------------------15000 ብር
ሎት2. የፅዳት እቃዎች -----------------------------------------25000 ብር
ሎት3. ደንብ ልብስ ----------------------------------------------30000 ብር
ሎት4. የህትመት አገልግሎቶች-------------------------------------5000 ብር
ሎት5. የኤሌክትሮኒክስ ጥገና አገልግሎቶች -----------------------5000 ብር
ሎት6. የትራንስፖርት አገልግሎቶች--------------------------------10000 ብር
ሎት7. የመስተንግዶ አገልግሎቶች----------------------------------5000 ብር
ሎት8. የተለያዩ ኪራይ አገልግሎቶች--------------------------------5000 ብር

1. ተጫራቾች በዘርፉ የተሰማሩበት የታደሰ ህጋዊ ፍቃድ ያላቸው እና የዘመኑን ግብር ለመከፈላቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ።
2. የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያለው፡፡
3. የአቅራቢነት ዝርዝር ውስጥ ተመዝጋቢ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ኮፒ ከሰነዱ ጋር ማቅረብ የሚችል፡፡
4. ለሚያቀርቡት እቃ የጥራት ደረጃውን የሚገልጽ ስልጣን ከተሰጠው አካል የተረጋገጠ ማስረጃ ኮፒ ከሰነዱ ጋር ማቅረብ የሚችል፡፡
5. ተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፡፡
6. ተጫራቾች ከዚህ በታች የተጠቀሰው የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ CPO ማቅረብ አለባቸው።
7. የጨረታ ሰነዱን ማስታውቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በየዕለቱ የማይመለስ ብር 300.00 ( ሶስት መቶ ብር) በመከፈል ሰነድ ከተቋሙ ቢሮ ቁጥር 305 እየቀረቡ መግዛት ይቻላል፡፡
8. ተጫራቾች ጨረታ ከወጣበት ቀን አንስቶ ባሉት 10 (አስር ) ተከታታይ የስራ ቀናት ቢሮ ቁጥር 305 ድረስ በመምጣት ዋጋው የተሞላበትን የጨረታ ሰነዱን ዋናውንና ፎቶ ኮፒ ለብቻው በማሸግ ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
9. ጨረታው በ10ኛው ቀን በ11፡ 00 ሰዓት ታሽጎ በሚቀጥለው ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ የጨረታው መዝጊያና መክፈቻ የስራ ቀናት ካልሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተጠቀሰው ተመሳሳይ ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
10. ተጫራቾች ያሸነፉበትን ዋና የውል ማስረከብያ 10% ማስያዝ አለባቸው ፡፡
11. ተጫራቾች ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ለሚወዳደሩበት ናሙና ለሚቀርብባቸው እቃዎች ናሙና ማቅረብ አለባቸው ናሙና የማይቀርብባቸው ቋሚ እቃዎች መስሪያ ቤቱ ባቀረበው ስፔስፊኬሽን መሰረት ወይንም /በፎቶ/ ማቅረብ አለባቸው ፡፡
12. የጨረታ አሸናፊ ድርጅት ያሸነፈበትን እቃ በራሱ ትራንስፖርት ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 4 ድረስ ማቅረብ ይኖርበታል ፡፡
13. መስሪያ ቤቱ ለጨረታ ከቀረበው እቃ እስከ 20% የመቀነስም ሆነ የመጨመር መብቱ የተጠበቀ ነው።
14. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
15. ተጫራቾች ዋጋ ሲሞሉ ስርዝ ድልዝ ቢፈጠር ከፊት ለፊት ፊርማቸውን ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል። ይህ ካልሆነ ግን የተሞላው ዋጋ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
16. የጨረታ ሰነዱ አንዱ የጨረታ መመሪያ መሆኑን ተጫራቾች ሊረዱት የሚገባ ሲሆን ኦርጅናል የጨረታ ሰነዱ የድርጅቱን ማህተም በማድረግ ማስገባት/መመለስ/ ይኖርባቸዋል። ነገር ግን በጨረታ ሰነዱ ያልተካተቱ ችግሮች ቢያጋጥሙ በግዥ መመሪያ መሰረት የሚዳኝ ይሆናል፡፡
17. የሚሞላው ዋጋ ቫትን ያካተተ መሆን አለበት ፡፡
18. ጨረታውን ለመወዳደር የእቃ ጥራት እና የዋጋ ዝቅተኛነት ግምት ውስጥ የምናስገባ ይሆናል፡፡
19. የጨረታ ሂደቱን ለማዛባት ወይንም እንቅፋት ለመፍጠር የሚሞክር ከጨረታ ውጭ ይደረጋል፡፡
20. ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ተጫራቾች ባቀረቡት የመወዳደሪያ ዋጋ ለውጥ ወይንም ማሻሻያ ማድረግ እና እራሳቸውን ማግለል አይችሉም፡፡ እንዲሁም ለአንድ እቃ ለሚቀርበው ናሙና ተለዋጭ ናሙና ማቅረብ አይቻልም፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ ፡-**ፕላዛ ሆቴል 100 ሜትር ወደ ውስጥ ገባ ብሎ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 04 አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤት 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 305 በአካል በመቅረብ ወይንም በስልክ ቁጥር 0118538953 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ ፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ አስተዳደር ወረዳ 04 ፋይናንስ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ በለጥሻቸው ወርቁ አስፋው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ካርታ ቁጥር ቦሌ 2/33/7/2/2422/00 ሴሪ ቁጥር 018955 የሆነ ይዞታ/የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ጉዳዩ፡- የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በወረዳ 02 በ ሪሃና መስፍን አንዱ ስም የተመዘገበ የይዞታው ካርታ ቁጥር የካ/1/8/22/165323/00 የተሰጠበት ቀን 09/01/2017 ዓ.ም እና በሴሪ ቁጥር 1688222 የሆነ የሙብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር የካ/ፖ/መወ/07/8037/17 በቀን 10/04/2017 ዓ.ም የሚገልፅ መረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም ሙብት አለኝ ባይ በ30 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች በምትክ ሰርተፊኬት የሚሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 09 ክልል ውስጥ በአቶ በፍቃዱ ሀይለማርያም ገብረየስ ስም በልዩ መለያ ቁጥር AA000070900300130426 በሆነ የተመዘገበው የጋራ መኖሪያ ቤት ፤ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/የመሬት ይዞታ ሙብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቱ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጄ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ ሙብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በሀጂ ጀማል ቡራዩ ቱሉ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 የሚገኘው በይዞታ ካርታ ቁጥር AA000080116204 በሴሪ ቁጥሩ 0159361 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ሳሙኤል ማንያዘዋል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 የካርታ ቁጥር ቦሌ 10/82/1706/00 ሴሪ ቁጥር 072509 የሆነው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው አናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ሀብተማርያም በላይ መንግስቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የ ይዞታ መለያ ቁጥር AA000061007346454O425 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በካሰች ጉልማ ጋሪ ስም የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000080122413 የሴሪ ቁጥር 091709 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ኮፒ(ካርታ) እና ማህደሩ ከመዝገብ ቤት ስለጠፋ በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 15 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ማህደር አደራጅተን ተለዋጭ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት /ካርታ/ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቶ ደመላሽ አበበ ቱጂ ስም በልደታ ክ/ከተማ አዲሱ ወረዳ 04 የቀድሞ ወረዳ 04 ቀበሌ 29 የቤት ቁጥር 063 በቀን 02/02/1976 ዓ.ም፣ በካርታ ቁጥር 19226 የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ ታውጀ አገልግሎት እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳዩች ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጂናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ ሙብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ ሙብት ማረጋጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 08 የካርታ ቁጥር የካ/214275/11 በሴሪ ቁጥር 0644484 በአስጨናቂ ሀይሌ ስም ያለውን ይዞታ አስመልክቶ ይህን ይዞታ በእዳ እገዳ ይዤዋለሁ የሚል ተቋምም ሆነ ግለሰብ ወይም ይዞታው ላይ የይገባኛል ጥያቄ ያለው አካል ካለ በ30 (ሰላሳ) ቀን ውስጥ በየካ ክ/ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት ቀርቦ ካርታቸውን እንዲያስረክበን እንጠይቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# የተጫዋቾች ዝውውር ከሌላ ማዕዘን

በሳህሉ ብርሃኑ




ፎቶ ገፀ ድር

የ2025 የክረምት የዝውውር መስኮት ከፍተኛ የገንዘብ እንቅስቃሴዎችን አስተናግዷል

በዘመናዊው የእግር ኳስ ዓለም የክለቦች የገቢ ምንጭ ስፖንሰርሺፕ፣ የቴሌቪዥን መብት ሽያጭ እና የቲኬት ገቢ ብቻ አይደለም። የዝውውር ገበያው እጅግ ትልቅ ገንዘብ የሚንቀሳቀስበት ኢንዱስትሪ ከሆነ ወዲህ በርካታ ክለቦች ተጫዋቾችን ማፍራት፣ ማሳደግ እና ውድ በሆነ ዋጋ መሸጥን እንደ ስኬታማ የገቢ ማግኛ ስትራቴጂ መጠቀም ከጀመሩ ሰነባብተዋል። በተለይም ጠንካራ የአዳጊዎች አካዳሚ ያላቸው ወይም ጥብቅ የፋይናንስ ደንቦች የሚገድባቸው ክለቦች ይህንን አማራጭ በስፋት ሲጠቀሙ ይስተዋላል።

በዚህ ጽሑፍም ያልተጠበቁ ክስተቶችን እያስመለከተ ያለውን የ2025 የክረምት ወቅት የአውሮፓ እግር ኳስ ተጫዋቾች ዝውውርን መነሻ አድርገን የእግር ኳስ ሽያጭን እንደ ገቢ ምንጭ እየተጠቀሙ ያሉ የእግር ኳስ ክለቦችን እንቃኛለን። የተለያዩ የእግር ኳስ ክለቦችን በማጣቀሻነት በማውሳት እንዲህ አይነቱ ስትራቴጂ ያለውን እግር ኳሳዊ ፋይዳና ተያያዥ ጉዳዮችን ለመፈተሽ ወደድን፡፡

የእግር ኳስ ተጫዋቾች የዝውውር መስኮት ሁሌም ቢሆን ድራማዊ እና አስገራሚ ክስተቶች የሚስተናገድበት ጊዜ ነው። የ2025 የክረምት የዝውውር መስኮት ደግሞ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ብዙ ያልተጠበቁ ክስተቶችን እና ከፍተኛ የገንዘብ እንቅስቃሴዎችን አስተናግዷል። የዚህ መስኮት ዋና ዋና ገጽታዎች የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ ክለቦች ከፍተኛ የገንዘብ ወጪ፣ የሳውዲ ሊግ ተጽዕኖ መጨመር እና ታዋቂ ተጫዋቾች ወደ አውሮፓ መመለሳቸው ከተስተዋሉ ክስተቶች መካከል ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የዝውውር ገበያ ባለሙያው ጋዜጠኛ ዴቪድ ኦርንስቴይን አስተያየት ተጫዋቾችን መሸጥ በዘመናዊ እግር ኳስ ውስጥ የክለቦች የፋይናንስ አቅም እና የስፖርት ስኬት ወሳኝ አካል መሆኑን ያሳያል። ይህ አዝማሚያ ወደፊትም ይቀጥላል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን፣ ይህም የዝውውር ገበያውን ይበልጥ ተለዋዋጭ እና አስደናቂ ያደርገዋል። የ2025 የክረምት የዝውውር መስኮት በእግር ኳስ ዓለም ላይ በርካታ የረጅም ጊዜ ተጽዕኖዎችን የሚያሳድር እንደሚሆን ይጠበቃል ይላል ጋዜጠኛው።

ዓለም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ክለቦች ወጣት እና ተስፋ ያላቸው ተጫዋቾችን በዝቅተኛ ዋጋ በማምጣት፣ ከፍተኛ ልምድ እንዲያገኙ በማድረግ እና ዋጋቸው ሲጨምር መሸጥ እየተለመደ መጥቷል። ለዚህ ማሳያ ከሆኑ የእግር ኳስ ክለቦች መካከል እንደ ጀርመኑ ቦርሺያ ዶርቱመንድ ባሉ ክለቦች ጁድ ቤሊንግሃም፣ ኤርሊንግ ሃላንድ፣ ኡስማን ደምቤሌ እና ጃዶን ሳንቾ ለክለቡ ከፍተኛ የገቢ ምንጭ የሆኑ ኮከቦች ናቸው። በፈረንሳይ ሊግ እንደዚሁ ሞናኮ እንደ ኪሊያን ምባፔ፣ በርናርዶ ሲልቫ እና ፋቢንሆ የመሳሰሉትን ኮከቦች ከዚህ ቀደም በመሸጥ ከፍተኛ ገቢ አግኝቷል።

የፖርቹጋል ሊግ ክለቦች በተለይም ቤንፊካ እና ፖርቶ ተጫዋቾችን በማሰልጠን እና ውድ በሆነ ዋጋ በመሸጥ የሚታወቁ ክለቦች ናቸው። ቤንፊካ በቅርብ አስርት ዓመታት ከተጫዋቾች ሽያጭ ከፍተኛ ገቢ ካገኙ ክለቦች ቀዳሚው ነው። እንደ ጆአኦ ፌሊክስ፣ ኤንዞ ፈርናንዴዝ፣ ዳርዊን ኑኔዝ፣ ሩበን ዲያስ እና ኤደርሰን የመሳሰሉ ተጫዋቾችን በከፍተኛ ገንዘብ በመሸጥ ትልቅ ትርፍ አግኝተዋል። እንደ ቤንፊካ ሁሉ ፖርቶም ተጫዋቾችን በአዳጊነታቸው በመግዛት፣ በማሳደግ እና በከፍተኛ ዋጋ በመሸጥ ረገድ ከፍተኛ ስኬት ስለማስመዝገባቸው የዘ አትሌቲክስ ዘገባ ያሳያል።

ዘ አትሌቲክስን ዋቢ አድርገን ስንቀጥል የምናገኘው ሌላኛው መረጃ የኔዘርላንድስ ሊግን ሲሆን፣ የሊጉ ክለቦችም ወጣት ተሰጥኦዎችን በማፍራት እና በመሸጥ የሚታወቁ ሆነው እናገኛቸዋለን። የአያክስ እግር ኳስ ክለብም ለረጅም ጊዜ የታወቀ የእግር ኳስ ተሰጥኦዎች ቤት ነው እስከመባልም ደርሷል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥም እንደ አንቶኒ፣ ፍሬንኪ ዲ ዮንግ፣ ማቲያስ ደ ሊክት እና ጁሪያን ቲምበር ያሉ ተጫዋቾችን በከፍተኛ ገንዘብ በመሸጥ ገቢ አግኝቷል።

ምንም እንኳን እንደ እንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ እና የስፔን ላሊጋ ክለቦች በአብዛኛው ተጫዋቾችን የሚገዙ ቢሆኑም፣ አንዳንድ ጊዜ ትርፋማ የሆኑ ሽያጮችን ያከናውናሉ፡፡ በተለይም በአካዳሚዎቻቸው ያሳደጓቸውን ወጣቶችን በማዘዋወር ለዚህ ማሳያ የሚሆነው ቼልሲ የእግር ኳስ ክለብ ሲሆን፣ እጅግ ከፍተኛ ገንዘብ አውጥቶ ተጫዋቾችን የሚገዛ ቢሆንም፣ የራሱን ጠንካራ አካዳሚ በመጠቀም ሜሰን ማውንት፣ ታሚ አብርሃም እና ፊካዮ ቶሞሪ የመሳሰሉ ተጫዋቾችን በመሸጥ ከፍተኛ ገቢ አስገብቷል። ይህን ደግሞ የፋይናንስ ፍትሐዊ የጨዋታ (FFP) ህጎችን ለማሟላት እና ገቢ ለማግኘት ጭምር ተጠቅመውበታል። የስፔኑ አትሌቲኮ ማድሪድም እንደዚሁ አንቷን ግሪዝማን እና ጆአኦ ፌሊክስ የመሳሰሉ ተጫዋቾችን በመሸጥ ከፍተኛ ገቢ አስገብቷል።

እዚህ ጋር ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ ታዲያ እነዚህ የእግር ኳስ ክለቦች ለምን ተጫዋቾችን መሸጥ ላይ ትኩረታቸውን አደረጉ? የሚለው ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ደግሞ የቴሌ ግራፍ ጋዜጠኛው ማት ላው ምላሽ አለው፡፡ ጋዜጠኛው እንደሚለው ክለቦች ተጫዋቾችን እንደ ገቢ ምንጭ የሚጠቀሙባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል ከተጫዋቾች ሽያጭ የሚገኘው ገቢ የክለቡን የፋይናንስ ሁኔታ ለማረጋጋት፣ ዕዳ ለመክፈል እና በፋይናንስ ፍትሐዊ የጨዋታ ህጎች ስር ለመቆየት ይረዳል። እንደዚሁም የተጫዋቾች ሽያጭ ከወጣበት አካዳሚዎች ለሚወጡ ተጫዋቾች የልማት ፕሮግራሞችን ለማስፋፋት እንደሚያግዝና ከሽያጭ የሚገኘው ገንዘብም አዲስና ተፈላጊ ተጫዋቾችን ለመግዛት በማስቻል ቡድኑን ለማደስ እና ስልታዊ ለውጦችን ለማድረግ ያግዛል።

የተጫዋቾች ዝውውር ተንታኙ ሮማን ግራሃም በበኩሉ በጉዳዩ ላይ ማርካ ላይ ባሰፈረው ጽሑፍ ተጫዋቾችን በከፍተኛ ዋጋ መሸጥ ለክለቦች ትልቅ ገቢ ያስገኛል። ይህ ገቢ የክለቡን የስራ ማስኬጃ ወጪዎች ለመሸፈን፣ ዕዳ ለመቀነስ፣ አዳዲስ ተጫዋቾችን ለመግዛት ወይም የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ይጠቅማል።

በርካታ ክለቦች በዩኢኤፍኤ(UEFA) እና በየሀገራቸው ባሉ የእግር ኳስ ማህበራት የሚወጡ የፋይናንስ ህጎች ይገደባሉ። ተጫዋቾችን ከአካዳሚዎቻቸው አሳድገው ሲሸጡ የሚያገኙት ትርፍ 'ንጹህ ትርፍ' ስለሆነ፣ እነዚህን ህጎች ሳያጡ የገንዘብ ሚዛናቸውን እንዲጠብቁ ይረዳቸዋል። የአካዳሚ ተጫዋቾችን ወደ ዋናው ቡድን ሲያሳድጉ ውድ የሆኑ ዝውውሮችን እና ከፍተኛ የደመወዝ ክፍያዎችን ከውጭ ተጫዋቾች ለመግዛት የሚያወጡትን ወጪ ይቀንሳሉ የሚለውም አስተያየት የተንታኙ ሮማን ግራሃም ነው። አያይዞም ሲቀጥል የተጫዋቾች ሽያጭ ስኬት የአካዳሚዎችን ጥራት እና የኢንቨስትመንት ፍላጎትን ይጨምራል። ይህ ደግሞ ለወደፊት ተጨማሪ ተሰጥኦ ያላቸው ተጫዋቾችን ለማፍራት ይረዳል ይላል።

በዘንድሮው የተጫዋቾች ዝውውር መስኮት ብዙ ገቢ ያገኘው የጀርመኑ አርቢ ሌብዢግ ክለብን ለአብነት ጠቅሶ ጎል ዶት ኮም በድረ ገፁ ባስነበበው ጽሑፍ እንዳሰፈረው ወጣት ተጫዋቾችን በማፍራት እና በማሳደግ የሚታወቁ ክለቦች በዓለም አቀፍ ደረጃ አዎንታዊ ምስል ይገነባሉ። በአጠቃላይ፣ ተጫዋቾችን አሳድገው የሚሸጡ ክለቦች ዘመናዊውን የእግር ኳስ ንግድ ስትራቴጂ በሚገባ ተረድተው በተሳካ ሁኔታ እየተጠቀሙበት ነው። ይህ ሞዴል ለክለቦች የገንዘብ አቅም ከማሳደጉም በላይ ስፖርታዊ ብቃታቸውን ለማሻሻልና ዘላቂ የእድገት ጎዳና ለመከተል ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

ድረ ገፁ ለአብነት የጠቀሰውን የጀርመኑ አርቢ ሌብዢግ ክለብን ልምድ በወፍ በረር አንስተን ጽሑፋችንን እንቋጭ፡፡ ክለቡ ከሌሎች ትልልቅ ክለቦች በተለየ መልኩ ትኩረቱን የሚያደርገው ልምድ ባላቸው እና ከፍተኛ ዝና ባተረፉ ኮከቦች ላይ ሳይሆን፣ ከ24 ዓመት በታች የሆኑ ወጣት እና ተሰጥኦ ያላቸው ተጫዋቾችን በማስፈረም ላይ ነው። የክለቡ ስኬት መሰረትም በዓለም ዙሪያ ባለው ሰፊ አውታር (Network) እና ሳይንሳዊ ትንተና ላይ የተመሰረተ መሆኑ ሲሆን፣ ተጫዋቾችን ለመለየት እና ለመገምገም የስፖርት መረጃዎችን (Sports Analytics) በስፋት ይጠቀማሉ።

ክለቡ የሚያስፈርማቸውን ወጣት ተጫዋቾች በከፍተኛ ደረጃ በማሰልጠን፣ የጨዋታ ልምድ እንዲያገኙ በማድረግ እና ችሎታቸውን በማሻሻል ዋጋቸውን ይጨምራል። ከጥቂት ዓመታት በኋላ እነዚህ ተጫዋቾችን ለሽያጭ ያቀርባሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ጥቂቶችን ብንጠቅስ በ2023/24 የውድድር ዘመን በ90 ሚሊዮን ዩሮ ወደ ማንቸስተር ሲቲ ያቀናው ጆሽኮ ግቫርዲዮል፣ በ2023/24 የውድድር ዘመን በ70 ሚሊዮን ዩሮ ሊቨርፑልን የተቀላቀለው ዶሚኒክ ስዞቦዝላይን፣ በ2024/25 የውድድር ዘመን በ55 ሚሊዮን ዩሮ ወደ ባርሴሎና ያመራውን ዳኒ ኦልሞን ከብዙ በጥቂቱ መጥቀስ ይቻላል፡፡